የቅጣት አወሳሰን ወጥነትና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የቅጣት ማንዋል ዝግጅት ጥናትና የመፍትሄ አማራጮች

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ከጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ

በመካሻ አበራ

ማስታወሻ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ 1997 በአንቀጽ 84(4) እንደተደነገገው የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትና ወጥነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ እንዲያወጣ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከ 80 በመቶ በላይ የሚሆኑት የወንጀል ክሶች የሚመሰረትባቸውን 10 የወንጀል አይነቶች በመምረጥ የቅጣት መመሪያ ለማዘጋጀት ባለሙያዎችን በመጋበዝ ጥናት

ሲጠና የቆየ ሲሆን፣ በተለያየ ምክንያት ከተመረጡት በሶስቱ ጥናቱ ባይጠናቀቅም በተመረጡት በ 7 ት የወንጀል አይነቶች ላይ ጥናትና የቅጣት አወሳሰን ረቂቅ *መመሪያ* ወይም ህጎች ቀርበዋል። እነዚህ ባለሙያዎችም፣

1. አቶ ሃይለ አብርሃ (የትግራይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት)
2. አቶ ሰለሞን አረዳ (የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ም/ፕሬዚዳንት)
3. አቶ ተፈሪ ገብሩ (የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ)
4. አቶ አዱኛ (በኦሮሚያ ክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ)
5. አቶ ዘካርያስ ኤርኮላ (በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የህግ አማካሪ)
6. አቶ መስፍን ማሬ (በግል የጥብቅና ስራ የተሰማሩ)
7. አቶ መኳሻ አበራ (የፌዴራል የፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ማእከል ም/ዳይሬክተር)

ናቸው።

በእነዚህ 7 የቅጣት አወሳሰን የውሳኔ ህጎች ላይ ከፌዴራልና ከክልል ፍርድ ቤቶችና አቃቤ ህግ መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች በተሳተፉበት የሶስት ቀን አውደጥናት በማድረግ ጥናቶቹ ውይይት የተደረገባቸውና የዳበሩ ሲሆን፣ በቀጣይነትም ለፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም የበላይ አመራር ኮሚቴ ቀርበው ውይይት ተደርጎበትና እርማትና *መመሪያዎቹን* በመስጠት ተቀባይነት አግኝተዋል። በቀጣይነት ወደትግበራ ለመግባት እንዲቻል ጥናቶቹ ወደአንድ ጥናት ተጠቃለውና ተዋህደው አንድ የጥናት ሰነድ ሆነው እንዲቀርቡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመወሰኑ ምክንያት ይህ የተጠቃለለና የተዋህደ ሰነድ ቀርቧል።

በሰባቱም ባለሙያዎች የቀረቡት የውሳኔ ህጎች የየራሳቸው *መለያ* መገለጫዎች ቢኖራቸውም በዋነኛነት በሁለት ሞዴሎች ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው። ስለሆነም በዚህ ጽሁፍ በየጥናቶቹ ያሉትን *መ*ለስተኛ ልዩነቶች በማስታረቅና በማስወገድ ወደሁለት አማራጭ ሞዴሎች ተስተካክለው እንዲቀርቡ ተደርገዋል።

ይሁንና በተለይም ለጥናቶቹ መሰረት በሆኑት የወንጀል ህግ የቅጣት ድንጋጌዎች ግምገማ፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ግምገማ፣ የተለያዩ አገራት ተሞክሮ ግምገማን በሚመለከት በዚህ ጽሁፍ የቀረበ አዲስ ነገር የለም። በ 7 ቱ ጽሁፎች ውስጥ የነበሩትን ድግግሞሽን በሚያስወግድ *መ*ልኩ ብቻ እንዳለ የተወሰዱ ናቸው። ስለሆነም የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ህጎችና ልምዶችን ግምገማ በተመለከተ በየቦታው የግርጌ ማስታወሻ ባይገኝም፣ ከዋናዎቹ የጥናት ሰነዶች የተወሰዱ እንጂ የዚህ ጽሁፉ የጥረት ውጤቶች አለመሆናቸውን ግልጽ ሊደረግ ይገባል። ስለሆነም ስለቅጣት አወሳሰን የተደረገው ጥናት ላይ የበለጠ ለመረዳት ለዚህ ጥናት መሰረት የሆኑትን 7 የጥናት ሰነዶችን ማንበብ ጠቃሚነት አለው።

በዚህ ጥናት ወደሁለት አማራጭ ሞዴሎች አንሰው የቀረቡትም ወጥነትና ተናናቢበት እንዲኖራቸው በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የተሰሩ ስራዎች ቢኖሩም፣ እነዚህ ሞዴሎች አዲስ ህጎች ሳይሆኑ፣ በ 7 ቱ ባለሙያዎች በቀረቡ ጥናቶች በተለያየ *መ*ልኩ ተንጸባርቀው

የነበሩትን እና ከየጥናቱ ጠቃሚ የሆኑትን በመውሰድና በማዋሀድ የተሰራ በመሆኑ፣ ይህ ስራ የሚመሰገንና ተቀባይነት የሚያገኝ ከሆነ በዋነኛነት ምስጋናውን ሊወስዱ የሚገባቸው ሁሉም አጥኚዎች መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል።

በመጨረሻም የጥናቱን ስራ የሰሩትን ባለሙያዎችን ሙሉ ክፍያ በመሸፈን እንዲሁም አስፈላጊውን ፋሲሊቲ በማሟላት የጥናቱ ስራ ከዚህ ደረጃ እንዲደርስ ለረዳው ጀስቲስ ፎር ኦል ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ምስጋና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ማውጫ

መግቢያ.....3

ክፍል አንድ.....7

በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርአት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች፣ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችና የፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔዎች ግምገማ.....7

1.1. የቅጣት አላማና ግቦች በኢትዮጲያ የወንጀል ህግ.....7

1.2. የቅጣት አወሳሰን የሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች.....10

1.3. የ 1997 የወንጀል ህግ ቅጣት አወሳሰንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ግምገማ.....11

1.4. በፍርድ ቤት የሚሰጡ ቅጣቶች አወሳሰን ግምገማ፣.....17

ክፍል ሁለት.....22

በቅጣት አወሳሰን የሌሎች አገራት ልምድ.....22

2.1. አሜሪካ.....22

2.2. እንግሊዝ.....26

2.3. ኔዘርላንድ.....29

2.4. ፊንላንድ.....33

2.5. ጀርመን.....35

2.6. ፈረንሳይ.....37

ክፍል ሶስት.....37

በኢትዮጵያ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የቀረቡ አማራጮች.....37
3.1. የሚዘጋጀው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አላማና ውጤት.....38
3.2. ‹በቀመር› ወይም ‹ፎርሙላ› ላይ የተመሰረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ.....40
3.3. የወንጀል ደረጃዎችን እንደክብደታቸው/አደገኝነታቸው ደረጃ በማውጣት ላይ የተመሰረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ› 51
3.3.1. በስልጣን አለአግባብ መገልገል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች፣.....52
3.3.2.የስርቆት ወንጀል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች**(665** እና **669)**.....62
3.3.3.የማታለል ወንጀል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች **(692** እና **693)**.....67
3.3.4.የውንብድና ወንጀል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች**(670** እና **671**.....71
3.3.5.በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ከዝቅተና ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች **(555-560)**.....77
3.3.6.ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ መነሻና መድረሻ ቅጣት፣.....83
3.3.7.ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ መነሻና መድረሻ ቅጣት፣.....91
3.3.8.የቅጣት ማክበጃ አሰላልን በሚመለከት፣.....107
3.3.9.የቅጣት ማቅለያዎችን አሰላል በተመለከተ፣.....109
3.3.10.ተደራራቢ ወንጀል በሆነ ጊዜ፣.....113
3.3.11.ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ፣.....113
3.3.12.ቅጣትን በመሰለው ማቅለልን በተመለከተ፣.....113
3.3.13.ተጨማሪ ማስታወሻዎች.....114
3.4. የሁለቱ አማራጭ ሞዴሎች ጠንካራ ጎንና ውሱንነት ትንተናና አስተያየት.....115
ማጠቃለያ.....118
ዋቢ ሰነዶች.....120

መግቢያ

የወንጀል ህግ ዋና አላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርአት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው። ይህ አላማ የሚሳካውም ወንጀል እንዳይፈጸም በመከላከል ሲሆን፣ ይህንንም የሚያሳካው ለህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት አደጋ የሆኑ የወንጀል ተግባራትን እና እነዚህን መፈጸም የሚያስከትለውን ቅጣት ሰዎች አውቀው ከወዲሁ ከህገወጥ ተግባር እንዲቆጠቡ ማስተማርና ማሳወቅ ሲሆን፣ ይህ ሳይሳካ ቀርቶ ጥፋት አድራጊዎች ሲኖሩ እነዚህን ተገቢውን ቅጣታቸውን እንዲያገኙ በማድረግ ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጽሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው።[1]

የወንጀል ህጉ የቅጣት አላማ ግቡን ይመታ ዘንድ ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት መነሻና ጣሪያ ቅጣት ያስቀመጠ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣት የታሰበለትን አላማና ግብ ያሳካ ዘንድ ቅጣቱን ለመወሰን የሚያገለግሉ መርሆዎችንና መመሪያዎችን የያዙ ጠቅላላ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችንም የያዘ ነው።

ይሁንና በፍርድ ቤቶቻችን ሲሰጥ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ተሞክሮ በመነሳት፣ በቅጣት አወሳሰን የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን መርሆዎችና ድንጋጌዎች በራሳቸው በቂ ስላልሆኑ፣ የወንጀል ህጉን መርሆዎችና ድንጋጌዎች በሚደግፍና በሚያሟላ መልኩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትንና ወጥነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ማውጣት እንዲችል በዚሁ የወንጀል ህግ አንቀጽ 88(4) ስልጣን ሰጥቶታል።

[1] የወንጀል ህግ አንቀጽ 1

መመሪያውን የማውጣቱ መርህ የሚጠይቀው በተመሣሣይ ወንጀል ጥፋተኛ የተሰኙ እና ተመሣሣይ የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያቶች የቀረቡባቸው እና የግል ሁኔታዎቻቸው ተመሳሳይ የሆኑ አጥፊዎች ተመሣሣይ ወይም ተቀራራቢ ቅጣት ሊጣልባቸው የሚገባ መሆኑን ነው።

የቅጣት አወሳሰን አንድ ወጥነት እና ትክክለኛነት ጠቃሚነቱ በአንድ ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ ለሚቀጣ ወንጀል ፈፃሚ ብቻ ሣይሆን በወንጀሉ በቀጥታ ተጠቂ ለሆኑት የግል ተበዳዩች እና ተመሣሣይነት እና አንድ ወጥነት በጐደለው የቅጣት አወሳሰን ምክንያት በወንጀል የፍትህ አስተዳደሩ ላይ እምነት ለሚያጣው ለጠቅላላው የህብረተሰብ ክፍል ነው። ዲሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ለመገንባት እንዲሁም ልማት እና እድገትን ለማፋጠን እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶች አጠናክሮ ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ፍትሃዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ተገማችና ሚዛናዊ የሆነ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የሚከተል ውጤታማ የፍትህ አሰጣጥ እንዲኖር የቅጣት አወሳሰን ወጥነትና ትክክለኛነት ያለው መሆን የግድ ይላል።

የቅጣትን አንድ ወጥነት እና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ህገ መንግስታዊ እና ከመሠረታዊ መብቶች በተለይ ከእኩልነት መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል መሆናቸው በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሣይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ እንደሚደረግላቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 በግልጽ ተመልክቷል። ስለዚህ ለምሣሌ ከህጉ መንፈስ ውጭ የተጣለ ከባድ ቅጣት ቢኖር በዘፈቀደ የተወሰነ ብቻ ሣይሆን የዜጎችን እኩል የህግ ጥበቃ የማግኘት መብት የሚጥስ እና የዳኝነት አካሉም በህገ መንግስቱ የተመለከቱ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶቻቸው የማክበርና የማስከበር ግዴታውን አለመወጣቱን ስለሚያመለክት የቅጣት ውሣኔው ህገ መንግስታዊ ነው አይባልም።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረትም በአጠቃላይ ከ 80 በመቶ በላይ የሚሆነውን የፍርድ ቤት መዝገቦች የሚይዙትን፣ በተደጋጋሚ የወንጀል ድርጊት እየተፈጸመባቸው የሚቀርቡትን በቁጥር 10 የሆኑ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ላይ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለማዘጋጀት የወሰነ ሲሆን፣ እነርሱም፣

1. በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወንጀል፣
2. ከታክስ ጋር በተያያዙ ወንጀሎች፣
3. በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣
4. የስርቆት ወንጀል፣
5. የማታለል ወንጀል፣
6. የውንብድና ወንጀል፣
7. አስገድዶ መድፈር ወንጀል፣
8. ተራ አገዳደል ወንጀል
9. የግድያ ወንጀል

ናቸው። በእነዚህ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንዲወጣላቸው በተመረጡ የወንጀል ድንጋጌዎች ላይም ጥናት እንዲያደርጉ 10 የሕግ ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ በተለያየ ምክንያት በሶስቱ (የታክስ ወንጀል፣ ከባድ የሆነ የሰው ግድያ) ላይ የተጀመረው ጥናት ባይጠናቀቅም፣ ከተመረጡት በ 7 ቱ የወንጀል ድንጋጌዎች ላይ በባለሙያዎች ሰባት የጥናት ሰነዶች የየራሳቸውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አማራጭ ሀሳብ ይዘው ቀርበዋል።

ይህ ጽሁፍ እነዚህ በተለያዩ ሰባት ባለሙያዎች ተዘጋጅተው የቀረቡት ጽሁፎች ውስጥ ያሉትን ድግግሞሽ በመቀነስ፣ እንዲሁም በቀረቡት አማራጭ ሀሳቦች መካከል ያሉትን መለስተኛ ልዩነቶች በመቀነስና በማጠቃለል አንድ የጥናት ሰነድ ሆኖ የቀረበበት ነው።

ይህ ጽሁፍ የወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ለሚገኙ የሚጣለው ቅጣት ወጥነትና ትክክለኛነት ስለሆነም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ሊያመጣ የሚችል እንዲሆን ምን ሊደረግ ይገባል? ለሚለው የመፍትሄ ሀሳብ የሚያቀርብ ሲሆን፣ በቅድሚያ በአጠቃላይ በወንጀል ህጉ ስለቅጣት አወሳሰን የተደነገጉት ድንጋጌዎች፣ እያንዳንዱን የቅጣት መነሻና መድረሻ ለመወሰን፣ ማክበጃና ማቅለያዎችን ተግባራዊ ስለሚደረግበት ሁኔታ በወንጀል ህጉ ስለቅጣት አወሳሰን በጠቅላላው ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች ያላቸው ውስንነት በተመለከተ አጭር ትንተና ያቀርባል።

አሁን ባለው የቅጣት አወሳሰን የህግ ማእቀፍ መሰረት በፍርድ ቤቶች በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ጥፋተኞች ላይ የሚጣለው ቅጣት ወጥነት ያለው፣ ተመጣጣኝነት፣ ግልጽነትና ተገማችነት ያለው ስለመሆኑ በቁጥር ከ 500 ያላነሱ መዝገቦች የተመረመሩ ሲሆን፣ በእነዚህ መዝገቦች የተወሰኑትን ቅጣቶች፣ ቅጣቱን ለመጣል እንደምክንያት ሆነው የቀረቡትን ምክንያቶች እና ቅጣትን ለመወሰን በቀረቡት ምክንያቶችና በተጣለው ቅጣት መካከል ምክንያታዊ ግንኙነት ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ ስለሆነም በቅጣት አወሳሰን አንጻር ያለው ልምድና ተሞክሮ ምን እንደሚመስል አጭር ትንተናና ድምዳሜ ያቀርባል።

በመቀጠልም በቅጣት አወሳሰን ዝርዝር አሰራር የተለያዩ አገሮችን አሰራሮችና ተሞክሮዎች በአጭሩ ለማቅረብ ይሞክራል።

ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ዋናው ክፍል የሆነው በተመረጡት የወንጀል ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙ ሰዎች ላይ ቅጣት አወሳሰንን ለመርዳት የሚያስችል ስልትና ዘዴን በተመለከተ ሁለት አማራጮችን የያዘ ዝርዝር አሰራር ያቀርባል። በመጨረሻም የሁለቱንም አማራጭ ሞዴሎች ጥንካሬና ውስንነት በሚመለከት ትንታኔ በመስጠትና ምን ሊደረግ እንደሚገባ አስተያየት በመስጠት ይጠናቀቃል።

በዚህ ጽሁፍ የቀረበው ጥናት አላማና ግብ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህ በአገሪቱ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር አዲስ በመሆኑ ለዚህ ዝግጅት የሚሆን ተሞክሮ በአገሪቱ አይገኝም። ከዚህ በተጨማሪ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎችም ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ተሞክሮ እና ልምድ የሌላቸው መሆኑ በጥናቱ ውጤት ላይ የሚያሳድረው የራሱ የሆነ ውስንነት እንዳለውም መግለጽ ተገቢ ነው። ለዚህ ጥናት ጽሁፍ አላማ ሲባል የቅጣት ውሳኔ መዝገቦች የተመረመሩና

የተገመገሙ ሲሆን፣ ቁጥራቸው ወደ 500 አካባቢ ይሆናል። ይህ በአጠቃላይ በሌሎች አገሮች ለቅጣት አወሳሰን በማለት ከሚጠኑ የውሳኔ መዛግብቶች ቁጥር አንጻር ሲታይ በጣም ትንሽ ነው። ይሁንና ጥናቱ ሊያሳይ ከፈለገው ሁኔታ አንጻር በቂ ናቸው። ለዚህ ጥናት ዝግጅት ሲባል የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በተመለከተ በኢንተርኔት ከተገኙ ጽሁፎች በስተቀር በአካል በመገኘት ወይም ከእነዚህ አገሮች በተግባር ላይ ከሚሰሩት ጋር የተደረገ ውይይት ባለመኖሩ በተወሰነ መልኩ የጥናቱን ጥልቀት ሊገድበው እንደሚችል መገመት ይቻላል። በአጠቃላይ ጥናቱ የተሰራው በእነዚህ ውሱንነቶች ውስጥ መሆኑ ከግምት በማስገባት የጥናቱ ውጤት ችግሮችና እንከኖች ሊኖሩበት እንደሚችሉ መገመት ተገቢ ነው። ይሁንና ይህ ጥናት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አይደለም። ስለሆነም ይህ ጥናት የጀመረው ከፍተኛ አላማ በቀጣይነት በሚደረጉ ጥናቶች እየዳበረ ጥናቱ የተነሳበትን አላማ የኢትዮጵያን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የሚያሳካ ስለመሆኑ ግን አያጠራጥርም።

ክፍል አንድ

በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርአት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች፣ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችና የፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔዎች ግምገማ

1.1. *የቅጣት አለማና ግቦች በኢትዮጲያ የወንጀል ህግ*

በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርአት ውስጥ በወንጀል ጥፋተኞች ላይ ተገቢውን ቅጣት በትክክል መወሰን እጅግ ውስብስብና አስቸጋሪ በመሆኑ! ከማንኛውም ሂደት በተለየ መልኩ የፍርድ ቤት ዳኞችን በእጅጉ የሚፈታተን ከባዱ ስራ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ዳኞች በወንጀል ሕጉ መሰረት የሚሰጣቸውን የመወሰን ነፃነት (discretion)፣ በቅጣት ፍልስፍና እና መርህ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ፣ የያዙትን የወንጀል ጉዳይ ተፈጥሮና የነገሩ አካባቢ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ተገቢ ነው ብለው ያመኑበትን ቅጣት መወሰናቸው ባይቀርም! የቅጣት አወሳሰን ስልት አወዛጋቢና አጠቃላይ ስምምነት ያልተደረሰበት በመሆኑ፣ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የቅጣት አወሳሰን ስሌት መፍጠር አስቸጋሪ ነው።

የወንጀል ቅጣት አወሳሰን ስልት የአንድ ሀገር የወንጀል ሕግ መሰረት የሚያደርገው መርህና ሊደረሰበት የሚፈልገው ግብ በተገቢው መንገድ ማሳካት ይጠበቅበታል። በመሆኑም በመጠኑም ቢሆን የአንድ ሀገር ወንጀል ሕግ አላማና ግብ ከሌሎች ሀገሮች የወንጀል ሕጎች የሚለይበት የራሱ የሆነ መገለጫ ባሕርይ ስለሚኖረው የቅጣት አወሳሰን ዘዴውም በዚያው ልክ አንዱ ከሌላው ላይመሳሰል ይችላል።

አንድ የወንጀል ህግ ከበስተጀበርባው የሚያጅቡት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ እሴቶችና ፖሊሲዎች መኖራቸው ስለማይቀር እነዚህ የእሴቶችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ከሀገር ወደ ሀገር በተለያየ መጠን የቅጣት አወሳሰን ዘዴም መለያየቱ አይቀርም።

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ የቅጣት አወሳሰን ዓላማና ግቦች ታሪክ! ከወንጀል ሕጉ አፈጣጠርና ታሪካዊ እድገት ጋር በእጅጉ የተቆረኘ በመሆኑ! ከ 15 ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በከፊል የወንጀል ህግ ጠባይ ያንፀባርቅ እንደነበር ከሚነገርበት የፍትህ-ነገስሰት ሕግ ጀምሮ የነበሩትን ሁኔታዎች መዳሰሱ ባይጎዳም! ለዚህ ጥናት መሰረት የሆነውና በ 1997 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ ብቻ መመስረቱ ጊዜንና ጥረትን ይቆጥባል የሚል እምነት አለን። ስለዚህ በዚህ ፅሁፍ የወንጀል ህግ ስንል በ 1997 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግን እንደሚያመለክት ግንዛቤ በመውሰድ ወደ ዋናው ነጥብ እንግባ።

የወንጀል ህጉ አላማና ግቦች በህጉ አንቀፅ አንድ እንደዚሁም በመግቢያው ላይ በዝርዝር ተገልፀው ይገኛሉ። በዚህ መሰረት የወንጀል ሕጉ ዓላማ ስለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገራቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎችን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ሲሆን! የሕጉ ግብ ደግሞ ወንጀል እንዳይፈፀም ለመከላከል የሚያስችል ስለወንጀሎችና ስለማያስከትሉት ቅጣት በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይህ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀለኞቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ ! ለሌሎችም ማስተማሪያ እንዲሆኑ፣ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎችን በመውሰድ እንደሆነ ! በወንጀል ህጉ አንቀፅ አንድ ተገልፀዋል። በዚህ መሰረት የወንጀል ህጉ ከላይ ከተዘረዘሩት የቅጣት አላማና ግቦች ውስጥ በተለይ፣ ችሎታ ማሳጣትን፣ ማስጠንቀቂያ ወይም መቀጣጫነትን፣ እና እርማት ወይም መልሶ ማቋቋምን አዋህዶና አካቶ ይዟል ለማለት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ሕጉ የቅጣት ዓላማና ግቦች በሕጉ በጠቅላላም ሆነ ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ ስለቅጣት አወሳሰን በሚደነግጉት አንቀፆች ስር ተንፀባርቆ ይገኛል።

በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸው የህጉ ድንጋጌዎች፣ ስለ እያንዳንዱ የቅጣት ዓላማና ግብ በግልፅ ዘርዝረው ባያመለክቱም፣ በተለያዩ የወንጀል ዓይነት ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የተደነገጉት የቅጣት አይነትና መጠን፣ ተቀባይነት ያላቸውን የቅጣት አላማና ግብ ለማሳካት እንደሆነ አንፀባራቂ ናቸው። ለምሳሌ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል በአንቀፅ 117 የተደነገገው የሞት ፍርድ፣ በአንቀጽ 118 የተገለፀው እድሜ ልክ እስራትን ጨምሮ የተደነገገው ነፃነትን የማሳጣት ቅጣት፣ በአንቀፅ 123 ስር የተደነገገው ከቤተሰባዊ፣ ሙያዊና ተመሳሳይ ከሆኑ መብቶች የመሻር ቅጣት፣ በአንቀፅ 127 ስር የተገለፀው ከወታደራዊ መአረግና የስራ ገበታ መቀነስ ወይም ማስለቀቅ፣ እንዲሁም ከአንቀጽ 142-150 የተገለፁት የተለያዩ ፍቃድ የመንጠቅ ቅጣቶች ! የወንጀል ሕጉ የቅጣት ዓላማ ወንጀል የመፈፀም ችሎታን ማሳጣት እንደሆነ የሚያስረዱ ናቸው።

በሌላ በኩል ከአንቀፅ 157-167 በተገለፀው መሰረት በወጣት ጥፋተኞች ላይ የሚወሰዱ የጥንቃቄና አያያዝ እርምጃዎች! ከአንቀፅ 129-133 በተገለፀው መሰረት ከፊል የወንጀል ሀላፊነት ባለባቸው ጥፋተኞች ላይ የሚወሰዱ የጥንቃቄና የአያያዝ ሁኔታዎች፣ በአንቀፅ 190 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች መሰረት ወንጀለኞችን በአመክሮ መልቀቅ፣ እንዲሁም በአንቀፅ 134 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች መሰረት የሚወሰዱ አጠቃላይ የወንጀለኞች አያያዝና የጥንቃቄ እርምጃዎች በእርማት ወይም ወንጀለኛን መልሶ በማቋቋም ዓላማ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

በተጨማሪ፣ በተለይ ከባድና አሰቃቂ ወንጀል በሚፈፅሙ ወንጀለኞች ላይ የተከበደና ከፍተኛው ቅጣት እንዲወሰንባቸው መሰረታዊ የሆኑ የቅጣት ማክበጃ ድንጋጌዎች እንደዚሁም በልዩ ልዩ የህጉ ድንጋጌዎች መገለፁ የቅጣቱ አላማና ግብ ማስጠንቀቂያና መቀጣጫ ጭምር ሊሆን እንደሚገባው ያስገነዝባል።

የወንጀል ህጋችን በቅጣት አማካኝነት ሊጠብቀውና ሊያሳካው የፈለገው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ የፖሊሲ አጀንዳ በመቅደሙ ላይ በሰፊው ተዘርዝሮ ይገኛል። በዚህ መሰረት "የወንጀል ህጉ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን የሚያስችልና የተረጋጋ የነፃ ገበያ ስርአት እንዲጎለብት የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር፣ የሀገራችን ትክክለኛ የፍትህ ስርአት ለማስፈን እንደሚረዳ በመታመኑ ...." በማለት በመቅድሙ ፓራግራፍ ላይ ተሰምሮበት ይገኛል። እንደዚሁም የወንጀል ህጉ ዓላማ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ፣ በህብረተሰቡ ላይ ወንጀል እንዳይፈፀም ለመከላከል ግብ የሚመታበት አንዱና ዋናው መንገድ ቅጣት እንደሆነ በመቅድሙ ላይ ተገልፀዋል።

1.2. *የቅጣት አወሳሰን የሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች*

በወንጀል ህጋችን በግልጽ ተለይቶ ነጥሮ ባናገኘውም፣ በተለያዩ ድንጋጌዎች ውስጥ ቅጣት ሊከተላቸው የሚገባቸው መርሆዎችን እንመለከታለን። በዋነኛነት የወንጀል ህጉ ቁጥር 88(2) ቅጣት ሲወሰን ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮችን የሚያመለክት ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ አንቀጽ 88(4) ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት ወጥነትንና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ መመሪያ እንዲያወጣ ማስቀመጡ እነዚህ የቅጣት አወሳሰን መመሪያችን ሊሆኑ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው።

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አዉጥተዉ በተገበሩ አገሮች እንዲሁም ስለቅጣት አወሳሰን በተጻፉ የምርምርና የጥናት ጽሁፎች ከቅጣት አወሳሰን ጋር በተያያዘ የቅጣት አወሳሰን ሊገዛባቸው የሚገቡ መርሆዎችን ያስቀምጣሉ። እነዚህም በአጭሩ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ተመዛዛኝነት/**proportionality**/፦ ይህ መርህ ከተከሰሰዉ ሰዉ አንፃር የሚታይ ሆኖ የቅጣት ዉሳኔዉ ሊሰነዘር የሚገባዉ ዉስን የሆኑ ነገሮችን በመንተራስ ሳይሆን የወንጀሉን ዓይነት፣ ክብደት፣ የተከሳሹን የጥፋተኛነት ደረጃ እና ያለፈ የወንጀል ታሪኩን በማገናዘብ መሆን እንዳለበት ነዉ።

ለ. ወጥነት/**consistency**/፦ በእርግጥ ወንጀል ግላዊ ባህሪ ያለዉ በመሆኑ የአንዱ ምክንያት ለሌላዉ የሚተላለፍ አይደለም። ይህ ማለት ግን ወጥ በሆነ መልክ ተመሳሳይ የሆኑ የወንጀል ጉዳዮች አንፃራዊ ልዩነቶች ተጣበዉ ተቀራራቢ የሆነ ዉሳኔ ሊወሰንባቸዉ አይቻልም ማለት አይደለም። ስለዚህ ይህ መርህ ፍርድ ቤቶች እንደፈለጉት ወይም እንዳሻቸዉ ቅጣት ከመጣል ገታ በማድረግ ወጥ የሆነ በየጊዜዉ መሻሻል የሚታይበት እንዲሆን ያስችላል ማለት እንደመርሆ ያስቀምጠዋል።

ሐ. አድሎ የሌለበት/**Fairness/:-** ብዙ ዓይነት የማህበረሰብ ክፍል ባለበት አገር በፍትህ አካላት ዘንድ የህሳብ ወደ አንድ ወገን ማጋደል እንዳይከሰት የቅጣት አወሳሰን መርህ ክልከላ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል። ስለዚህ በዘር፣ በፖሊቲካ፣ በዖታ፣ በኃይማኖት፣ በህብት ደረጃ እና በመሳሰሉት መነሻ ልዩነት ሳይደረግ ቅጣት መጣል እንዲቻል ያደርጋል ማለት ነዉ።

መ. ግልፅነት/**Transparency/:-** ግልፅነትና ተጠያቂነት አብረዉ የሚሄዱ መርሀዎች ናቸዉ። ዳኞች ዉሳኔቸዉን በምክንያት ለማስደገፍ ይገደዳሉ። በምክንያት ማስደገፍ ግዴታ ሆኖ በተጨማሪም የሚያቀርቡት ምክንያት ቅጣት ለማክበድም ሆነ ለማቅለል ግልፅነት ያለዉ መሆን ይጠበቃል። የቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ እነዚህን ምክንያቶች ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ በግልፅ በማስቀመጥ ሌሎች የህብረተሰብ አካላትም በግልጽ አይተዉት መገመት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ማለት ነዉ። የግልፅነት መርሀዉ የዳኞችን የተጠያቂነት አድማስንም ያሰፋል ማለት ነዉ።

1.3. *የ1997 የወንጀል ህግ ቅጣት አወሳሰንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ግምገማ*

በ 1997 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል ሕግ የቅጣት አወሳሰን መነሻ የሕጉ አንቀፅ 87 ነው። በዚህ መሰረት የወንጀል ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሰረት የሕጉ መንፈስና ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ በሚቻልበት አኳኋን፣ እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን በጠበቀ መንገድ መፈፀም እንዳለባቸው ይደነግጋል። ስለሆነም ፍ/ቤቶች የወንጀል ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሲወስኑ፣ በአንድ በኩል እንደ መነሻ ማድረግ ያለባቸው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ አንድ የተገለፁትን የሕጉን ዓላማዎችና ሊሳካ የሚፈለገውን ግብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በሕጉ ልዩ ክፍል የተገለፁትን የቅጣት መነሻና መድረሻ ነጥቦችንና የቅጣቱን ዓይነት በመለየት ነው።

በወንጀል ሕጉ አንቀፅ አንድ እንደተገለፀው የወንጀል ሕጉ ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት ሊንከባከበው የሚፈልገው የሕ/ሰቡን አጠቃላይ መብትና ጥቅምን ነው። ስለሆነም ፍ/ቤቶች የሚወስንዋቸው ቅጣቶችና የሚወስዱአቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች የሕ/ሰቡ ጠቅላላ መብትንና ጥቅምን መሰረት በማድረግ፣ ሕጉ በቅጣት አማካኝነት ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ማሳካት መቻል ይጠበቅባቸዋል።

በወንጀል ህጉ ማንኛውም የወንጀል ድንጋጌ በመጣስ ወንጀል ተፈጽሞ በተገኘ ጊዜ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት መጠንና አይነት ምን እንደሆነ ለመረዳት በቅድሚያ በድንጋጌው ወንጀሉን ለማቋቋም የተቀመጡትን ፍሬነገሮችና የቅጣት መነሻና መድረሻ ጣሪያውን መመልከት ተገቢ ነው።

በወንጀል ህጉ ከቁጥር 238 ጀምሮ የተዘረዘሩትን የወንጀል ድንጋጌዎችን ስንመለከት በጣም በሚበዙት ድንጋጌዎች ለወንጀሉ በተደነገጉት የቅጣት መነሻና ጣሪያ መካከል ሰፊ ልዩነት እንዳለ መረዳት እንችላለን። አብዛኛዎቹ የቅጣት መነሻና መድረሻዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

- ከ 1 አመት እስከ 10 አመት
- ከ 3 አመት እስከ 10 አመት
- ከ 5 አመት እስከ 15 አመት
- ከ 7 አመት እስከ 15 አመት
- ከ 5 አመት እስከ 20 አመት
- ከ 10 አመት እስከ 25 አመት

ስለሆነም እንደዚህ አይነት የቅጣት ሬንጅ ባላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ውስጥ የሚወድቁ የወንጀል አይነቶች፣ አንዱ ከሌላው በአፈጻጸሙ እና በሌሎችም ምክንያቶች ቢለያዩም አንዱን ከሌላው አነጻጽሮ ቅጣቱን ለመጣል እንዲቻል ዳኛው ሌሎች መስፈርቶች ወይም መለኪያዎች እንደሚያስፈልጉት ግልጽ ነው።

ህግ አውጪውም ይህንን በግልጽ በመረዳት ዳኛው ለቅጣት አወሳሰኑ እንዲረዳው በማለት ስለቅጣት አወሳሰን በጠቅላላ ክፍሉ እንዲደነገጉ አድርጓል።

ቅጣት ሲወሰን ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በወንጀል ህጉ በቁጥር 88 (2) የተመለከቱ ሲሆን፣ እነርሱም፣

- የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣
- ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣
- ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሀሳቡን አላማ፣
- የግል ኑሮውን ሁኔታ፣
- የትምህርቱን ደረጃ፣
- የወንጀሉ ከባድነት እና
- የአፈጻጸሙ ሁኔታዎች

የሚሉ ናቸው።

ከዚህ በላይ የተቀመጡትን መለኪያዎች ዳኛው እንዴት አድርጎ ነው ቅጣቱን ለመወሰን የሚጠቀምባቸው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም።

እነዚህ ምክንያቶች አብዛኛዎቹን ቅጣትን ለማቅለል በተደነገገው ድንጋጌ(ቁጥር 82) እንዲሁም ቅጣትን ለማክበድ በተደነገገው ድንጋጌ(ቁጥር 84) ተመልክተው ስናያቸው፣ ቅጣቱን ለመወሰን የሚረዱት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ቅጣቱን በማክበድ ወይም ቅጣቱን በማቅለል እንደሆነ እንረዳለን።

የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች (አንቀጽ 84) በአምስት ዋና ክፍሎች ተከፍለው እናገኛቸዋለን። እነርሱም፣

ሀ. ወንጀሉን ያደረገው በክህዲነት ወይም በወስላታነት፣ወራዳነትን ወይም መጥፎ አመልን በሚያሳይ ምቀኝነት፣ጥላቻ፣ስግብግብነት፣መጥፎ ነገርን ለመስራት ወይም ሰውን ለመጉዳት ፍጹም ፈቃደኛ በመሆን፣በተለየ ክፋት ወይም ጨካኝነት እንደሆነ፣

ለ. ስልጣኑን፣ ተግባሩን ወይም የተጣለበትን እምነት ወይም ሀላፊነት ያላግባብ በመገልገል እንደሆነ፣

ሐ. ወንጀሉ በቀድሞ ጥፋተኝነቱ፣ወንጀልን ማድረግ ሙያ ወይም ልማድ አድርጎ መያዙ፣የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ ጊዜና ቦታ የአፈጻጸሙ አኳኋን በተለይም በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሳሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኛነቱን አሳይቶ እንደሆነ፣

መ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው ወንጀል ለመፈጸም በተደረገ ስምምነት መሰረት ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ወይም ወንጀል ለመፈጸም ከተቋቋመ ቡድን ጋር በመስማማት ወይም አባል በመሆን ይልቁንም እንደወንጀል ቡድን ሹም፣ አደራጅ ወይም መሪ በመሆን እንደሆነ፣ ወይም፣

ሠ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በእድሜው፣ በጤንነቱ፣ በኑሮው ወይም በስራው ሁኔታ ልዩ ጥበቃ በሚያሻው ሰው ላይ በተለይም ለመከላከል አቅም በሌለው፣ መንፈሰ ደካማ፣ በሽተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ፣ እስረኛ ወይም በቅርብ ዘመዱ ላይ ወይም የበላዩ ወይም የበታቹ በሆነ ሰው ላይ፣ በህግ በተቋቋመ ባለስልጣን ወይም የስራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንድ የህዝብ አገልጋይ በሆነ ሰራተኛ ላይ እንደሆነ ነው።

የሚሉ ናቸው። እነዚህ ምክንያቶች ከሞላ ጎደል በአንቀጽ 88 በጥቅሉ ከተቀመጡት መለኪያዎች ከፊሉን በዝርዝር ያስቀመጡ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

የቅጣት ማቅለያዎች ደግሞ በአንቀጽ 82 የተመለከቱት ሲሆኑ፣ እነርሱም፣

ሀ. ወንጀለኛው ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም እንደሆነና ያጠፋውም በእውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ፣

ለ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ያደረገው በተከበረና በግል ጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ፍላጎት ወይም ከፍ ባለ ሀይማኖታዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማህበራዊ እምነት ተነሳስቶ እንደሆነ፣

ሐ. ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተበደለው ከፍተኛ ቁሳዊ እጦት ወይም የህሊና ስቃይ ደርሶበት፣ ከፍ ያለ አደጋ የሚያመጣ ነገር የተቃጣበት መስሎት፣ መሰረት ያለው ፍርሀት አድሮበት ወይም ደግሞ ሊታዘዝለት በሚገባው ወይም በስልጣኑ ስር በሚያስተዳድረው ሰው ተጽእኖ ምክንያት እንደሆነ፣

መ. ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተበደለው ሰው ጠባይ ከብርቱ ፈተና ላይ ጥሎት፣ በከባድ ጸብ ቀስቃሽነት ወይም በአስጸያፊ ስድብ ምክንያት ወይም ደም ከሚያፈላ ንዴት፣ ስቃይ ወይም ብስጭት ላይ ጥሎት እንደሆነ፣ ወይም ከፍ ያለ አስገዳጅነት ባለው ስሜትን በሚለውጥ ሁኔታ ወይም ምክንያት ባለው የመንፈስ ሁከት ላይ ሆኖ እንደሆነ ወይም፣

ሠ. ወንጀለኛው ወንጀሉን ካደረገ በኋላ በእውነት የተጸጸተ መሆኑን፣ በተለይም በደል ላደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ፣ ወይም ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትህ አካላት በማቅረብ ወይም የወንጀሉ ጥፋት ላደረሰው ጉዳት በተቻለ መጠን በመካስ መጸጸቱን በተግባር አሳይቶ እንደሆነ ወይም ተከስሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ ነው።

እነዚህም በተመሳሳይ በከፊል በቁጥር 88 የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚመለከቱ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ በህጉ ልዩ ማክበጃና ልዩ ማቅለያ ምክንያቶች ተብለው ቅጣቱን እንዴት እንደሚያከብዱና እንደሚያቀሉ የተቀመጡ ድንጋጌዎች አሉ።

<u>ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች</u>

የወንጀል ህጉ የወንጀሎችን መደራረብና መደጋገምን እንደ ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሚወስድ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ አንቀፅ 85 ተደራራቢ ወንጀሎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣቱን ከወሰነ በኋላ፣ የእያንዳንዱን ቅጣት በመደመር ቅጣቱን እንደሚወስን፣ ይሁንና በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለየቅጣቱ አይነት ከተደነገገው ከፍተኛ ጣሪያ በላይ እንደማይሄድ ይደነግጋል። በሌላ በኩል ደጋጋሚነት በሚያጋጥምበት ጊዜ፣ ለአዲሱ ወንጀል ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ አልፎ ለመወሰን እንደሚችል ይሁንና በህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገው ጣሪያ በላይ እንደማይሄድ ይደነግጋል።። (ቁጥር 184-188)

<u>ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች</u>

በሌላ በኩል ዳኛው በመሰለው ቅጣቱን ሊያቀል ይችላል ተብሎ ተደንግጎ በሚገኝበት ጊዜ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ ወንጀል በተቀመጠው የቅጣት መነሻ ሳይወሰን መነሻ ከሆነው ቅጣት ዝቅ ብሎ ለመወሰን ስልጣን እንዳለው ያመለክታል። ይሁንና በዚህ መልኩ የሚወሰነው ማናቸውም ቅጣት በህጉ ጠቅላላ ክፍል ለየቅጣቱ አይነት ከተደነገገው ዝቅተኛ መነሻ ዝቅ ማለት እንደማይችል ይደነግጋል። (ቁጥር 180)

እንግዲህ ዳኛው በወንጀል ህጉ መሰረት ጥፋተኛ የሆነን ወንጀለኛ ቅጣት ሲወስን ታሳቢ ሊያደርጋቸው የሚገቡት እነዚህን የጠቅላላ ክፍሉን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ነው። ይሁንና ዳኛው እነዚህን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችና ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ወጥነት፣ ተመጣጣኝነትና ፍትህዊ የሆነ ቅጣት ላይ ለመድረስ ይችላል ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ አይደለም የሚል ነው። ለዚህም ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. በህጉ እንደተመለከተው ዳኛው በመጀመሪያ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱን ማስላት እንዳለበት ይደነግጋል።[2] ተደራራቢ ወንጀሎች በሚኖሩም ጊዜ በመጀመሪያ ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣቱን መወሰን አለበት። ይሁንና ለወንጀሉ መነሻ ቅጣቱ ስንት ነው? ይህ በዝርዝር ድንጋጌዎቹ የትም ቦታ አናገኘውም። ለምሳሌ በ 407(1) መሰረት መነሻው 1 አመት ሲሆን መድረሻው 10 አመት ነው ይላል። ይሁንና ዳኛው ከየት ነው መነሳት ያለበት? ከአንድ አመት? ከአምስት አመት? ከአስር አመት? ስለሆነም መነሻው ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ መነሻውን ለማስቀመጥ ከዳኛ ዳኛ ሊለያይ እንደሚችል መገመት ይቻላል። በዚህ ሁኔታ(context) ውስጥ ወጥነትንና ሚዛናዊነትን ማረጋገጥ በጣም አስቸጋሪ ነው።
2. በቀጣይነት ህጉ እንደሚያዘው ተግባራዊ መደረግ ያለበት የቅጣት ማክበጃዎች ከቀረቡ፣ በቀረቡት ማክበጃዎች መሰረት ቅጣቱን ማክበድ ነው።[3] ይሁንና ሁሉም ማክበጃዎች ተሟልተው በሚገኙ ጊዜ መድረሻው መሆን ያለበት የትኛው ነው? ለወንጀሉ የተቀመጠው ጣሪያ ነው? በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ውስጥ የሚወድቁ ወንጀሎች ቢሆኑም አንዱ ከሌላው የሚበላለጥ በመሆኑ፣ ለሁሉም ተመሳሳይ ጣሪያ ላይ መድረስ ተገቢ ነው? አንድ ማክበጃ ብቻ ቢሆን መድረሻው የት ነው? ሁለት ማክበጃ ቢኖር መድረሻው የት ነው? ወዘተ። እነዚህም ለዳኛው ህሊናዊ ዳኝነት የተተዉ ናቸው።
3. ማቅለያ ምክንያቶቹም በተመለከተ ቅጣቱ ሲቀል መድረሻው በጥቅሉ ነው የተቀመጠው። ለምሳሌ ከአንድ አመት በላይ በጽኑ እስራት ለሚያስቀጡ ቅጣቶች ቅጣቱ ሲቀል መነሻው አንድ አመት እንደሆነ አስቀምጧል። ከአንድ አመት በላይ የጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ያላቸው በ 407(2) መሰረት ከ 7 አመት እስከ 15፣ እንዲሁም በ 407(3) መሰረት ከ 10 አመት እስከ 25 አመት ነው። ስለሆነም ከየትኛው ተነስቶ ነው አንድ አመት ላይ የሚደረሰው? በየደረጃው ላለው የወንጀል አይነት መድረሻው መሆን ያለበት ስንት ነው? ለእነዚህም ህጉ የሚያስቀምጠው መልስ የለም።

ስለሆነም በወንጀል ህጉ የተቀመጡትን የቅጣት ድንጋጌዎችና ስለቅጣት አወሳሰን የተቀመጡት ድንጋጌዎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ቅጣቶች ወጥነት፣ ተመዛዛኝነት ያለው፣ ፍትሀዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ አይደለም። በዚህ ምክንያት ለተመሳሳይና ተቀራራቢ የወንጀል አፈጻጸሞች ተመሳሳይና ተቀራራቢ ቅጣት ለመጣል አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

1.4. *በፍርድ ቤት የሚሰጡ ቅጣቶች አወሳሰን ግምገማ፣*

ከዚህ በላይ እንደቀረበው የወንጀል ህጉ ስለቅጣት አወሳሰን ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት እና ፍትሀዊ የሆነ ቅጣት ለመወሰን የማያስችሉ ቢሆንም፣ በፍርድ ቤቶች እስከአሁን ድረስ ቅጣት የተወሰነባቸውን መዝገቦች ምን ይመስላሉ? በህጉ ላይ ያለውን ክፍተት ሊዘጋ ወይም ሊቀንስ በሚችል መልኩ የዳበረ ልምድ አለ ወይ? ከሚለው አንጻር በቀጣይነት እንመለከታለን።

[2] የወንጀል ህግ ቁጥር 189
[3] ተደራራቢ ወንጀል ወይም ደጋጋሚነት ከሌለ፣

ለዚህ ጥናት አላማ እስከ 500 የሚደርሱ የቅጣት ውሳኔዎች የተመረመሩ ሲሆን፣ የስነስርአት ህጉ እንደሚደነግገው ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት የአቃቤ ህግና የተከሳሽ/ጠበቃውን አስተያየት ይጠይቃል። ከተመረመሩት መዝገቦች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል የቅጣት አስተያየት አቀራረቦችና ፍርድ ቤቱ ወደቅጣት መጠን ውሳኔ የሚደርስበትን ስንመለከት ዝርዝሩ ከሞላ ጎደል የሚከተለውን ይመስላል።[4]

ከተሰባሰቡት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው አቃቤ ህግ የቅጣት ሀሳብ ሲጠየቅ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቅሳቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ሪከርድ ስላለበት ቅጣቱ ከብዶ ይወሰን፣
- ለወንጀለኛውና ለህዝብ ትምህርት የሚሰጥ ቅጣት ይወሰን፣
- በተከሰሰበት ቁጥር ያለው ቅጣት ተመጣጣኝ ይወሰን፣
- ከተሰጠው ሀላፊነትና አደራ አንጻር ትምህርት የሚሰጥ ቅጣት ይወሰን፣
- ትልቅ ሀላፊነት የተሰጠውና ሀላፊነቱን በአግባቡ ያላከናወነ በመሆኑ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰን፣
- ሆን ብሎ ከህግ ሸሽቶ በማምለጡ ተገቢው ቅጣት ይሰጠው፣
- ከፍተኛ የመንግስት ሀብት የመዘበረ በመሆኑ ከብዶ ይቀጣ፣
- በአፍቅሮ ንዋይ የሰራ ስለሆነ ቅጣቱ ይክበድ፣
- ካደረሰው ጉዳት አንጻር ተመጣጣኝ ቅጣት ይሰጠው፣
- በስግብግብነት በመስራቱ ከብዶ ይወሰን፣
- ሪከርድ ስለሌለበት ተገቢው ቅጣት ይሰጠው፣
- ድርጊቱ አደገኛ ስለሆነ ከብዶ ይወሰን፣
- ሀሰተኛ ምስክሮችን በማቅረቡ ቅጣቱ ይክበድ፣
- ወዘተ

የሚሉ ናቸው። እነዚህ በጥቅሉ ተመጣጣኝ ቅጣት ይሰጠው፣ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰን በሚል ጥቅል አባባል ከመደምደማቸው ያለፈ፣ ምን ያህል ሊቀጣ እንደሚገባ የማያሳዩ፣ ዳኛው ለቅጣት አወሳሰን የሚረዳውን መንገድ ወይም አቅጣጫ የሚያሳዩ አይደሉም።

በተከሳሽ የሚቀርቡት የቅጣት ሀሳቦችም ከሞላ ጎደል የአቃቤ ህጉን የሚመስሉ ናቸው።

- ሪከርድ የሌለው በመሆኑ፣
- ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድር በመሆኑ፣
- ህብረተሰቡ ውስጥ ጥሩ ጠባይ ስላለው፣
- ጥፋተኛ የሆኑት ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም በመሆኑ፣

[4] የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 149

- ቤተሰቦች በከፍተኛ ችግር ላይ ያሉ በመሆኑ፣
- ብቁ ትምህርት የሌላቸው በመሆኑ፣
- የደከሙ እናት አለው፣
- በመንግስት ስራ ብዙ ያገለገሉ በመሆኑ፣
- በወጣትነት የእድሜ ክልል የሚገኙ ስለሆነ፣
- በእስር ላይ በቆየሁበት ጊዜ የተማርኩ ስለሆነ፣
- ከመንግስት ስራ ሌላ መተዳደሪያ ስለሌለኝ፣
- ደመወዜ ቆሞ ቤተሰቤ እየተጉላላ ስለሆነ፣
- በእውቀት ማነስ የፈጸምኩት ስለሆነ፣
- በኤችአይቪ ኤድስ ተጠቂ ስለሆንኩኝ፣
- ለአገር ሉአላዊነት የቆሰልኩ ስለሆነ፣፣
- የ 2 ወር አራስ በመሆኜ፣
- በትጥቅ ትግሉ ተሳታፊ የነበርኩ በመሆኜ፣
- ወዘተ፣

ተከሳሾች ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ምክንያቶች በማቅረብ ቅጣቱ እንዲቀል፣ ወይም በገደብ እንዲለቀቁ ይዘረዝራሉ እንጂ ምን ያህል ሊቀልል እንደሚገባ የሚያስቀምጡት የለም። እርግጥ ከአቃቤ ህጉ በተሻለ እስከአሁን ያለው እስር በቅቶ በነጻ ልለቀቅ፣ በገደብ ይደረግልኝ የሚሉ አሉ። እነዚህንም የሚሉት አንድም ፍላጎታቸውን ሊያሟላ ስለሚችል እንጂ የቅጣቱ መጠን ካቀረቡት ማቅለያ ምክንያት ጋር ያለውን ግንኙነት አያስረዱም።

ዳኞች በዚህ መልኩ ተገቢው ርዳታ ሳይቀርብላቸው ነው የሚወስኑት። አጠቃላይ ስንመለከተው ዳኞች ቅጣቱን ለመወሰን ምን ይጠቀማሉ?

<u>ቅጣትን ለማክበድ</u>

- የወንጀል ሪከርድ አለው
- የወንጀል አፈጻጸሙ አደገኛነት
- በወስላታነት የተፈጸመ ነው።
- ወንጀል የተፈጸመው አስቀድሞ ዝግጅት ተደርጎበት በመሆኑ አደገኛነቱን ያሳያል
- ስልጣኑንም አለአግባብ በመጠቀም በመሆኑ የአፈጻጸሙን አደገኛነት ያሳያል
- በተሳትፎ ደረጃም ሌሎችን በማሳተፍ በመምራት አስተዋጽኦ አድርጓል።
- ድርጊቱ የተፈጸመው በአፍቅሮ ንዋይ በመሆኑ፣
- ተከሳሾች እቃውን የገዙት በባለሙያ ተመክረውና እያወቁ በመሆኑ፣
- የመንግስትን መመሪያ እያወቀ በመጣሱ፣

- በትምህርት የዳበረና ክፉና ደጉን በሚገባ የሚያውቅ በመሆኑ፣
- ድርጊቱ ፀጥታን እናስከብራለን የሚል ሽፍን የተፈፀመ በመሆኑ ከባድ ነው፣

<u>ቅጣትን ለማቅለል</u>

- የወንጀል ሪከርድ የለውም ስለሆነም አደገኛ አይደለም።
- የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነው።
- ታማሚው ማረሚያ ቤት ቢገባ ሞቱ ይፋጠናል።
- የመንግስት መስሪያ ቤት አሰራር ለወንጀሉ አፈጻጸም አስተዋጽኦ ያደረገ በመሆኑ
- ብዙ አመት በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገለ በመሆኑ፣
- የድርጊቱ አፈጻጸም አደገኛነትን አያሳይም
- የግል ተበዳይ ጉዳት አልደረሰበትም
- አፈጻጸሙ ቀላል ነው።
- ሪከርድ ስላልቀረበበት የቀድሞ ታሪኩ መልካም ነበር።
- መብት እናስጠብቃለን በሚል የተፈጸመ በመሆኑ፣
- ተከሳሽ በጎ አድራጊ በመሆኑ፣
- ጡረተኛና በእድሜ የገፉ በመሆኑ
- የጡረታ ጊዜው የደረሰ በመሆኑ፣
- የአስም በሽታ ያለበት በመሆኑ
- ትምህርት የሌላቸውና በቅንነት የተፈጸመ በመሆኑ
- ፍ/ቤት ብዙ በመመላለሳቸው ትምህርት አግኝበተዋል፣
- እናቱን የሚጦርና ከስራ ተባሮ ዝቅተኛ ስራ በመስራት ላይ መሆኑ ምት ውስጥ ገብቷል
- ድርጊታቸውም ከባድ ባለመሆኑ ቅጣቱ ሊቀል ይገባል

የሚሉ ናቸው። በተወሰኑ መዝገቦች ደግሞ ፍርድ ቤት የትኛውን መስፈርት እንደሚጠቀሙ ሳይገልጹ በጥቅሉ የግራ ቀኙን ሀሳብ አገናዝበን የሚከተለውን ቅጣት ሰጥተናል ይላሉ።

ዳኞች እነዚህን ምክንያቶች ይጥቀሱ እንጂ፣

- በየትኛውም መዝገብ ቅጣቱን ለመወሰን መነሻው ስንት መሆን እንዳለበት ተመልክቶ አይታይም።
- በማክበጃነት የቀረቡትንና በማቅለያነት የቀረቡትን ምክንያቶች የሚቀበለውና የሚቀበሉትንና የማይቀበሉትን ከለዩ በኋላ፣ ከምክንያቶቹ ጋር ግንኙነቱን ለማስረዳት በማይቻል መልኩ በጥቅሉ የቅጣቱ መጠን ይቀመጣል።

ስለሆነም፣

- መነሻ የቅጣት መጠኑ ስንት እንደሆነ፣

- በማክበጃነት የተቀመጡት ምክንያቶች ቅጣቱን በማክበድ ያላቸው አስተዋጽኦ እንዲሁም ማቅለያ ምክንያቶች እንዴት አገልግለው ቅጣቱ እንደቀለለ፣

ለማወቅ አይቻልም። በአጭሩ ቅጣቱን ለመወሰን በቀረቡት ምክንያቶችና በተወሰነው ቅጣት መካከል ያለው ምክንያታዊ ግንኙነትን ለማስረዳት የሚያስችል አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ በወንጀል ህጉ ቁጥር 88 (2) ያሉትን ነጥቦች በቅጣት ውሳኔ ዉስጥ እንዲሁ ከመዘርዘር ባሻገር ትኩረት እና ተገቢ ትርጉም ሰጥተዉ የሚተገብሩበት ሁኔታ አይታይም።

የፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ መዝገቦች ውጤት ስንመለከት በወንጀል ህጉ ያለውን ክፍተት ለመዝጋት የሚያስችሉ ሊሆኑ ይቅርና እንዲያውም የባሰ የወንጀል ህጉ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችን ጨርሶውኑ የተዉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ቢያንስ ከዳኛ ዳኛ በሚደረሰው የቅጣት መጠን መለያየት መኖሩን የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ሊያስቀሩት ባይችሉም፣ ነገር ግን ህጉ ያስቀመጣቸው ስነስርአቶች ማለትም በቅድሚያ መነሻ ቅጣቱን መወሰን፣ ቀጥሎ ማክበጃ ምክንያቶችን ተመልክቶ ቅጣቱን ማክበድ፣ በመቀጠልም ማቅለያ ምክንያቶችን ተመልክቶ ቅጣትን ማቅለል በሚል በህጉ ላይ የተቀመጠው መመሪያ ተከብሮ አናገኝም። ስለሆነም በህጉ ላይ ያለውን ክፍተት ከማሟላት ይልቅ፣ ወጥነት የሌለው መያዣና መጨበጫ የሌለው የቅጣት አወሳሰን ልምድ ያለን መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ቅጣትን ለመወሰን የሚያስችል ጋይድላይን ባለመኖሩም የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ለማቅረብ፣ በማስረጃ ለማስረዳት ይህ ነው የሚባል ተገቢው ዝግጅትም ስለማይደረግ፣ ውሳኔው በህሊና ግምት እንደሚወሰን መገመት አያዳግትም። በዚህ አይነት የአወሳሰን ስርአት ውስጥ ወጥነት ያለው ነው፣ ምክንያታዊ ነው ተመጣጣኝነት ያለው ውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር መመኘት ህልም ነው። በሆነ አጋጣሚ ተመሳሳይ ለሆኑ ወንጀሎች ተመሳሳይ ቅጣት ቢጣል የአጋጣሚ ከመሆን አልፎ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ስለሆነም፣

1. በወንጀል ህጉ የተቀመጡት የቅጣት መነሻና መድረሻ እንዲሁም ስለቅጣት አወሳሰን የተቀመጡት ድንጋጌዎች በራሳቸው ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት፣ ፍትሀዊና ተገማችነት ያለውን ቅጣት ለመስጠት የሚያስችሉ አይደሉም።
2. በተጨባጭ የተመረመሩት መዝገቦችም በቅጣት አወሳሰን ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት፣ ፍትሀዊነትና ተገማችነት ያለው ቅጣት እየተሰጠ እንደሆነ አያመለክቱም ብቻ ሳይሆን፣ የተዘበራረቁና ለማስረዳት የሚያስቸግሩ ቅጣቶችን የሚሰጡ ሆነው ይታያሉ።

ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት፣ ፍትሀዊ እና ተገማችነት ያለው ቅጣት ለመጣል፣

1. እንደወንጀሉ አይነት/ ከአፈጻጸሙ፣ ከደረሰው ጉዳት ወይም ከተገኘው ጥቅም አንጻር፣ መነሻው ምን ሊሆን እንደሚገባ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።
2. ከተቀመጠው መነሻ ቅጣት በመነሳት ቅጣቱን ማክበጃ ምክንያቶች ሲኖሩ፣ ወጥ የሆነ የቅጣት ማክበጃ ስርአት መዘርጋት ያስፈልጋል።

3. የቅጣት ማቅለያንም በተመሳሳይ ተግባራዊ ለማድረግ የቅጣት ማቅለያዎችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ዝርዝር አሰራር መደንገግ ያስፈልጋል።

ክፍል ሁለት

በቅጣት አወሳሰን የሌሎች አገራት ልምድ

የቅጣት ጋይድላይን አውጥቶ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ተጠቃሽ ሆነው የሚገኙት በአንግሎ ሳክሶን ወይም የኮመን ሎው የህግ ስርአት በሚከተሉ አገሮች ነው። ስለሆነም ለዚህ ጥናት አላማ ከአሉት የቅጣት ጋይድላይኖች ወካይና የተሻሉ ናቸው የሚባሉትን ለማየት ተሞክሯል። ይሁንና የኮድ ስርአት ባላቸው አገራትም የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ ያለውን ልምድ ለመመልከት ተሞክሯል። በዚህ ክፍል እነዚህን ተሞክሮዎች እንመለከታለን።

2.1. *አሜሪካ*

1. አሜሪካ የፌዴራል አስተዳደር ሥርዓት ተከታይ እንደመሆኗ መጠን በፌደራል መንግስት የፌዴራል የወንጀሎች ተብለዉ በተለዩትና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚያዩአቸዉ የወንጀል ጉዳዮች የቅጣት አወሳሰን ጋይድላየን አዉጥታለች። የተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶችም /ክልሎችም/ የየክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የክልል መንግስታት የቅጣት አወሳሰን ጋይድላየን አዉጥተዉ ሥራ ላይ አዉለዋል።
2. በስራ ላይ ያሉት የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች የተዘጋጁት የተለያዩ አካሄዶችን በመከተል ሲሆን አንዳንዶቹ አስገዳጅ የቅጣት ሬንጅ ሲያዘጋጁ፣ ሌሎቹ አስገዳጅ ያልሆነ በማዘጋጀት ሲሰሩ፣ አንዳንዶቹ ለተወሰነ ወንጀል አይነት ብቻ መመሪያ ሲያዘጋጁ፣ ሌሎቹ ለሁሉም የወንጀል አይነቶች አዘጋጅተዋል።
3. የቅጣት መመሪያዎቹ ሲዘጋጁ ሁሉም ግለት ይቻላል አላማ ያደረጉት ተመሳሳይ የሆኑ ናቸው። እነርሱም፣

    - የሚሰጡ ቅጣቶች አንድ ወጥና ተመሳሳይ እንዲሆን በማድረግ ምክንያታዊ ያልሆኑ የቅጣት ልዩነቶችን ማስወገድ፣
    - የቅጣት ተመጣጣኝነት (Proportionality) ማስጠበቅ፣
    - የተጠያቂነት (Accountability) መርህን ማንጸባረቅ፣
    - ቅጣት በምክንያት የተደገፈ በማድረግ ፍትህዊነትን ማሳየት፣
    - ቅጣት ሊገመት የሚችልና ግልጽነት በተሞላበት የሚሰጥበትን ሁኔታ መፍጠር የሚሉ ናቸው።

4. ለዚህ ጥናት አላማ የፌዴራል መንግስቱ የቅጣት ጋይድላይን በአብዛኛዎቹ ግዛቶችም ተግባራዊ ስለሚሆን ይህው ቀርቧል።
5. የቅጣት ጋይድላይኑ United States Sentencing Commission Guideline Manual ይባላል።
6. በ 1985 በወጣዉ የቅጣት አወሳሰን ማሻሻያ ህግ መሠረት ነፃ የሆነ የቅጣት አወሳሰን ኮሚሽን የሚባል ተቋቁሟል። በቅጣት አወሳሰን ማሻሻያ ህግ ላይ የተመለከተዉ የኮሚሽኑ የመጀመሪያ ዓላማዉ ብሔራዊ የሆነ የቅጣት አወሳሰን ፖሊሲ እንዲያወጣ፣ በወንጀል ህጉ የተመለከተዉ የቅጣት ዓላማ ግቡን እንዲመታ ማድረግ እና በቅጣት አወሳሰን ረገድ ተመሳሳይ በሆኑ ወንጀሎችና የቀድሞ የወንጀል ታሪክ ባላቸዉ አጥፊዎች ላይ የሚታየዉን ተገቢ ያልሆነ ልዩነት በማስወገድ ትክክለኛና ፍትሀዊ የሆነ የቅጣት አወሳሰን ልምድ እንድጎለብት ማድረግ ናቸዉ። የቅጣት አዋሳሰን ጋይድላየኑ ሥራ ላይ እንዲዉል የተፈለገዉ ዋናዉ ምክንያት በተመሳሳይ ወንጀል የሚከሰሱ ወንጀል ፈፃሚዎች ተመሳሳይ የቅጣት መጠን እንድወሰንባቸዉ ታስቦ ነዉ። ኮሚሽኑ በተጨማሪም በምርምርና በጥናት አስደግፎ የወጣዉ ጋይድላየን በአግባቡ በፍርድ ቤቶች ሥራ ላይ መዋሉን ግምገማ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል።
7. በጋይድላይኑ የወንጀል ደረጃዎችን ከታች ወደላይ (vertically) ከዝቅተኛ 1 ጀምሮ እስከ 43 በሚደርስ ደረጃ (offence level) የተከፋፈለ ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ ደረጃ መነሻና መድረሻ ያለው የቅጣት ሬንጅ ተቀምጧል። በዚህ መሰረት ዝቅተኛው የቅጣት ሬንጅ ከ 0-6 ወር ሲሆን፣ ከፍተኛው የቅጣት ሬንጅ ከ 360 ወራት እስከ እድሜ ልክ እስራት ነው። በሌላ በኩል የጥፋተኛውን የወንጀል ታሪክ በተመለከተ ወደጎን (horizontally) በአምስት ካታጎሪ ደረጃ ወጥቶለት እናገኛለን። በየደረጃው ባሉት የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል overlapping ያለ ሲሆን፣ የቅጣት ሬንጁም ተመሳሳይ ከ 6 ወር ያላነሰ ወይም ከመነሻው ቅጣት ከ 25 በመቶ ያልበለጠ እንዲሆን ተደርጎ የተቀመጠ ነው።
8. በእያንዳንዱ ተከታታይ ደረጃዎች የሚቀጥለው ደረጃ የቅጣት መነሻ ቀድሞት ከነበረው የቅጣት ደረጃ የቅጣት ጣሪያ ዝቅ ብሎ እንዲጀምር የተደረገ ስለሆነ ተከታታይ የቅጣት ደረጃዎች የቅጣት መድረሻቸውና መነሻቸው overlap ያደርጋል።
9. ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 18 ድረስ በቅጣት መነሻና ጣሪያ መካከል ያለው ልዩነት የስድስት ወር ሲሆን፣ ከ 19 ነኛው ደረጃ ጀምሮ ቀስ በቀስ ልዩነቱ እየሰፋ ከ 7 ወር ጀምሮ እስከ 81 ወራት ይዘልቃል። ይሁንና የቅጣቱ ጣሪያ ከቅጣቱ መነሻ 25 በመቶ ያልበለጠ ነው። ለዚህም ዋና ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው በቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለው ልዩነት (range) በተቻለ መጠን እንዲጠብና በተመሳሳይ ደረጃ ለሚወድቁ ወንጀሎች የሚሰጠው ቅጣትን ተቀራራቢ በማድረግ ወጥነትና ተመጣጣኝነትን ማረጋገጥ ነው።
10. ከዚህ ሌላ ዋናው የጋይድላይኑ አካል የሚባለው የወንጀል ተግባራት በዝርዝር የተገለጹበት ሲሆን፣ በዚህ ዝርዝር መመሪያ ውስጥ የተዘረዘረው የወንጀል ተግባር የትኛው ቨርቲካል የቅጣት ደረጃ (vertical offence level) ማለትም (ሌቨል/እርከን 20 ወይም 21 ወዘተ...) ላይ እንደሚያርፍ ያስቀምጣል።

11. ስለሆነም ዳኛው የወንጀል አፈጻጸሙን ፍሬነገር በመመልከት በየትኛው የወንጀል ተግባር ዝርዝር ውስጥ እንደሚወድቅ ያውቃል። ለዚያ የወንጀል ተግባር የቅጣቱ መነሻ ስንት እንደሆነ እዚያው ጋይድላይን ላይ ስለሚያመለክት ለወንጀሉ መነሻ ቅጣቱን ለመወሰን ከስንት እንደሚጀምር ያውቃል። ለምሳሌ በእርከን 20 የተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ ከ 33-41 ወራት (ከ 2 አመት ከ 9 ወር - 3 አመት ከአምስት ወር) ነው።

12. ከዚህ በመቀጠል ግን የወንጀሉን ልዩ ባህርይ መሰረት በማድረግ የተወሰኑ ነገሮች ተሟልተው ከሆነ፣ ከተቀመጠው ደረጃ ወደላይ ከፍ ወይም ወደታች ዝቅ ሊል ይችላል። ለምሳሌ ጉቦ መቀበልን በተመለከተ የተመለከተውን እንመልከት፣[5]

    1. ወንጀሉ ተፈጽሞ ሲገኝ መነሻው የወንጀል ደረጃ 6 ኛ ሌቭል/እርከን ነው።
    2. ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ባለስልጣን ባልሆነ ከሆነ ሁለት ሌቭል/እርከን ወደታች ይቀንሳል። 4 ኛ ሌቭል ይሆናል ማለት ነው።
    3. ወንጀሉ ከአንድ በላይ ከሆነ በሁለት ሌቭል ወደላይ ይጨምራል። 8 ኛ ሌቭል ይሆናል ማለት ነው።
    4. የተገኘ ጥቅም ወይም በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት(ከሁለቱ ከፍተኛ የሆነው ታይቶ) በዚህ መሰረት የቅጣት ደረጃውም ይጨምራል።
    5. በከፍተኛ ባለስልጣን የተፈጸመ ከሆነም ሌቭሉ በ 4 ይጨምራል።
    6. የተፈጸመው የወንጀል አይነት ለምሳሌ ከውጭ አገር ለሚገባ ሰው ፓስፖርት መስጠት ወዘተ ከሆነ በሁለት ሌቭል ይጨምራል።
    7. ወንጀሉ የተደረገው ሌላ ወንጀል ለመፈጸም ከሆነ፣ ያ ሊፈጸም ለታሰበው ወንጀል ያለበት ደረጃ አሁን ካለው ከፍ ያለ ከሆነ፣ ከፍ ባለው መሰረት ይስተካከላል።
    8. ወንጀሉ የተፈጸመው ሌላ ወንጀል ለመደበቅ ከሆነ፣ የዚያኛውን ወንጀል ሌቭል/እርከን ከዚህኛው ከፍ የሚል ከሆነ ከፍተኛው ሌቭል ተግባራዊ ይደረጋል።
    9. የተገኘው ጥቅም ወይም ጉዳት በገንዘብ ማስቀመጥ በማይቻልበት ጊዜ (ለምሳሌ የማይገባውን ላይሰንስ ማግኘት ቢሆን) ዝቅተኛ ገንዘብ በሚለው ውስጥ የሚጠቃለል ይሆናል። ይሁንና ድርጊቱ ከሀገር ከህደት ጋር የተያያዘ ከሆነ ከፍተኛ ገንዘብ ከሚለው ጋር የሚጠቃለል ይሆናል።

13. በዚህ መልኩ የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም በመጨረሻ የትኛው እርከን/ሌቭል ላይ እንደሚደርስ ይታወቃል።

14. በዚህ መልኩ ተደምሮና ተቀንሶ የሚያልፍበት ቨርቲካል የቅጣት ሌቭል ከታወቀ በጎዋላ፣ ቀጣዩ ስራ የቀድሞ የወንጀል ታሪኩን በተመለከተ የሚወድቅበትን ካታጎሪ መለየት ነው። ይህንን በተመለከተም ምን ያህል ጊዜ ወንጀል

[5] US sentencing guideline. Part C offences involving public officials and violation of federal election campain laws 2C1.1.

ሰርቶ ተቀጣ፣ የቅጣቱ መጠን ምን ያህል ነው የሚለውን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ነጥብ ስለሚኖር ይህንን መሰረት በማድረግ በድምር የተገኘው ነጥብ፣ ከአምስቱ የወንጀል ካታጎሪዎች የትኛው ላይ እንደሚወድቅ ይለያል።

15. በመጨረሻ የወንጀል ሌቭል(vertical) እና የካታጎሪ ሌቭል(horizontal) የሚገናኙበት ቦታ የተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው። ይህ እንግዲህ መነሻና መድረሻ ቅጣት ያለው ሲሆን፣ በመነሻና በመድረሻ መካከል ያለው ልዩነት የመነሻውን 25 በመቶ ያልበለጠ ነው። ስለሆነም ዳኛው ከዚህ ሬንጅ ውስት ሳይወጣ መነሻው ላይ፣ መሀከል፣ ወይም መድረሻው ላይ ወዘተ የቅጣት መጠኑን ይጥልበታል ማለት ነው።

16. ዳኛው አሳማኝ ምክንያት ካለው ከሬንጁ ውጭ ቅጣት ለመጣል ይችላል። ይሁንና ወደዚህ ውሳኔ ሊያደርሰው ያስቻለውን ምክንያት መግለጽ ይኖርበታል።

17. ሁሉም የወንጀል አይነቶች በተሟላ መልኩ ያልተዘረዘሩ ስለሆነ፣ በጋይድላይኑ ከተጠቀሰው ውጭ ያለ ወንጀል ሲያጋጥም በአናሎጂ የቅጣት መጠንን እንደሚጥሉ ጋይድላይኑ ያስቀምጣል።

2.2. <u>እንግሊዝ</u>

1. በእንግሊዝ የሴንቴንሲንግ ጋይድላይን magistrate court sentencing guideline ተብሎ ይታወቃል። ይህ ጋይድላይን በ 2008 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ ቀድሞ በ 2004 ወጥቶ የነበረውን የሚተካ ነው።
2. ሁሉንም የወንጀል አይነቶች ያካተተ ሳይሆን በርካታ የወንጀል አይነቶችን የሚያካትት ነው። ያልተካተቱት በየጊዜው ጋይድላይን እየተዘጋጀላቸው የሚካተቱ እንደሆነ እራሱ ጋይድላይኑ ይገልጻል።
3. አቀራረቡም አንዱን ወንጀል በመውሰድ(ለምሳሌ ሌብነት ሊሆን ይችላል) በእያንዳንዱ ወንጀል እንደከባድነት (seriousness) ደረጃው ወንጀሉን ሊወክሉ የሚችሉ ምሳሌዎች ወይም ማሳያዎች ተቀምጠዋል። ለእነዚህ ለእያንዳንዳቸው የቅጣት መነሻና መድረሻ አላቸው። (ይህ መነሻና መድረሻ ሲቀመጥ ጥፋተኛ ነኝ ብሎ ላላመነ የተቀመጠ ነው) መነሻ ቅጣቱ የሬንጁ መነሻ ሳይሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ በሬንጁ መሀል ያለ ነው። ለምሳሌ ቅጣቱ ሬንጅ ከ 12 ሳምንት እስከ 18 ሳምንት ቢሆን፣ መነሻው 15 ሳምንት ሊሆን ይችላል። ይህም ቅጣቱ የሚጀምርበት ወይም starting point ነው።
4. የወንጀሉን አደገኛነት (seriousness) ለመወሰን የተጠቀመው አራት የጥፋተኝነት ደረጃዎችን የለየ ሲሆን እነርሱም፣
    5. intention
    6. recklessness
    7. knowledge and
    8. negligence ናቸው።

ስለሆነም ጥፋቱ የተፈጸመው በኢንቴንሽን(intention) ከሆነ የቅጣቱ መጀመሪያ ከፍ የሚል ሆኖ በደረጃ ዝቅ እያለ ይሄዳል ማለት ነው።

3. በዚህ መሰረት ዳኛው መፈጸሙ የተረጋገጠው ወንጀል ከየትኛው ማሳያ ጋር እንደሚመሳሰል ወይም እንደሚቀራረብ በማየት ወንጀሉ የሚወድቅበትን ደረጃ ወይም ክፍል ይለያል ማለት ነው። ለምሳሌ ከሌብነት ጋር በተያያዘ፣ የቅጣት ደረጃውን ለመወሰን የተጠቀመው በወንጀሉ የተገኘውን ገንዘብ መጠን ነው።
    - ከ 2000 ብር በታች ከሆነ ከ band ቢ እስከ 25 ሳምንት እስር ሲሆን፣ የቅጣቱ መጀመሪያ community order ነው።
    - ከ 2000 በላይ ከ 20000 በታች ከሆነ ሬንጁ highlevel community order to crown court ሲሆን፣ መነሻው 18 ሳምንት እስር ነው።[6]
4. በቀጣይነት ቅጣቱን በሬንጁ ውስጥ ከፍ ለማድረግ ወይም ለማቅለል የሚያስችሉ ምክንያቶች ተቀምጠዋል። ማለትም አደገኛቱን የሚጨምሩ ምክንያቶች በምሳሌነት ቀርበዋል። ለምሳሌ በአደራ የተሰጠውን ንብረት ለግል ጥቅሙ ማዋልን በተመለከተ፣
    - የወንጀል ተጎጂው ምን ያህል እንደተጎዳ መመልከት መነሻው እንደሆነ ያስቀምጣል። ስለሆነም የጉዳቱ መጠን በጨመረ ቁጥር ከባድነቱም ይጨምራል ማለት ነው።
    - የተጣለበት አደራ ደረጃ/ማለትም በአጥፊውና በአደራ አስቀማጩ መካከል ያለው ግንኙነትም የበለጠ አደራ እንዲጣልበትና እንዲታመን የሚያደርግ መሆኑም ወንጀሉን አክብዶ ለማየት እንደምክንያት ይታያል።
    - ወንጀሉ የተፈጸመው የተለየ ጥበቃ በሚያስፈልገው ሰው ላይ መሆኑም ወንጀሉን እንደሚያከብደው ያስቀምጣል።
5. በዚህ ውስጥ የወንጀሉን አፈጻጸም ሊያቀሉ የሚችሉ ምክንያቶችም ተዘርዝረዋል። ለምሳሌ ንብረቱን የመለሰ መሆኑ፣ በችግር ምክንያት ወንጀሉን ለመፈጸም የተገፋፋ መሆኑ ወዘተ። ስለሆነም ቅጣት የሚወስነው እነዚህን ማክበጃና ማቅለያ ሁኔታዎች ተመልክቶ ነው። ከዚህ በመነሳት ጊዜያዊ የቅጣት መጠን በሬንጁ ውስጥ ይወስናል። (ይሁንና ፍርድ ቤቱ በቂ ምክንያት ካለው ይህንን በመጥቀስ ከሬንጁ ውጭ የቅጣት መጠን ሊያስቀምጥ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ከሆነ የቅጣት መጠኑ ከሬንጁ በላይ ሊቀመጥ እንደሚችል ጋይድላይኑ ያስቀምጣል።)
6. በቀጣይነት የተከሳሽ ማቅለያዎች ምክንያቶችን በመመልከት ቅጣቱን ሊያቀል እንደሚችል የሚደነግግ አለ። እነርሱም፣ እውነተኛ ጸጸት (Genuine remorse)፣ ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል (Admissions to police in interview)፣ ከህግ አስፈጻሚዎች ጋር ያሳየው ዝግጁነት (Ready co-operation with authorities)

    ናቸው።

[6] Band ቢ ማለት የገንዘብ መቀጮን ለማመልከት ነው። ከራውን ኮርት፣ ኮሚኒቲ ኦርደር ወዘተ የሚሉትን ቴክኒካል ቃላቶች ትርጉም ለመረዳት የጋይድላይኑን የመጨረሻ ማብራሪያ ክፍል በመመልከት መረዳት ይቻላል።ከገጽ 147 ጀምሮ

7. ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ተከሳሽ ጥፋቱን አምኖ ከሆነ እንደገና ሊቀልለት ይችላል። በዚህ ጊዜ አንዳንድ ጊዜ ከሬንጁ በታች ቅጣቱ ሊወርድ ይችላል። ይሁንና መቼ ነው ጥፋቱን ያመነው የሚለው የሚቀለውን መጠን ለመወሰን ያገለግላል። ገና በመጀመሪያው የጥፋተኝነት ማመን ከአለ አንድ ሶስተኛ የሚቀነስ ሲሆን፣ ክርክሩ የሚደረግበት ቀን ከተወሰነ በኋላ ያመነ ከሆነ አንድ አራተኛ ይቀነስለታል። ክርክሩ ከተጀመረ በኋላ ከሆነ አንድ አስረኛ ይቀነስለታል።
8. በመቀጮ የሚቀጣውን ለመወሰን ሳምንታዊ ገቢውን መሰረት ባደረገ መልኩ የቅጣት መነሻውና ሬንጁ ይቀመጣል። ለምሳሌ የቅጣት ሬንጁ ከ 25 እስከ 75 በመቶ የሚሆነው የሳምንት ገቢው ቢሆን፣ መነሻው 50 በመቶ ይሆናል ማለት ነው። መቀጮው በአመት ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ እንደሚሆን ታሳቢ ያደረገ ነው።
9. የተሟላ መረጃ ካላገኘ ወይም ፍርድ ቤቱ የቀረበውን መረጃ የማያምንበት ከሆነ ፍርድ ቤቱ የራሱን ፋይናንሻል ገቢ በመገመት ቅጣቱን ይወስናል። ማስረጃ በሌለ ጊዜ በሳምንት 350 ፓውንድ እንደገቢ አድርጎ ይወስደዋል።
10. ዳኛው የደረሰበትን የቅጣት መጠን እንዴት እንደደረሰ ምክንያቱን እንዲጠቅስ ይጠይቃል።
11. ፍርድ ቤቱ ጉዳት የደረሰ ከሆነ ስለሚካሰውም መጠን መወሰን አለበት። ተጨማሪ ቅጣቶችን ይመለከታል።

በአጭሩ የእንግሊዝ ጋይድላይን አቀማመጥ ይህንን ይመስላል።

2.3. *ኔዘርላንድ*

በ 1983 የታወጀዉ የኒዘርላንድ መንግሰት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በጣም ሰፊ የሆነ አዉድ ያላቸዉን የቅጣት ዓይነቶችና መጠኖች ማለትም የገንዘብ መቀጮ፣ እስራት እና የግዴታ ሥራን ይጨምራል። ህጉ እነዚህን የተለያዩ የቅጣት ዓይነቶችን ቢደነግግም ፍርድ ቤቶች ላይ የቱን የቅጣት ዓይነት፣ መጠን እና ምን ያህል መቅጣት እንዳለባቸዉ ገደብ አይጥልባቸዉ። በህጉ የተቀመጠዉ ዝቅተኛ የቅጣት መጠን አንድ ቀን ሲሆን ከፍተኛዉ የቅጣት መጠን ደግሞ አስራ አምስት ዓመት ሲሆን ቅጣት በሚከብድበት እንደ ነፍስ ግድያ ዓይነት በሆኑ ወንጀሎች እስከ 20 ዓመት ከፍ ሊል ይችላል። ነፍስ ግድያ በመሳሰሉት የዕድሜ ልክ እስራት ቅጣት ፍርድ መወሰን እንደሚቻል ቢመለከትም እነዚህ በአመክሮ መልክ በሂደት እስከ 20 ኣመት ባለዉ የእስራት መጠን ሊቀየሩ ይችላሉ።

ይሄዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ዉስን የሆኑ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ይደነግጋል። ቅጣትን በማክበድ ረገድ ሦስት አጠቃላይ የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎችን ይደነግጋል። እነሱም፦

ሀ. በተደጋገመ ጥፋት ቅጣት

ለ. ተደራራቢ ወንጀሎች በሆኑ ጊዜና

ሐ. የሲቪል ሠራተኛነቱ ምክንያት ወንጀል ፈፅሞ የሚገኝበት ጊዜ ናቸዉ።

ከእነዚህ ከተገለጹት ከሶስቱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አንዳቸዉ በአንድ ጉዳይ ለማክበጃነት በቀረቡ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በ 1/3 (በአንድ ሦስተኛ) በህጉ ከተመለከተዉ የቅጣት ጣሪያ ቅጣቱን ከፍ አድርጎ ሊያሳድግ ይችላል። ለአንድ አንድ የተለዩ ወንጀሎች ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች የተደነገጉ ሲሆን እነዚህም በጣም ከፍ ያለ ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን አስመልክቶ ህጉ አንድ አጠቃላይ የሆነ የዕድሜ ዝቅተኛ መሆን (tender age) ግምት ወስጥ ያስገባ ሲሆን ዕድሜን መሠረት በማድረግ ለቅጣት አወሳሰን የሚያግዝ የወጣት ጥፋተኞች ህግ ሥራ ላይ ያዉላል።

አንድ ተጠርጣሪ በበርካታ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ በሁሉም ጥፋቶች ቅጣት ይጣልበትና የቅጣቱ መጠን ግን በአንዱ ወንጀል ሊጣል ከሚችለዉ የጣሪያ ቅጣት ከ 1/3 (ከአንድ ሦስተኛ) እንዳይበልጥ ተደርጎ ማስተካከያ ይደረግለታል።

2.3.1 የቅጣት አወሳሰን ጋይድላየን በኒዘርላንድ

የተለያዩ ጥናቶች እንዳመላከቱት የቅጣት አወሳሰን ልዩነቶች በኒዘርላንድ ፍርድ ቤቶች ተከስተዉ ነበር። የዳኞችን ነፃነት በማይጋፋ መልኩ ነፃ (ፍቅድ) የሆነዉን የቅጣት ልዩነቶችን ለማጥበብ የተለያዩ መነሻ ሀሳቦች /ፕሮፖሳሎች/ ቀርበዉ ነበር። በጅምር አከባቢ ሦስት መነሻ ፕሮፖሳሎች ቀርበዉ ነበር። እነሱም፡

ሀ. የቅጣት ዉሳኔዎችን የሚወስን የተለየ ፍርድ ቤትን ማቋቋም፤

ለ. የቅጣት ዉሳኔዎችን በተመለከተ በኤሌክትሮኒክስ መረጃ መረብ የተደገፈ የመረጃ-ባንክ /electronic data-bank on sentencing/ ማቋቋም ወይም

ሐ. የቅጣት አወሳሰን ጋይድላየን /ቼክሊስት/ ሥራ ላይ ማዋል ነበር።

እነዚህ አማራጮች ሁሉም በቂ የሆነ መፍትሄ ባለማስገኘታቸዉ አንድ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጎ የኒዘርላንድ ዐቃቤ ህግ በዉሳኔ አሰጣጥ ወቅት በመጨረሻና ክርክር መቆሚያ ንግግሩ ለቅጣት የሚሆን መነሻ ሀሳብ እንዲያቀርብ መመሪያዉ በሁሉም የዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ነበር። ፍርድ ቤቶች በዚህ ዐቃቢያነ ህግ መመሪያ የማይገደዱ በመሆናቸዉ ከዐቃቤ ህጎች የሚቀርበዉን መነሻ የቅጣት ሀሳብ ፍርድ ቤቶች ዉድቅ የሚያደርጉበት ሁኔታም ተከስቶ ነበር። ይሁን እንጅ የዐቃቤ ህጉ የቅጣት መነሻ ሀሳብ ከፍርድ ቤቶች የቅጣት አወሳሰን ፖሊሲ ጋር የሚስማማ ሆኖ በሚገኝበት ወቅት የማጣጣሚያ ብቃት ያለዉ ሆኖ /harmonizing effect/ በመገኘቱ ፍርድ ቤቶች በተወሰነ መጠን ይቀበሉት ነበር። ይህ አጋጣሚ የሚከሰተዉ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ባለመሆኑ በመመሪያዉ አፈፃፀም ክፍተቶችና ልዩነቶች ተከስተዉ ከአንዱ ዐቃቤ ሌላዉ ዐቃቤ ህግ ዘንድ ልዩነቶች ተከስዋል።

እዚህ ደረጃ ላይ ከተደረሰ በኃላ በ 1970 አካባቢ ለጊዜዉ የሚሆን “የዐቃቤ ህጎች የቅጣት አወሳሰን መመሪያ” ወጥቶ መተግበር ተጀመረ። በመቀጠልም በ 1990 አከባቢ ሁሉአቀፍ የሆነ ሥራ ለመስራት ታስቦ ፕሮጀክት ተቀርፆ እስከ 1999 ድረስ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ በቅጣት አወሳሰን ያለዉን ልዩነት ለማስወገድ በቁጥር 35 የሚሆኑ አዳዲስ አገራዊ /ብሔራዊ/ የሆኑ የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች ወጥተዉ በሥራ ላይ ዉለዋል። የዚህ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ዓላማ በወጣዉ ብሔራዊ መመሪያ መሠረት ዐቃቤ ህግ ለፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳይ ተመሳሳይ የቅጣት መነሻ ሀሳብ /ጥያቄ/ እንዲያቀርቡ በማድረግ በፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳይ ልዩነት የሌለዉ ወጥነት ያለዉ ዉሳኔ እንዲሰጥ ማስቻል ነዉ።

2.3.2 የጋይድላየኑ ይዘት ወይም አወቃቀር

ጋይድላየኑ የተዋቀረዉ በዐቃቤ ህግ የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* ላይ ተንተርሶ ነዉ። አቀራረቡና ይዘቱ ለእያንዳንዱ የወንጀል ዓይነት የቅጣት አወሳሰን ነጥብ በመስጠት በመጨረሻም የተገኙ ነጥቦችን እንደየ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በመደመር ወይም በመቀነስ በመጨረሻም አጠቃላይ የነጥቡ *መጠን* ከታወቀ በኃላ ነጥቡን ወደ ቅጣት በመቀየር የቅጣት *መጠን* መወሰን ማለት ነዉ። የነጥብ አቀማመጡ በተመለከተ

ለምሳሌ፦

- ብስክሌት ስርቆት 10 ነጥቦች
- ቤት ሰብሮ ገብቶ *መሥረቅ* 60 ነጥቦች
- ሱቅ ላይ ስርቆት 4 ነጥቦች
- አካል ላይ ጉዳት ማድረስ 7 ነጥቦች
- በአደባባይ ኃይል በመጠቀም ማስገደድ 15 ነጥቦች
- የተከለከለ ዕፅ ማዘዋወር /ወደ አገር ዉስጥ ማስገባትም ሆነ ወደ ዉጭ አገር *መላክ*/ 30 ነጥቦች
- ፋብሪካ ሰብሮ በመግባት *መስረቅ* 42 ነጥቦች በማለት ይቀጥላል።

እንግዲህ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ እንደየምክንያቱ ነጥቡን ማሳደግም ሆነ *መቀነስ*ም የሚቻልበት *ሥርዓት* አለ ማለት ነዉ።

2.3.3.ነጥቦችን መጨመር ወይም መቀነስ

ለምሳሌ በአንድ በተፈፀመ ወንጀል የጦር *መሣሪያ* ተጠቅሞ ወይም አካላዊ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ነጥብ በተያዙ ነጥቦች ላይ ያስጨምራል። ለሁለተኛ ጊዜ ወንጀሉን የደገመዉ /በድጋሚ/ የፈፀመ ከሆነ የተያዘዉ ነጥብ በግማሽ እንዲጨምር ይደረጋል ደጋጋሚ /ከሁለት በላይ/ ወንጀል የደጋገመ ከሆነ ግን ነጥቦችን በእጥፍ ያሳድጋል።

በሌላ በኩል አንድ አንድ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ደግሞ ነጥቦች እንዲቀነሱ ይደረጋሉ። ለምሳሌ ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ ቀርቶ ጥፋተኛ ያሰኘዉ ከሆነ ከተያዘዉ ነጥብ ያስቀንሳል። እንደዚሁም ሌሎች ምክንያቶች ቅጣትን ለማስቀነስ የሚሆኑ ምክንያቶች አሉ ማለት ነዉ።

2.3.4 መቀየሪያ /ማስተካከያ/ Conversion Methods/ ዘዴዎች

ከላይ የተመለከቱት የቅጣት አደማመር ሂደቶች በመጨረሻ ላይ የቅጣቱን መጠን በማሳደግ/በመጨመር/ እጅግ ከፍ ሲያደርጉት በጣም ከባድ የሆነ ቅጣት ተከሳሽ ላይ እንድወሰን ሊያደርጉት ይችላሉ። ይህንን በጣም ከፍ ያለ የቅጣት *መጠን* አወሳሰን *መጠን*ን ለማስታረቅ የተለየ ዘዴ ተበጅቶለታል። ይህ ዘዴ ቀጥሎ ባለዉ *መ*ልኩ አጠቃላይ ደምር ዉጤቶችን ይቀያይራል።

- በሁሉም ጉዳዮች የመጀመሪያ 180 ነጥቦች እያንዳንዳቸዉ አንድ *ሙ*ሉ የቅጣት *መ*ወሰኛ ነጥብ ይያዛሉ፤

- ቀጥሎ ያሉት በ 181 ነጥብ እና በ 540 መካከል ያሉት ነጥቦች እያንዳንዳቸዉ 1/2 (ግማሽ) የቅጣት መወሰኛ ነጥብ ይይዛሉ፤
- በመቀጠል ከ 541 በላይ ያሉት ነጥቦች እያንዳንዳቸዉ ¼ (አንድ አራተኛ) ነጥብ ይይዛሉ፤
- እያንዳንዱ ነጥብ ደግሞ ወደ ተወሰነ ገንዘብ ሊቀየር የሚችልበት ወይም ደግሞ ወደ አንድ ቀን እስራት ወይም ደግሞ ወደ ሁለት ሰዓት የግዴታ ሥራ ሊለወጥ የሚችልበት ሥርዓት ተዘርግቷል፤
- አጠቃላይ የነጥቦቹ ድምር ከ 30 በታች በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ዐቃቤ ህግ ጉዳዩን ወደ ግልፅ ችሎች ከማቅረብ ይልቅ በራሱ ደረጃ በገንዘብ ወይም በግዴታ ሥራ እንዲቀጣ፤
- የነጥቦቹ ድምር ከ በ 30 እና በ 60 መካከል በሚሆኑበት ወቅት ዐቃቤ ህጉ ለፍርድ ቤት በግዴታ ሥራ ብቻ እንዲቀጣ ሀሳብ ማቅረብ የሚችልበት፤
- የነጥቦቹ ድምር ከ 60 እስከ 120 በላይ በሚሆንበት ወቅት ዐቃቤ ህግ ክስ ለማቅረብ የሚገደድ ሲሆን ከ 60 በላይ ለሆኑት የግዴታ ሥራ ቅጣትን ከ 120 በላይ ለሆኑት ግን የእስራት ቅጣት ጥያቄ ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት፤
- ዐቃቤ ህግ የቅጣት ሀሳብ በመመሪያዉ መሠረት ማቅረብን መተዉ እንደሚችልና ለዚህም ግልፅ ምክንያት ማቅረብ ማስቀመጥ እንዳለበት፣
- ነገር ግን ከአጠቃይ ፖሊሲዉ ሀሳብ አንድ ዐቃቤ ህግ የተለየ አቋም መያዝ የሚፈልግ ከሆነ ግን ከጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ጋር የዉይይት መድረክ ተከፍቶ ስምምነት መደረስ እንዳለበት ተቀምጧል።

ከዚህ ዉጭ የኒዜርላንድ ፍርድ ቤቶች በመረጃ መረብ ከቀድሞ ዉሳኔዎች መረጃ የሚያገኙበት በወንጀል ዓይነት፣ በወንጀል የቀድሞ ታሪክ እና በዕድሜ ሁኔታ የተደራጀ ሥርዓት አላቸዉ።

2.4. ፊንላንድ

የፊንላንድ ፍርድ ቤቶች አወቃቀር ልክ እንደ አገራችን በ 3 ደረጃ /እርከን/ ነዉ። አሰያየማቸዉ የታችኛዉ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመባል ይታወቃል። የታችኛዉ ፍርድ ቤት በራሱ ሁለት ዓይነት የተከፈለ ሲሆን እነሱም፡-

1. የህግ ባለሙያ በሆኑ በሦስት ዳኞች የሚያስችል የከተማ ፍርድ ቤት
2. አንድ የህግ ባለሙያ በሆነ ዳኛ እና ከ 5 እስከ 7 በሚደርሱ የህግ ባለሙያ ባልሆኑ (lay judges) ዳኞች የሚያስችል ተዘዋዋሪ ችሎት የሚያስኬድ ማለት ነዉ።

በዚህ በሁለተኛዉ ዓይነት ፍርድ ቤት ዉሳኔዎች የሚሰጡት የህግ ባለሙያ በሆነዉ ዳኛ ሲሆን ህግ ባለሙያ ያልሆኑት ቁጥራቸዉ 5 ወይም 7 ሊሆን የሚችሉት በሙሉ ድመፅ የሚስማሙ ከሆነ ግን ባለሙያ የሆነዉ ዳኛ የወሰነዉን ዉሳኔ ሊጥሉት ይችላሉ ማለት ነዉ።

ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በሦስት ዳኞች የሚያስችል ሲሆን ከታችኛዉ ፍርድ ቤት የሚመጡ የይግባኝ ጉዳዮችን ያያል። ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚያየዉ ጉዳይ ደግሞ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ተብሎ አቤቱታ ሲቀርብለትና ለወደፊት ሊከተሉት የሚገባ ማጣቀሻ ዉሳኔ (precedent) መወሰን አለበት ብሎ ሲያምን ነዉ። በዚህ ደረጃ 5 ዳኞች ተቀምጠዉ በፓናል ጉዳዩን ያዩታል ማለት ነዉ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዚህ ደረጃ የተለያዩ የቅጣት አማራጮችንና መጠንን በመወሰን ለቅጣት አወሳሰን የሚጠቅም የመመሪያ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል ማለት ነዉ። ይሁን እንጅ የቅጣት ደረጃዎችን በተመለከተ ሥራ ላይ ሊዉል የሚችል መመሪያ ለማዉጣት ዳተኛ ሆነዋል።

የፊንላድን የወንጀል ህግ ስንመለከት ዘርዘር ያሉ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችንና የወንጀል ህግ የሚገዛበትን ፍልስፊናዎችን ያትታል።

- ተመዛዛኝነት፣
- ተገማችነት እና
- እኩልነት

የቅጣት አወሳሰን ዋና ዋና መርሆዎች ናቸዉ። የተመዛዛኝነት መርሆ መሠረት የሚያደርገዉ የወንጀሉን ክብደት (seriousness of the crime) እና የቅጣቱ ጠንካራ መሆን (severity of the sanction) ነዉ።
የወንጀል ህጉ ጥፋተኛ በተሰኘ ተከሳሽ ላይ ሊወሰኑ የሚችሉ አምስት የቅጣት ዓይነቶችን በደረጃ ያስቀምጣል። እነሱም፦

1. ቅጣትን መተዉ/sentence waiver/
2. የገንዘብ መቀጮ/fine/
3. በሁኔታዎች ላይ የተወሰነ እስራት/ለወጣት ጥፋተኞች /conditional imprisonment /juvenile/
4. በሁኔዎች ላይ የተወሰነ እስራትና የገንዘብ መቀጮ እና /conditional imprisonment with fine/
5. በሁኔታዎች ያልተገደበ እስራት/ማኅበረሰብ አገልግሎት/unconditional imprisonment/community service/

በተጨማሪም የወንጀል ህጉ ዝቅተኛዉንና የጣሪያ ቅጣቱን በማስቀመጥ ከ - እስከ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበትን ክልል ይደነግጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቅጣት ሲወሰን ከግንዛቤ መግባት ያለባቸዉ ተያያዥ የሆኑ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ሁኔታዎች ተዘርዝረዋል። የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶቹ በሁለት የተከፈሉ ሲሆን፦

1 ኛ. በጣም ከባድ ያልሆነ ቅጣት

2 ኛ. ዝቅ ያለ ቅጣት በተወሰኑ የወንጀል ዓይነቶች ናቸዉ።

የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የተባሉት ተዘርዝረዉ ያላለቁ /open-ended/ ሲሆኑ ቅጣት ሲወሰን ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ካሉ መጨመር መጠቀም ይቻላል ማለት ነዉ። ነገር ግን የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ሁሉም የተዘረዘሩ በመሆናቸዉ ቅጣት የሚወስነዉ ዳኛ ሌላ ልጨምርበት (ሊያካትት) አይችልም። ፍርድ ቤቱ በበቂ ሁኔታ የሚያሳምን ምክንያት ካለዉ

ከዝቅተኛዉ የቅጣት ወሰን ወርዶ መወሰንም ይችላል። በጣም ከባድ በሆኑ ወንጀሎች ግን ያለቅድመሁኔታ እስራት የሚወሰን ሲሆን በሌሎች ጉዳዮች ግን የገንዘብ መቀጮ እና እስራት፣ በቅድመሁኔታ እና ያለቅደመሁኔታ እስራት፣ ያለቅድመሁኔታ እስራት ከማኅበረሰብ አገልግሎት ጋር ሊወሰን ይችላል።

የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ ተመሳሳይ የሆነ የቅጣት አወሳሰን ልማድ እንዲኖር ተገቢ ትኩረት መስጠት አለባቸዉ ይላል። ልክ እንደ ሌሎቹ አገሮች የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በዚህ ክፍል ዉስጥ ልዩ አሳማኝ ምክንያት ካልተገኘ በስተቀር ዳኛዉ በተመሳሳይ ጉዳይ ዘወትር ተደጋግመዉ የሚወሰኑ ዉሳኔዎችን (sentence that is imposed most frequently) ተከትሎ መወሰን አለበት ይላል። ይህ በተደጋጋሚ ተዘወትሮ የሚወሰን ዉሳኔ ደግሞ መደበኛ ቅጣት (Normal punishment) ይባላል። ከዚህ አንፃር የቅጣት አወሳሰኑ ሂደት የተዋቀረ እንዲሆንና ፍርድ ቤቶች ለዉሳኔያቸዉ መነሻ የሚሆን ጽኑ መሠረት ላይ እንዲቆሙ የቅጣት አወሳሰን ህግ (Sentencing Act) አዉጥታለች። ህጉ የሚያካትተዉ ፦-

- የቅጣት ናሙናዎችን(Models)
- መደበኛ ቅጣቶችመርሀ(Notion of normal punishment)

ይህንን ሞዴል ሥራ ላይ ለማዋል አንድ ዳኛ 3 ዓይነት መረጃዎችን ማግኘት አለበት። እነዚህም፦-

1. በተያዘዉ ጉዳይ ዓይነት ላይ በስፋት እየተወሰነ ያለ የቅጣት ዓይነት የሚያሳይ ስታቲስቲክስ
2. በዉሳኔዉ ዉስጥ ለጉዳዩ የተሰጠ ማብራሪያ
3. ቅጣት ሲወሰን የተጠቀሙት የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንየቶች።

የመጀመሪያ ሁለቱ መረጃዎች ከፍርድ ቤት ስታትስቲክስና ዓመታዊ ሪፖርት ዉስጥ የሚገኙ መረጃዎች ሲሆኑ 3ኛ መረጃ የሚገኘዉ በህንች ዉስጥ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔዎች እና በከፊል ደግሞ ከህግ ፍልስፍና ጽሁፎች ዉስጥ ይገኛል።

ይህ ሞዴል ዳኛዉ የቅጣት ዉሳኔን ከየት (ከስንት) መጀመር እንዳለበት መረጃ ይሰጣል። ሞዴሉ የዳኞችን ነፃነት ያለልከ የሚገድብ ሳይሆን ከአንድ አንድ ጉዳዮችና ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች በመነሳት ከሞዴሉ የተለየ ዉሳኔ እንደየጉዳዩ ዓይነት መወሰን የሚቻልበትን ይፈቅዳል ማለት ነዉ።

2.5. ***ጀርመን***

ጀርመን የፌዴራል ሥርዓተ መንግስት የምትከተል ስትሆን 16 ክልሎች አሏት። የፌዴራል ወንጀል ህጉና የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህጉ በተመሳሳይ በክልሎችም ይፈፀማል። የቅጣት አወሳሰን ልዩነቶች ከክልል ክልል እንደሚታይ ጥናቶች ይጠቁማሉ[7]። የጀርመኑ ወንጀል ህግ በጠቅላላ ክፍሉ አጠቃላይ ድንጋጌዎችን ከመነሻዉ እስከ ጣሪያዉ ሰፋፊ የቅጣት ልዩነቶችን የያዙ ድንጋጌዎችና በሌሎች የህጉ ክፍሎች ደግሞ ለእያንዳንዱ ወንጀል የቅጣት መጠንን ይደነግጋል። የቅጣት አወሳሰን ሰፊ ሥልጣን በአብዛኛዉ

[7] Sentencing in Germany At http://wings.buffalo.edu/law/bclc/bclrarticles/7/nestler.pdf

ለዳኞች የተተወ ሲሆን ዝቅተኛዉ የቅጣት መጠን አንድ ወር ሲሆን ከ 6 ወር በታች የሚያሳስር ወንጀል ልዩ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር እስራቱ አይፈፀምም ይታገዳል። ነገር ግን ትልቅ አደጋ የሚያመጣ ከሆነ ብቻ በእስራት ይቀጣል። ከአንድ ዓመት በታች የሚያሳስርን ወንጀል እንዳይታገድ የሚፈለግ ከሆነ ፍርድ ቤቶች በቂ አሳማኝ ማብራሪያ መስጠት አለባቸዉ። የገንዘብ ቅጣት የጥፋተኛዉን ገቢ መሠረት ያደረገ በጥፋተኛዉ የቀን ገቢ ልክ የሚሰላ ሆኖ ከ 360 ቀናት ገቢ አይበልጥም።

እንደ ኒዘርላድ የጀርመኑ አቃቤ ህግ በቅጣት አወሳሰን ላይ ትልቅ ሚና የመጫወት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ቀላል የሆኑ ወንጀሎች ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ ተበዳይን እንዲክስ ወይም የወሰደዉ እንዲመልስ፣ ወይም ለአንድ በጎ አድራጎት ድርጅት ክፍያ እንዲፈፅም በማድረግ ክሱን ሊያነሳ ይችላል። ከጥፋተኛነት ዉሳኔ በኃላ ዐቃቤ ህጉ ጥፋተኛዉ መቀጣት ያለበትን ቅጣት ዓይነት ጭምር በፅሁፍ አስተያየት ያቀርባል።

በዚህ ዙሪያ አስተያየት ሰጪዎች በወንጀል ህጉ የተቀመጠዉ የወንጀል ህጉ መርሆዎች በዳኞች የዕለት ተዕለት ዉሳኔ ተግባራዊ እየሆኑ አይደሉም ይላሉ። የቅጣት አወሳሰን ጋይድላይን የሌለ በመሆኑ የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በመርህ ላይ የተመሰረተ ለእያንዳንዱ ጥፋተኛ እንደጥፋቱ መጠንና ወንጀልን መከላከል መሠረት የሚያደርግ ግን ለሥራ በሚያመቻቸዉ መልክ የየዕለት ከስተቶችን፣ የወንጀሉን ሁኔታ፣ ተበዳይ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ወይም ጥፋተኛዉ ያስከተለዉ ጉዳትና የቀድሞ ሪኮረዱ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነዉ ይላሉ።

የጀርመኑ የወንጀል ህግ አፈፃፀም አሁን በኢትዮጵያ የሚፈፀመዉ ዓይነት በመሆኑ ለጋይድላየን አዘገጃጀት ትምህርት የሚቀሰም ልምድን ሊያደብርልን የሚችል ነገር የለዉም ማለት ይቻላል።

2.6. <u>ፈረንሳይ</u>

ከፈረንሳይ የቅጣት አወሳሰን ለጋይድላየን ዝግጅት የሚሆን ተሞክሮ የለም። የወንጀል ህጋቸዉ በአራት መፃህፍት የተከፋፈለ ነዉ። የወንጀል ዓይነቶችም በሦስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ (ወንጀል፣ ቀላል ወንጀል እና መተላለፍ) ሲሆን ቅጣታቸዉም እንደ ክብደታቸዉ ከገንዘብ መቀጮ እስከ እድሜ ልክ እስራት የሚደርሱ ናቸዉ።

በፈረንሳይ ፍርድ ቤቶቹ በሦስት ደረጃዎች የተዋቀሩ ናቸዉ።

1. የፖሊስ ፍርድ ቤት (police court)፡- በአንድ ዳኛ የሚያስችል ሲሆን በገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጡትን ወይም እስራትን የማያስከትሉ ቢያስከትሉ እንኳ ከአንድ ዓመት የማይዘሉትን ያያሉ።
2. የወንጀል ፍርድ ቤት፡- ከበድ ያሉትን እስከ 10 ዓመታት ሊያሳስሩ የሚችሉትን ጉዳዮች በ 3 ዳኞች የሚያይ ሲሆን አልፎ አልፎ ግን በአንድ ዳኛም ሊያስችሉ ይችላሉ።

3. የበላይ ፍርድ ቤት (Court of assizes)፦ ይህ ፍርድ ቤት በጣም ከፍ ያሉ ከ 10 ዓመት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉትን ወንጀሎችን በ 3 ዳኞች ፓናል እና በ 9 ከህዝቡ በሚወጡ ተች ዳኞች የሚያይ ፍርድ ቤት ነዉ።
4. ሰበር ሰሚ (cassation):- በፈረንሳይ የዳኝነት ሥርዓት ዉስጥ የሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት የመጨረሻዉ ትልቁ ፍርድ ቤት ሲሆን ህግን ሳይከተሉ የተወሰኑትን ዉሳኔዎች በይግባኝ የሚያይ ፍርድ ቤት ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት ወጥነት የጎደለዉን ፍርድ ሙሉ በሙሉ ወይም የማያስፈልግ ነዉ የሚለዉን ክፍል የመሻር ሥልጣን አለዉ።

ክፍል ሶስት

በኢትዮጵያ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የቀረቡ አማራጮች

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አቀራረጽና ስርአት የኮንቲኔንታል የህግ ስርአት እንደሚከተሉት ጀርመንና ፈረንሳይ ነው። እነዚህ የኮንቲኔንታል የህግ ስርአት የሚከተሉ አገራት በህጉ ላይ ልክ በእኛ አገር ካለው አጠቃላይ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ያለፈ ዝርዝር የቅጣት አወሳሰንን የሚመለከት መመሪያ ወይም ማንዋል የላቸውም። ስለሆነም በቅጣት አወሳሰን አሁን ያለውን ችግር ለማስወገድ ተመሳሳይ የህግ ስርአት ካላቸው አገራት ልንወስደው የምንችለው ልምድ የለም ማለት ይቻላል።

ከዚህ በላይ በቀረበው ክፍል እንደተመለከትነው፣ የደረጀና የዳበረ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ያላቸው የኮመንሎው የህግ ስርአት የሚከተሉት አገሮች በተለይም እንግሊዝና አሜሪካ ናቸው። የእነዚህ አገሮች የቅጣት አወሳሰን ጋይድላይን በቅጣት አወሳሰን ወጥነትን፣ ተመጣጣኝነትን፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማምጣት የሚያስችል እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ስለሆነም የቅጣት ጋይድላይን ወይም ማንዋል ልናዘጋጅ የሚያስፈልገን ከሆነ ትምህርት ልንወስድ የምንችለው ከእነዚህ የኮመን ሎው አገሮች ነው።

እነዚህን ልምዶችና የኢትዮጵያን የወንጀል ህግ አወቃቀርና ስርአት ጋር ሊጣጣም በሚችል መልኩ የቅጣት አወሳሰንን በሚመለከት ጥናት ባደረጉ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሁለት አይነት ሞዴሎች ቀርበዋል። ከእነዚህም አንደኛው ‹በቀመር› ወይም ‹ፎርሙላ› ላይ የተመሰረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ› የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹የወንጀል ደረጃዎችን እንደክብደታቸው ደረጃ በማውጣት ላይ የተመሰረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ከዚህ በመቀጠል ሁለቱ ሞዴሎች በዝርዝር ቀርበዋል። ሁለቱም ሞዴሎች አላማና ያስገኛሉ ተብሎ የሚጠበቀው ውጤት ግን ተመሳሳይ ነው።

3.1. *የሚዘጋጀው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አላማና ውጤት*

የወንጀል ህጋችን አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 4 የቅጣት አወሣሰን *መመሪያ* / ማንዋል / አላማው ምን መሆን እንዳለበት ያመለክታል። ድንጋጌው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አመሣሰንን ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የቅጣት አወሣሰን *መመሪያ* (manual) እንደሚያወጣ ይደነግጋል።

በመሆኑም ህግ አውጭው የቅጣት ማንዋል በሀገራችን እንዲኖር የፈለገበት ዓላማ የፍ/ቤቶችን የቅጣት አወሣሰንን ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ ነው ለማለት ይቻላል ። የሚቀረፀውም የቅጣት ማንዋል በዚሁ እሣቤ መነሻነት ነው።

የቅጣት አወሣሰንን ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት የማረጋገጥ ጠቅላላ ዓላማ እንደተጠበቀ ሆኖ *መመሪያው* ሊያስገኝ የሚገቡት ውጤቶች የሚከተሉትን ያካትታል።

3.1.1. አንድ ወጥነት ፣ **(consistency)**

ቅጣትን በአንድ አይነት *መልኩ* መወሰን የማይቻል እና የማይፈለግ ቢሆንም አንድ ወጥ አወሣሰን እንዲኖር ግን ያስፈልጋል ። ለተመሣሣይ የድርጊት አፈጻጸም እና የግል ሁኔታዎች ሁሉ *ተመሣሣይ* ከሆኑ የተለያዩ ሰዎች ለተመሣሣይ ወንጀል *ተመሣሣይ* ቅጣት እንዲጣልባቸው የቅጣት ማንዋሉ ያስችላል።

3.1.2. ተመዛዛኝነት **(proportionality)**

ማንዋሉ የሚወሰነዉ ቅጣት ተከሣሹ በግሉ ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል ፣ ካለፈ የህይወት ታሪኩ ፣ ከአፈጻጸሙ ወዘተ ----------ጋር የተመዛዘነ እንዲሆን ይረዳል ።

3.1.3. ተገማችነት ፣ **(predictability)**

ቅጣት ተገማች እንዲሆን ያደርጋል።

3.1.4. ግልጽነት **(transparency)**

በፍ/ቤቶች የሚወሰኑ ቅጣቶች ግልጽነት የሚጐድላቸው ስለመሆኑ ከተሰበሰበው ዳታ መረዳት ይቻላል ። ከተጠቀሱ የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ያልተነሣ ውሣኔ ከመስጠት ጀምሮ ምንም አይነት ምክንያት እንኳ ሣይሰጥ ቅጣት ቀልሎ እና ከብዶ መወሰኑም የተለመደ ነው። የቅጣት ማንዋሉ ከዚህ አንጻር የጎደለውን ግልጽነትን በማስፈን ረገድ ጠቀሜታ አለው።

3.1.5. ተጠያቂነትን ያሰፍናል /demand for accountability/

የአሰራር ግልጽነት መኖር እና ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ማድረግ ሁሉ የማንዋሉ ዓላማ ነው። ምክንያታዊ ያልሆነ ዉሳኔ ተጠያቂነትን እንዲያስከትል ለማድረግ ማንዋሉ ያስችላል ።

3.1.6. የግለሰቦችን መብት ማስከበር እና የፍ/ቤቶችን ሰፊ ፍቀድ ስልጣን መቆጣጠር (concern about individual right and the control of discretion)

ማንዋሉ ግለሰቦችን ካላስፈላጊ ከባድ ቅጣት እና የመብት ጥሰት የመታደግ ውጤት ሲኖረው የፍ/ቤቶችን ሰፊ ስልጣን ለተፈለገው አላማ መጠቀም በሚያስችል መልኩ መከፋፈል እና ማጥበብ ያስችላል ።

3.1.7. ወንጀልን መከላከል (crime control)

ቅጣት ከተገቢው በታች ቀልሎ ሲወሰን ህ/ሰቡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ላይ እምነት እንዲያጣ ከማድረጉም ሌላ አደገኛ ባህሪ ያላቸው ሊታረሙ የሚገባ እጥፊዎች ወደ ህብረተሰቡ ሣይታረሙ እንዲቀላቀሉ እና ህ/ሰቡ በሌላ ወንጀል እንዲጋለጥ ያደርጋል ።

3.2. ‹በቀመር› ወይም ‹ፎርሙላ› ላይ የተመሰረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ

በዚህ ሞዴል መሰረት የቅጣት አወሳሰን እንዲሰራ ሀሳብ የቀረበባቸው አስገድዶ መድፈር፣ ተራ የሆነ የሰው ግድያን የሚመለከት ሲሆን፣ ዋናው የሞዴሉ መገለጫ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።[8]

3.2.1. የቅጣት አወሳሰን ማንዋሉ ቀመር ቀረፃ እና ማንዋሉ የተመሰረተባቸዉ መሰረታዊ መርሆች[9]

በዚህ ፅሁፍ መግቢያ እንደተመለከተዉ በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አቀራረፅ እያንዳንዱ ወንጀል ሊያስከትል የሚችለው ቅጣት የተመለከተ ሲሆን የወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍልም የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ጠቅላላ እና ልዩ ምክንያቶችን ይዘረዝራል። በተጨማሪም ቅጣትን ለማቅለል ወይም ለማክበድ የሚያስችል በህግ በግልጽ ያልተፃፈ ሌላ በቂ ምክንያት ሲገኝና ይህንኑ ፍ/ቤቱ የሚቀበለው ሲሆን የተቀበለበትን ምክንያት ገልፆ በመፃፍ ሊገለገልበት እንደሚችል ሁሉ ተመልክቷል።[10]

[8] ስለዝርዝሩ በይበልጥ ለመረዳት በሁለቱ የወንጀል ድንጋጌዎች ላይ የቀረቡትን ጥናቶች ይመልከቱ፣

[9] በዚህ ክፍል (3.2) ውስጥ ያለው ጽሁፍ ሙሉ በሙሉ አቶ ተፈሪ ካዘጋጁት የቅጣት አወሳሰን ጥናት ላይ የተወሰደ ነው።

[10] የወንጀል ህግ አንቀፅ 82፣83፣84፣85፣86፣180

የወንጀል ህጉ በዚህ መልኩ የቅጣት አወሳሰንን አስመልክቶ ከተደራጀ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲያወጣ የታሰበው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ /Manual/ ምን መልክ ሊኖረው ይገባል የሚለውን ጥያቄ እዚህም ላይ ማንሳቱ ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን።

ከፍ ብሎ እንደተገለፀዉ ብዙዎቹ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አውጥተው የተገበሩ ምዕራባዊያን ሃገሮች የእኛን የወንጀል ህግ የመሰለ ስለ ቅጣት አወሳሰን ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ ህግ የላቸውም። ተበታትነው የሚገኙ ወንጀል ጠቀስ ህጐች ያሏቸው ሲሆን ከፊሎችም የእያንዳንዱን ወንጀል መቋቋሚያዎች ሣይቀር ከፍርድ ቤት ውሣኔዎች ያገኙም አሉ። በእነዚህ ሃገራት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የሚኖረው ይዘት ጥልቅ ሲሆን ኮዲፋይ የተደረገ የወንጀል ህግ ሊይዝ የሚገባው ቅርጽና ይዘት ኖሮት ሲወጣ ይስተዋላል። እነዚህ ሀገራት የቅጣት አወሳሰንን አንድወጥ የማድረጉን አስፈላጊነት ቢቀበሉም የዳኞችን መንሸራሸሪያ በእጅጉ መገደቡን ግን አይቀበሉም። ለምሳሌ ይሆን ዘንድ በእንግሊዝና በአሜሪካ የነበረዉንና ያለዉን ሁኔታ መመልከት ይቻላል[11]።

[11] As far as the UK sentencing policy is concerned, it was born as a result of the Halliday report and the subsequent White Paper named *Justice for All* which was presented in the British Parliament. The main aim of the sentencing frame work as explained by the White Paper is deterrence and protection of society above all others. In order to aid the judge a *Pre-sentence report* is prepared by a parole officer which contains "a front sheet, offence analysis, offender's assessment, risk assessment and a conclusion". As far as sentencing Guidelines are concerned, paragraph 5.14 explicitly states as follows: *"We need to have a consistent set of guidelines that cover all offences and should be applied whenever a sentence is passed. We must work to eradicate the wide disparity in sentencing for the same types of offences and the public's mistrust of the system that comes partly from this inconsistent sentencing."* The answer of the Halliday report to this problem is, *"For a new framework, an Act of Parliament should set out the general principles, specify the newly designed sentences, provide for review hearings, prescribe enforcement procedures and require guidelines to be drawn up. The Act should take the form of a* ***Penal Code****, which would be kept continuously available in up to date form."* This led to the establishment of the Sentencing Guidelines Council headed by the Lord Chief Justice. Also a whole new set of punishments with reformatory purpose have been introduced. In short, the main aim of the policy in

በአንፃሩ ከላይ እንደገለጽነው የእኛ ሃገር የወንጀል ህግ እያንዳንዱን የወንጀል ጥፋት እስከ ቅጣቱ የሚደነግግ ብቻ ሣይሆን ለቅጣት አወሳሰን የሚረዱ ዝርዝር አናቅጽ ይዞ የታወጀ በመሆኑ ሊወጣ የሚገባው የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* ከምዕራባዊያኑ የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* የተለየ እንዲሆን ይጠበቃል። ወንጀልን በየመልኩ *መመደብ* እና ቅጣቱን ከ - እስከ ብሎ *መወሰን* በወንጀል ህጉ አስቀድሞ ተሰርቷል።

---

protection of the public and rehabilitation. As far as discretion goes, there has not been any specific restriction except for ensuring that the judge has complete knowledge of all the details of the convict before passing the sentence. The aim, as can be seen, is to put forth the case in the best possible way and thereby ensure that no stone is left unturned.

In the US system, The Guidelines are the product of the United States Sentencing Commission and are part of an overall federal sentencing reform package that took effect in the mid-1980s. In the aftermath of *US v.Booker*, the Guidelines are discretionary, meaning that judges may consider them but are not required to adhere to their standards in sentencing decisions. That being said, federal judges almost invariably use the Guidelines at least as a starting point when sentencing criminal defendants. Any sentence outside of the scope of the guidelines requires a written explanation, by the judge, as to the reason for the discretion. The Guidelines determine sentences based primarily on two factors: (1) the conduct associated with the offence and (2) the defendant's criminal history. The statutory mission as stated in the 2005 Federal Sentencing Guideline Manual is “...deterring crime, incapacitating the offender, providing just punishment, and rehabilitating the offender. It delegates to the Commission broad authority to review and rationalize the federal sentencing process.” Once again discretion though guided is not completely removed in the case of US also.

በዚህ ምክንያት ማንዋሉ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት በማስቀመጥ እና እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ሊወክል የሚችለዉን የቅጣት ግዜ በማመልከት ሊወሰን ይገባል።

ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው የሚጠበቀው በተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛ የተሰኙ እና ተመሳሳይ የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያቶች የቀረቡባቸው እና የግል ሁኔታዎቻቸው ተመሳሳይ የሆኑ አጥፊዎች ትክክለኛ የሚባል ተመሳሳይ ቅጣት እንዲጣልባቸው ማስቻል እና በውጤቱም የቅጣት አወሳሰንን አንድወጥነት እና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው።

3.2.1.1. <u>የማንዋሉ ቀመር ቀረፃ</u>

ለተያዘው የቅጣት አወሣሰን ማንዋል ተገቢ የሆነና በቀላሉ ሊተገበር የሚችል በአጠቃላይም ለሚወሰኑ ቅጣቶች ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት የሚረዳ እና የወንጀል ህጋችን የቅጣት አወሣሰን ድንጋጌዎች ተጠቃለው ሊተገበሩበት ይችላሉ ተብሎ የታሰበዉ የቅጣት አወሣሰን ቀመር ተከታዩን ሂሣባዊ ስሌት የተከተለ ነው ።

<u>ይኸውም</u>

$$Y = a + n_1 x_1 - n_2 x_2$$

ይህ አጠቃላይ የስሌት ቀመር ሲሆን ፊደላቱ የሚወክሉት

Y - የሚወሰነው ቅጣት

a - መነሻ ቅጣት

n_1 , n_2 - የቅጣት ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያት/ቶች <u>ብዛት</u>

x_1 - ቅጣትን የሚያከብድ ጠቅላላ ምክንያት **(አንቀፅ 84)**

- ፍርድ ቤቱ የሚቀበው ሌላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት **(አንቀፅ 86)**

x_2 - ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት **(አንቀፅ 82)**

- ፍ/ቤቱ የሚቀበለው ሌላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት **(አንቀፅ 86)**

3.2.1.2. የቅጣት አወሳሰን ማንዋሉ የተመሰረተባቸዉ መሰረታዊ መርሆች

U¯U ”£” ¾¨”ËM lÑ< Ç™‹ up×ƒ ›¨dc” [ÑÉ ÁKv†¨<” Ÿõ}— ¾J’ Lò’ት ¾ሚ ÖlU u=J”U uሌL uŸ<M lÑ< ¾p×ƒ ›¨dc”” u}SKŸ} K Á”Ç”Æ ¾¨”ËM ¯Ã’ƒ cò ¾J’ ¾p×ƒ S¨c— ¡MM uTekSØ KÇ™‹ Ÿõ}— ¾J’ ፍቅድ eM×” ¾cÖ uSJ’< ŸÇ— Ç— ”Ç=G<U Ÿ‹KAƒ ‹KAƒ ¾T>cÖ< p×„‹ ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ ሲለያዩ ይስተዋላል። ¾p×ƒ ›¨dሰ” SS]Á T²ÒËƒ በፍርድ ቤቶች የሚታየውን ይህን cò ¾J’ ¾p×ƒ ›¨dc” M¿’ƒ u ÏÑ< uSk’e p×„‹ õèU ›”ድ ¯Ã’ƒ vÃJ፡U U¡”Á © uJ’ Å[Ë }k^^u= “ }ÑT‹ ”ዲJ’< KTÉ[Ó Áe‹ላ M።

¾p×ƒ ›¨dc” SS]Á KT²ÒËƒ ÅÓV uSËS]Á K=Ÿ“¨” ¾T>Ñv¨< ’Ñ` õ/u?„‹ p×ƒ” uT>¨e፡<uƒ ¨pƒ K=Ÿ}LD†¨< ¾T>Ñu<ƒ” S`J‹ ´`´` uJ’ G<’@ TekSØ ’¬:: uSJ’<U ለያዝነዉ ቀመር ትግበራ ይረዳ ዘንድ ¾p×ƒ ›¨dc” S`J‹ በዚህ ክፍል ተዘርዝረዋል።

በአጠቃላይ በ p×ƒ ›¨dc” ማንዋሉ }ðéT> K=J’< ¾T>Ñv†¨< S`J‹ ¾T>Ÿ}K<ƒ “†¨።

1) ቅጣት መነሻ /a/

በህግ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ ምክንያት ከሌለ ቅጣቱ ምን ሊሆን ይገባል ? በሌላ አነጋገር የቅጣቱ መነሻ ምን መሆን አለበት? ለሚለው ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ ከህጉ አይገኝም ። ነገር ግን በወንጀል ህጉ አንቀፅ 178 እንደተመለከተዉ ስለቅጣት አወሳሰን የተደነገጉት ጠቅላላ መርሆች /አንቀፅ 88/ እንደተጠበቁ ሆነዉ በተጨማሪ ቅጣቱን ለማቅለል ወይም ለማክበድ ህጉ በፈቀደ ወይም ግዴታ ባደረገ ግዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ ከአንቀፅ 179-189 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል እንደሚወሰን የተደነገገ በመሆኑ ቅጣቱ ከመክበዱ ወይም ከመቅለሉ በፊት በወንጀል ህግ አንቀፅ 88/2/ ስር የተደነገጉትን ጠቅላላ መርሆች በመከተል መነሻ ቅጣት ሊወሰን ይገባል።

ይሁንና መነሻ ቅጣቱን መወሰን ሙሉ በሙሉ ለፍርድ ቤቶች ከተተወ ወይም እጅግ ሰፊ መንሸራሸሪያ ከተቀመጠ የሚፈለገዉን ምክንያታዊ ያልሆነ መለያየት ማስቀረት አይቻልም። በሌላ በኩል መነሻ ቅጣቱ አንድ አስቀድሞ የተወሰነ የቅጣት ግዜ /አንድ አሀዝ/ ብቻ ከሆነ ቅጣት ግለሰባዊ እንዳይሆን ያደርጋል። በበቂ ሁኔታ ቅጣት ግለሰባዊ ካልሆነ ደግሞ “ትክክለኛ” አይባልም።

በመሆኑም የወንጀል ህጉን አሳቤዎች የተከተለ እና በሌሎች ሀገሮች የቅጣት ማንዋል እንደሚሆነው ሁሉ ፍ/ቤቶች ተቀብለውት እየተገበሩት ያለውን ልምድ መሰረት ያደረገ፤ እንዲሁም ለዳኞች በቂ መንሸራሸሪያ የሚተዉ መነሻ ቅጣት

እንዲኖር ይጠበቃል። እነዚህን መመዘኛዎች ያሟላል ተብሎ የተገመተዉ መነሻ ቅጣት በተከታዩ ስሌት መሰረት ይሰላል። ይኸዉም፦

- <u>የመነሻ ቅጣቱ መጀመሪያ</u> - ለአንቀጹ በወ/መ/ህ/ቁ 179 መሰረት ቢቀል መነሻ የሚሆነዉ ቅጣት ሲደመር የአንቀጹ ጣራ ቅጣት ሲካፈል ለሁለት ሲሆን
- <u>የመነሻ ቅጣቱ መድረሻ</u> -የአንቀጹ መነሻ ሲደመር ጣራ ቅጣቱ ሲካፈል ለሁለት ነዉ።

<u>ለምሳሌ</u> - በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀፅ 5 መሰረት ለሽብርተኝነት ድጋፍ መስጠት ከ 10-15 አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል። በመሆኑም የመነሻ ቅጣቱ_መጀመሪያ የሚሆነዉ በወ/መ/ህ/ቁ 179/ሐ/ መሰረት 1 አመት ሲደመር ጣራ ቅጣቱ 15 አመት ሲካፈል ለሁለት ይሆናል 8 አመት። የመነሻ ቅጣቱ መድረሻ ደግሞ 10 ሲደመር 15 ሲካፈል ለሁለት ይሆናል 12.5 አመት። በመሆኑም መነሻ ቅጣቱ ማለትም "a" ከ 8-12.5 አመት ሲሆን ዳኞች የነገሩን ሁኔታ ግምት ዉስጥ አስገብተዉ/የወ/መ/ህ/ቁ.88(2)/ ከዚህ ከልል ሳይወጡ የመነሻ ቅጣቱን ይወስናሉ።

2) õ/u?„‹ መነሻ ቅጣት መወሰን ÁKv†¨< ¾p×ƒ TpKÁ □“ T¡uÍ U¡”ያ„‹” ŸSS[S^†¬ uòƒ SJ” Ã•`u□M:: K¨”ËK< ¾ተkÖSÖ¨< kLM □Y^ƒ ŸJ’ }SXXÃ eK?ƒ SŸ}M ÁeðMÒM[12]:: ለማንዋሉ ስሌት ሲባል የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ጣራ በ 30 አመት ይወከላል። እንዲሁም የሞት ቅጣት የሚወሰን/በፍርድ ቤቱ የተመረጠ/ ሲሆን ይህን ስሌት መከተል አያስፈልግም።

3) õ/u?~ U”U ¯Ã’ƒ ¾p×ƒ TpKÁ“ T¡uÍ ምክንያት ያ LÑ– □”ÅJ’ ŸLÃ u}Ökc¨< eK?ƒ Sc[ƒ ከ}Ñ–¨< ¾S’h p×ƒ ክልል ሳይወጣ S¨c” Ã•`u□M::

4)- u¨”ËM IÑ< ›”kî 84 Y` የ}²[²ሩƒ ÖpLL ¾p×ƒ T¡uÍ U¡”Á„‹ u}Ñ–< Ñ>²? p×ቱ u}^lØ` 1 SW[ƒ }cM„ ŸT>Ñ–¨< ¾p×ƒ S’h LÃ U” ÁIM ŸwÊ K=¨c” □’ÅT>Ñv ¾T>ÁXÃ G<’@□” SõÖ` ያስፈልጋል:: በመሆኑም □Á”Ç”Æ ÖpLL ¾p×ƒ T¡uÍ U¡”Áት <u>u□Ÿ<M</u> p×ƒ” □’Ç=ÁŸwድ ተደርጓል:: u²=IU Sc[ƒ u›”kî 84 Y` ØpM uJ’ SMŸ< Ÿ}²[²\ƒ U¡ንÁ„‹ Sካ ŸM ›”Æ u}Ñ– Ñ>²? u}^ lØ` 1 ስK?ƒ Sc[ƒ Ÿ}Ñ–¨< ¾S’h

[12] ምንም እንኳ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ በቀላል እስራት የሚያስቀጣ ድንጋጌ ባይኖረዉም

p×ƒ SÖ” ላይ 1®% ÁIM p×~ ŸwÊ □”Ç=¨c” ይደረጋል።[13] ከአንድ በላይ ምክንያቶች ሲኖሩ በብዛታቸዉ ልክ ይሰላል። /X_1= a X 10%/

5) u¨”ËM IÑ< ›”kî 86 Sc[ƒ õ/u?~ ¾T>kuL†¨< ¾p×ƒ T ክ uÍ U¡”Á„‹ u}Ñ–< Ñ>²? U u}^ lØ` 4 Sc[ƒ □”Ç=ðìU ይደረጋል።[14] /X_1= a X 10%/

6) u¨”ËM IÑ< ›”kî 82 Y` ¾}²[²\ት ÖpLL ¾p×ƒ TpKÁ U¡”Á„‹ u}Ñ–< Ñ>²? □ያ”Ç”ዳቸዉ ¾p×ƒ TpKÁ ዎች u□Ÿ<M SÖ” p×ƒ □”Ç=ÁnMK< ተደርጓል። u²=IU Sc[ƒ u›”kî 82 Y` uØpM G<’@□ Ÿ}kSÖ<ƒ U¡”Á„‹ S ካ ŸM ›”Æ u}Ñ– Ñ>²? u}^ lØ` 1 eK?ƒ Sc[ƒ ከ}Ñ–¨< ¾S’h ¾p×ƒ SÖ” ላይ 1®% ÁIM p×~ kKA □”Ç=¨c” TÉ[Ó:: ከአንድ በላይ ምክንያቶች ሲኖሩ በብዛታቸዉ ልክ ይሰላል። /X_2= a X 10%/

7) u¨”ËM IÑ< ›”kî 86 Sc[ƒ õ/u?~ ¾T>kuL†¬ K?KA‹ ¾p×ƒ TpKÁ U¡”Á„‹ u}Ñ–< Ñ>²?U K□Á”Ç”Æ U¡”Áƒ u}^ lØ` 6 u}kSÖ ዉ Sc[ƒ □”Ç=ðìU ይደረጋል[15]:: /X_2= a X 10%/

8) u¨”ËM IÑ< ›”kî 85 Sc[ƒ õ/u?~ M¿ ¾p×ƒ T¡uÍ U¡”Á„‹ /የወንጀሎች መደራረብ እና መደጋገም/ S•ሩ<” c=Á[ÒÓØ uIÑ< Ÿ›”kî 184-188 É[e ¾}Å’ÑÑ<ƒ” Sc[ƒ uTÉ[Ó p×ƒ” ›ክ wÊ S¨c” ይኖርበታል።ይህን ሁኔታ ከመደበኛው መለየት የማንዋሉን ውስብስብ መሆን ያቀለዋል ለአፈጻጸሙም ቀና መንገድ ይፈጥራል። በመሆኑም የወንጀሎች መደራረብ እና መደጋገም ሲኖር በቅድሚያ ለነጠላዉ ወንጀል በቀመሩ መሰረት ወስኖ ቀጥሎ ህጉን ተከትሎ ማክበድ /184-188/ ይጠበቃል።

9) ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች ሲኖሩ ወይም õ/u?~ uScK¨< p×ƒ ¾T>ÁkMuƒ G<’@□ uT>ÁÒØUuƒ ¨pƒ /የ¨”ËM IÑ< ›”kî 83¯180/ õ/u?~ ÃI” T ንዋል መከተል ›ÃÖupuƒU:: ይህ ሁኔታ በማንዋሉ የሚስተናገደው በልዩ ሁኔታነት ነው ። ምክንያቱም ፍርድቤቱ በመሰለው ቅጣቱን ለማቅለል የተፈለገበት ዓላማ እና ዉጤቱ በማንዋሉ ሊገደብ ስለማይችል ነዉ።

[13] መቶኛውን በተመለከተ ለምሳሌ አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ ለተሰራው የቅጣት አወሳሰን የተለየ መቶኛ ያስቀምጣል።
[14] የወንጀል ህጉ ›”kî 84 እና 86 በተመሳሳይ ወደ 183 ስለሚመሩ እኩል ዋጋ እንዲይዙ ተደርጓል
[15]የወንጀል ህጉ ›”kî 82 እና 86 በተመሳሳይ ወደ 179 ስለሚመሩ እኩል ዋጋ እንዲይዙ ተደርጓል

10) Kጠpላላ ቅ×ƒ TpKÁ እ“ T¡uÍ ምክንያቶች እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ለሚቀበላቸዉ TpKÁ እ“ T¡uÍ ምክንያቶች □Ÿ<M ዋጋ uSeÖƒ u□Ÿ<M □”Ç=□¿ ¾}Å[Ñ u=J”U õ/u?~ □”Å’Ñ\ G<’@□ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል አንዱ ወይም ከአንድ በላይ u□Ÿ<M ¾TÁÃuƒ G<’@□ c=ðÖ` ÃI”’< u¨<X’@¨< LÃ Ÿ’U¡”Á~ uÓMî uTeð` uU¡”Á„‡ S ካ ŸM ለ TuLKØ“ በተለየ ፕርሰንት uTpKM ወይም uT¡uÉ ¨<X’@ K=cØ Ã‹LM[16]:: በዚህ መልኩ ፍርድ ቤቱ በቂ ምክንያት በመስጠት በማንዋሉ ሳይታጠር ዉሳኔ እንዲሰጥ መፈቀዱ ማንዋሉን የተሟላ ያደርገዋል። በተከታታይ ለማሻሻልም ይረዳል።

11) ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ¾p×ƒ ›¨dc” S`J ዎች (ከቁ. 1-10) u›ÖnLÃ c=□Ã ¾¨”ËM IÑ< የ p×ƒ አወሳሰን ማንዋል እንዲኖር የፈለገበት ¯LT TKƒU የ p×ƒ አወሳሰንን አንድወጥነት እና ትክክለኛነት በማረጋገጥ እሳቤ የተቀረፀ በመሆኑ □’²=I S`J‹ u¨”ËM IÑ< ¨<eØ Ÿ}ቀ SÖ<ƒ /Ÿ}SKŸ~ƒ/ K? KA‹ ¾p×ƒ ›¨dc” S`J‹ Ò` uTªHÉ □“ uT××U ØpU LÃ K=¨<K< ይ Ñv ል::

---

[16]በዚህ ረገድ በወንጀል ህጋችን ባህሪ ምክንያት በኛ ሀገር ሙሉ ለሙሉ በቀጥታ ሊተገበር ባይችልም በአሜሪካ ያለዉን ልምድ መመልከቱ ይረዳል፤-

In US the sentencing statute permits a court to depart from a guideline specified sentence only when it finds “an aggravating or mitigating circumstance of a kind, or to a degree, not adequately taken into consideration by the sentencing commission in formulating the guidelines that should result in a sentence different from that described”.

The commission has adopted this departure policy for two reasons:-

1st- it is difficult to prescribe a single set of guidelines that encompasses the vast range of human conduct potentially relevant to a sentencing decisions. The commission also recognizes that the initial set of guidelines need not do so. (*The Commission is a permanent body, empowered by law to write and rewrite guidelines, with progressive changes, over many years. By monitoring when courts depart from the guidelines and by analyzing their stated reasons for doing so, the Commission over time, will be able to refine the guidelines to specify more precisely when departure should and should not be permitted.

2nd. the Commission believes that despite the Courts legal freedom to depart from the guidelines, they will not do so very often. This is because the guidelines seek to take account of those factors that the commission’s data indicate made a significant difference in pre-guidelines sentencing practice.

The guidelines refer to two different kinds of departure. The first involves instances in which the guidelines provide specific guidance for departure by analogy or by other numerical or non-numerical suggestions as policy guidance for the courts. The commission expects that most departures will reflect the suggestions and that the courts of appeals may prove more likely to find departures “unreasonable ” where they fall outside suggested levels.

The second type of departure will remain unguided. It may rest upon grounds referred somewhere or on grounds not mentioned in the guidelines. The lists of factors that the commission believes may constitute grounds for departure, the list is not exhaustive. There may be other grounds for departure that are not mentioned. But such cases will be highly infrequent.

ምሳሌ-1

ጥፋተኛዉ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 3(1) ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ተብሏል፤ ፍርድ ቤቱም የሞት ቅጣት አማራጩን አልተቀበለም እንበል። በመሆኑም ቅጣቱ ከ 15 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ነዉ።

በሌላም በኩል ጥፋተኛዉ ወንጀሉን እስካደረገ ድረስ የዘወትር ፀባዩ መልካም እንደሆነና ያጠፋውም በእውቀት ማነስ እንደሆነ (የወ/ህ/ቁ 82(1)(ሀ))፤ በእድሜ ያልበሰለ ለጋ መሆኑ እና ያልተማረ መሆኑን ፍ/ቤቱ በቅጣት ማቅለያነት የተቀበለው እንደሆነ(የወ/ህ/ቁ 86)፣ እንዲሁም ወንጀሉን ያደረገው በጥላቻ ቢሆን (የወ/ህ/ቁ 84(1)(ሀ)) ስሌቱ ተከታዩን ይመስላል፤-

- 1 ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት በድምሩ 3 ቅጣት
- 2 ፍ/ቤቱ የቀበለው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ማቅለያ ምክንያት እና
  1 ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት አለ

-የመነሻ ቅጣቱ መጀመሪያ 1 ሲደመር 30 ሲካፈል ለሁለት = 15.5 አመት

-የመነሻ ቅጣቱ መድረሻ 15 ሲደመር 30 ሲካፈል ለሁለት = 22.5 አመት

በመሆኑም a= ከ 15.5 አመት – 22.5 ዓመት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የነገሩን ሁኔታ ገምቶ /የወ/ህ/ቁ.88(2)/ የመነሻ ቅጣቱ 20 አመት ሊሆን ይገባል ቢል

$n_1=1$ $x_{1=}$ 10% x 20 ዓመት = 2 አመት

$n_2=3$ $x_{2\ =}$ 10% x 20 ዓመት = 2 አመት

$$\mathbf{Y = a + n_1 x_1 - n_2 x_2}$$

y= 20 ዓመት + (1x10% x 20 ዓመት) – (3 x 10% x 20 ዓመት)

y= 20 ዓመት + 2 አመት - 6 ዓመት

y= 16 ዓመት

ስለሆነም የመጨረሻው ቅጣት 16 አመት ይሆናል ማለት ነው።

ምሳሌ-2

ጥፋተኛዉ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 5(1)(ለ) የተመለከተዉን ተላልፎ ለሽብርተኝነት የሙያ ድጋፍ በመስጠቱ ጥፋተኛ ተብሏል እንበል። አንቀጹ ከ 10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ያስቀጣል።

በሌላም በኩል ወንጀለኛዉ ወንጀሉን ያደረገው ከፍ ባለ ሀይማኖታዊ እምነት ተነሳስቶ እንደሆነ (የወ/ህ/ቁ 82(1)(ለ))፤ እንዲሁም የበርካታ ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑና ፣ በአነስተኛ ገቢ እራሱንና ቤተሰቡን ማስተዳደሩን ፍ/ቤቱ የሚቀበለው ምክንያት ቢሆን(የወ/ህ/ቁ 86) ፤በሌላ በኩል ምንም አይነት ቅጣት ማክበጃ አልቀረበም።

በመሆኑም የመነሻ ቅጣቱ መጀመሪያ በወ/መ/ህ/ቁ 179/ሐ/ መሰረት 1 አመት ሲደመር ጣራ ቅጣቱ 15 አመት ሲካፈል ለሁለት ይሆናል 8 አመት። የመነሻ ቅጣቱ መድረሻ ደግሞ 10 ሲደመር 15 ሲካፈል ለሁለት ይሆናል 12.5 አመት።

በመሆኑም መነሻ ቅጣቱ ማለትም “a” ከ 8-12.5 አመት ሲሆን ዳኞች የነገሩን ሁኔታ ግምት ዉስጥ አስገብተዉ/በወ/መ/ህ/ቁ.88(2)/ ከዚህ ክልል ሳይወጡ የመነሻ ቅጣቱ 10 ዓመት ነዉ ብለዉ ወስነዋል እንበል።

1 ጠቅላላ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት እና 2 ፍ/ቤቱ የተቀበላቸው ምክንያቶች አሉ ማለት ነው ። ይኸውም በአጠቃላይ 3 ማቅለያ ምክንያቶች አሉ

a= 10 ዓመት

n_2= 1 + 2 = 3

x_2 = 10 ዓመት x 10% = 1 ዓመት

$Y = a + n_1 x_1 - n_2 x_2$

ነገር ግን ቅጣት ማክበጃ አልቀረበም በመሆኑም ቀመሩ እንደሚከተለዉ ይሆናል

y= a - n_2x_2

=10 ዓመት - (3 x 1 ዓመት)

= <u>7 ዓመት</u>

ስለሆነም ቅጣቱ 7 አመት ይሆናል ማለት ነው።

<u>3.3. *የወንጀል ደረጃዎችን እንደክብደታቸው/አደገኛነታቸው ደረጃ በማውጣት ላይ የተመሰረተ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ*</u>

የቅጣት አወሳሰን ጋይድላይን ለማውጣት ከተመረጡት በአምስቱ ማለትም፣

- ስልጣን አለአግባብ መገልገል (407)
- በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ (ከ555-560)

- ስርቆት (665 እና 669)
- ውንብድና (670 እና 671)
- ማታለል (692 እና 693)

የተዘጋጁት ረቂቅ ጋይድላይኖች የሚያመሳስላቸው መሰረታዊ ባህርይ በወንጀል ድንጋጌው እንደአደገኛነቱና ከባድነቱ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የወንጀል አፈጻጸሞችን ደረጃ በማውጣት ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ በህጉ ከተቀመጠው ዝቅተኛ መነሻ በመነሳት የቅጣት መጠኑ እያደገ የሚሄድ የቅጣት መነሻ የሚጥሉ በመሆኑ፣ እናም ለዳኛው የነበረውን ሰፊ ፍቅድ የሚያጠብ የቅጣት መነሻና መድረሻ ማስቀመጣቸው ነው።

ይህ ሞዴል በመሰረቱ በአሜሪካ ፌዴራል መንግስት ከሚሰራበት የቅጣት ጋይድላይን ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።

በእነዚህ የጥናት ጽሁፎች በህግ አውጪው በወንጀል ህጉ የተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ ሳይለወጥ በቅጣት አወሳሰን የዳኞችን ሰፊ ፍቅድ በመቀነስ ቢያንስ አንድ የወንጀል ድንጋጌ ሲጣስ ተመሳሳይና ተቀራራቢ በሆኑ የወንጀል ድርጊቶች መካከል ወጥነት ያለው ስለሆነም እንደወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት አንጻርም ተመጣጣኝነት ያለው ቅጣት ለመወሰን የሚያስችል ስርአት መዘርጋት ይቻላል ከሚል መነሻ የተነሳ ነው።

በዚህ አማራጭ የቀረበው የቅጣት አወሳሰን አሁን ባለው የወንጀል ህግ ስርአት ውስጥ ከእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌ አንጻር የሚዘጋጅ የቅጣት አወሳሰን ጋይድላይን ወጥነትን፣ ተመጣጣኝነትን፣ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትንና ተገማችነትን ለማምጣት የሚከተሉትን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል የሚል መነሻ አለው።

<u>ታሳቢዎች</u>

1. ምንም እንኳን በየድንጋጌው ወንጀሉን የሚያቋቁመውን ፍሬነገር በሚመለከት ተመሳሳይ ቢሆንም፣ ይሁንና ከአደገኛነታቸው አንጻር፣ ወይም ከሚያደርሱት ጉዳት አንጻር ልዩነት ሊደረግባቸው የሚገቡ የወንጀል ድርጊቶች ተለያይተው ሊቀመጡ ይገባል። ከዚህ አንጻር በቅጣት አጣጣል ልዩነት ሊያመጡ የሚገቡ መሰረታዊ ፋክተሮች ምን እንደሆኑ ተለይቶ መቀመጥ አለበት።
2. ህግ አውጪው ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የቅጣት መነሻና ጣሪያ አድርጎ ያስቀመጣቸው የቅጣት መጠኖች ትርጉም ሊኖራቸው በሚችል መልኩም የቅጣት ጋይድላይኑ መዘጋጀት አለበት። ለወንጀል ድርጊቱ አግባብነት ያላቸው የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ተለይተው መቀመጥና እያንዳንዳቸውም ተሟልተው ሲገኙ በማቅለልም ሆነ በማክበድ ከጊዜ አንጻር የሚያመጡትን ልዩነት ጣሪያው ላይ የሚደረሰው መቼ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ሲቀልም ዝቅተኛው ወለል ላይ የሚደረሰው በምን ሁኔታ እንደሆነ ማሳየት አለበት።

3. እነዚህ የወንጀል ደረጃዎችን ለማውጣት እንዲሁም የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎችን የምንጠቀምባቸው መለኪያዎች አጠቃላይነት ስለሚኖራቸው፣ እና በዚህ ውስጥ ሊጠቃለሉ የማይችሉ እንደወንጀሉ ሁኔታ ሊታዩ የሚገቡ (ኢንዱቪዝዋላይዝ) የሚያደርጉ ባህርያትን ከግምት ለማስገባት እንዲቻልም፣ ተገቢ የሆነ ሬንጅ ወይም ፍቅድ ስልጣን ለዳኛው የተወ ሊሆን ይገባል። ይሁንና ሬንጁ/ ልዩነቱ ያለአግባብ እንዳይሰፋ ተቀራራቢነት ያለው ሊሆን ይገባል።

ከዚህ በመቀጠል ለአምስቱም የወንጀል አይነቶች በቅደም ተከተል እንደወንጀሉ ባህርይ/አይነት የሚያገለግሉ መለኪያዎችን ወይም መስፈርቶችን በማዘጋጀት የተዘጋጀውን ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ እያደገ የሚሄደውን የወንጀል ደረጃዎች የሚያሳይ መግለጫ እንመለከታለን፡

3.3.1. <u>በስልጣን አለአግባብ መገልገል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች፣</u>

<u>አንቀጽ **407.** በስልጣን አለአግባብ መገልገል</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፣

   ሀ. የተሰጠውን ሹመት ወይም ስልጣን በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፣

   ለ. በግልጽ ከተሰጠው ስልጣን አልፎ የሰራ እንደሆነ፣

   ወይም

   ሐ. ስልጣኑ የማይፈቅድለትን ጉዳይ በተለይም ስልጣን ሳይኖረው ወይም ከስራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ወይም ስልጣኑን ወይም ሀላፊነቱን ከተወ በኋላ የሰራበት እንደሆነ፣

   በህጉ ላይ ጉዳዩን በግልጽ የሚመለከት ከሌለ በቀር እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ አመት በማያንስ ቀላል እስራት፣ ወይም ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል።

2. ሀላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስበት የተፈለገበት አላማ፣ የተገኘው ጥቅሙ ከፍተኛነት፣ የጥፋተኛው የሀላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ፣ በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት የወንጀሉን አፈጻጸም ከባድ አድርጎት እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከሰባት አመት እስከ አስራ አምስት አመት ለመድረስ የሚችል ጽኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

3. በንኡስ አንቀጽ (2) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ተደራርበው ሲገኙ፣ ቅጣቱ ከአስር አመት እስከ ሃያ አምስት አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

የቁጥር 407 አደረጃጀትን ስንመለከተው፣ ወንጀሉ በሶስት ደረጃ ተከፍሎ ይታያል።

እነርሱም፣

1. ድርጊቱ በ 407(1) ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ ቅጣቱ ከ 1 አመት ቀላል እስራት እስከ 10 አመት ጽኑ እስራት ይሆናል።
2. <u>ከተፈጸመበት አላማ፣ ከስልጣን ደረጃው፣ ከተገኘው ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት አንጻር</u> ወንጀሉ ከባድ አድርጎት ከሆነ በቁጥር 407(2) ውስጥ የሚወድቅ ሆኖ ቅጣቱ ከ 7 አመት እስከ 15 አመት ይሆናል።
3. ወንጀሉን የሚያከብዱት ሁኔታዎች ተደራርበው ሲገኙ በቁጥር 407(3) ውስጥ የሚወድቅ ሆኖ ቅጣቱ ከ 10 አመት እስከ 25 አመት እንደሆነ ያስቀምጣል።

ከዚህ ድንጋጌ እንደምንረዳው የወንጀሉን ደረጃ (አደገኛነት) ለመወሰን፣ ስለሆነም ቅጣቱን ለመጨመር ወይም ለማክበድ ሶስት መስፈርቶች ስራ ላይ እንደሚውሉ ነው። እነርሱም፣

- ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ፣
- የወንጀል አድራጊው የሀላፊነት ደረጃ፣
- በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳት ናቸው።

እነዚህን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የወንጀል አድራጊው ሀላፊነት እየጨመረ ሲሄድ ቅጣቱ ሊከብድ እንደሚገባው፣ በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት እያደገ ሲሄድም ቅጣቱ ሊከብድ እንደሚገባው፣ ወንጀሉን ለመፈጸም የተያዘው አላማም ከባድ በሆነ ቁጥር ቅጣቱ እየከበደ ሊሄድ እንደሚገባው የህግ አውጪው ፍላጎት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር እነዚህን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ ደረጃ በደረጃ በሚያድግ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል።

ስለሆነም ለእያንዳንዱ መስፈርቶች መለኪያዎችን ማዘጋጀት ይቻላል። በዚህም መሰረት፣

<u>የወንጀል አድራጊው ሀላፊነት ደረጃን በተመለከተ፣</u>

የወንጀል አድራጊው የሀላፊነት ደረጃ የወንጀል አፈጻጸሙን ለማክበድ ስለሆነም ቅጣቱን ለማሳደግ እንደመስፈርት እንደሚያገለግል በህጉ ላይ ተመልክቷል። ይህንን መነሻ መሰረት በማድረግ የሀላፊነት ደረጃዎችን 1) ከፍተኛ የሀላፊነት ደረጃ፣ 2) መካከለኛ የሀላፊነት ደረጃ እና 3) ዝቅተኛ የሀላፊነት ደረጃ በማለት ከፋፍለናቸዋል።[17]

<u>ከፍተኛ የሀላፊነት ደረጃ</u>

የመንግስት ስልጣን በፌዴራልና በክልል የተከፋፈለ ሲሆን፣ የስልጣን መዋቅራቸውም እንደዚሁ የተለያየ ነው።

በፌዴራል ደረጃ በዋነኛነት የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ወይም የልማት ድርጅቶች ሲሆኑ፣ በተዋረድ የመምሪያ ሀላፊ፣ የቅርንጫፍ ሃላፊ፣ የስራ ሂደት መሪ ወዘተ የሚኖሩ ሲሆን፣ በክልል ደረጃ የቢሮ ሀላፊ፣ የዞን መስሪያ ቤት ሀላፊ፣ የወረዳ እና የቀበሌ

[17] የአሜሪካው ከብራይበሪ ጋር ያለው ድንጋጌ እንደሚያመለክተው የስልጣን ደረጃው ከፍ ማለት የሚቀጣበትን የቅጣት ደረጃ ከፍ እንደሚያደርገው ነው። (US sentencing guideline manual p.127, 2c1.1.(a)

መስተዳደር ሀላፊዎች ይኖራሉ። ከእነዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ ሌሎች ሰራተኞች ይኖራሉ። እነዚህን በሚመለከት የፌዴራል ህግን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የስራ ሀላፊዎችን በተመለከተ በተሻሻለው የፌዴራል የስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ የተሰጠ ትርጉም አለ። ይህ ትርጉም የተቀመጠው ከፍተኛ ሀላፊዎች የሚፈጽሙት ከባድ የሙስና ወንጀል ነው የሚለውን የአዋጁን ትርጉም መሰረት አድርጎ ነው።[18]

በአዋጁ አንቀጽ 2(9) ከባድ የሙስና ወንጀል ማለት የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች እንደሆኑ ይደነግጋል።

የመንግስት ባለስልጣን ማለት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 2(5) ተተርጉሟል።

‹የመንግስት ባለስልጣን ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባሎች፣ ከሚኒስትር ደረጃ በላይ የሆኑ የፌዴራል መንግስት ባለስልጣኖች፣ ሚስትሮች፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ ምክትል ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት አባላቶች፣ ከክልል ቢሮ ሀላፊዎች በላይ ያሉ ባለስልጣኖች፣ የክልል መንግስት ቢሮ ሀላፊዎች፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የአዲስ አበባ መስተዳድርና የድሬዳዋ መስተዳድር የምክር ቤት አባሎች፣ ከመስተዳድሮቹ ቢሮ ሀላፊዎች በላይ ያሉ ባለስልጣኖች፣ የመስተዳድሮቹ ቢሮ ሀላፎዎች እና በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል፣ የክልል እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬዳዋ መስተዳድሮች ባለስልጣኖችን ይጨምራል›

ይህንን ትርጉም ወስዶ አሁን ለማስቀመጥ ባሰብነው ከፍተኛ ሀላፊነት በሚለው ውስጥ ማስቀመጥ ይመረጣል። ከዚህ በላይ ከፍተኛ ሀላፊነት የሚባል በአገራችን ውስጥ የለምና:: በህጉም እነዚህ የሚፈጽሙት የሙስና ወንጀል ከባድ ተብሎ ተሰይሟልና።

ከዚህ በተጨማሪ ካላቸው የስራ ሀላፊነትና ለአገር ደህንነት ከሚያደርሱት ጉዳት አንጻር ምንም እንኳን በትርጉሙ ውስጥ የማይካተቱ ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ ከሀላፊነታቸው አንጻር በዚህ ደረጃ ሊመደቡ የሚችሉ ሀላፊዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ ዳኛው ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ደረጃዎች በአንዱ ውስጥ እንዲመደቡ ሊወስን ይችላል በሚል መፍቀድም ተገቢ ነው።[19]

<u>መካከለኛ የሀላፊነት ደረጃ</u>

ከእነዚህ የመንግስት ባለስልጣናት ውጭ ያሉ ውሳኔ የሚወስኑ የስራ ሀላፊነት ቦታዎች አሉ። እነዚህም ከፍተኛ ባለስልጣኖች ቀጥሎ ያሉት ማለትም የመምሪያ ሀላፊዎች ወይም ለበላይ ሀላፊው ተጠሪ የሆኑ ሀላፊዎች፣ የዞን ሀላፊዎችና መምሪያ ሀላፊዎች፣ የወረዳ ሀላፊዎችና መምሪያ ሀላፊዎች ይገኛሉ። እነዚህን በመሰረቱ በሀላፊነት የሚሰሩ ስለሆነ፣ የፌዴራል፣ የክልል ቢሮ፣ የዞን ወይም የወረዳ መሆናቸው ካልሆነ በስተቀር ተመሳሳይነት ስላላቸው መካከለኛ ሀላፊነት በሚለው ውስጥ መመደብ ይቻላል።

[18] የተሻሻለው የፌዴረል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2(9)

[19] ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 127. 2c1.1. b(3) (በአናሎጂ በመጠቀም ደረጃውን መመደብን የአሜሪካም ሆነ የእንግሊዝ ጋይድላይኖች ይፈቅዳሉ። ለምሳሌ በእንግሊዝ በእያንዳንዱ ጋይድላይን በምሳሌ መልክ በማስቀመጥ፣ ዳኛው ከምሳሌው ጋር የሚጣጣሙትን በተመሳሳይ እንዲያስቀምጥ ይፈቅዳል። በአሜሪካም በጋይድላይኑ ውስጥ ላልተጠቀሱ ወንጀሎች በአናሎጂ በመጠቀም ተመሳሳይ የሆነውን በመውሰድ የወንጀል ሌቭሉን እንዲያስቀምጡ ጋይድላይኑ ይፈቅዳል።

ዝቅተኛ የህላፊነት ደረጃ

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ምደባ ውስጥ የማይገቡትን ደግሞ በዝቅተኛ የስራ ደረጃ በሚለው እንዲመደቡ ማድረግ ይቻላል።

በወንጀሉ ምክንያት የተገኘው ጥቅም ወይም ጉዳት ከፍተኛነት ደረጃን በተመለከተ

በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወንጀል በዋነኛነት የሚፈጸመው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማስገኘት ስለሆነ፣ በተገኘው ጥቅም ወይም የገንዘብ መጠን መሰረት አደገኛነቱን ወይም ከባድነቱን ማስቀመጥ ይቻላል።

ይሁንና ወንጀል አድራጊው በፈጸመው ወንጀል ካገኘው ጥቅም ይልቅ ያደረሰው ጉዳት ሊበልጥ ይችላል። ህጉ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ጉዳቱም ከባድነቱን ለመወሰን እንደሚያገለግል የደነገገ ስለሆነ፣ ከጥቅሙና ከጉዳቱ የበለጠውን ከባድነቱን ለመመዘን እንደመስፈርት መውሰድ ምክንያታዊ ነው። በአሜሪካም ጋይድላይን በዚህ መልኩ ነው ደረጃውን ለማስቀመጥ የሚጠቀሙት። ጉዳቱ ከተገኘው ጥቅም በልጦ ከሆነ ለቅጣት አወሳሰን የሚወሰደው የበለጠው ነው።[20]

በዚህ መሰረት ወንጀሉን የሚያከብደውን መወሰን ይቻላል።

- ዝቅተኛው እስከ ብር 10000 የሚደርስ ጥቅም ወይም ጉዳት (ከሁለቱ የበለጠው)
- መካከለኛው የገንዘብ መጠን ከብር 10000 በላይ -100000
- ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ከብር 100000 በላይ[21]

የገንዘብ መጠኑን በተመለከተ ዝቅተኛው የሚባለው ውስጥ እስከስንት ብር ያለው ይውደቅ የሚለውን ለመወሰን አስቸጋሪ ነው። ይህንን በተመለከተ በዚህ ሰነድ የቀረበው በጸሀፊው አስተያየት መነሻ እንዲሆን ነው። ዋናው ነገር የገንዘቡ መጠን እየጨመረ መሄዱ ቅጣቱን እያከበደው መሄዱ ነው።

አንዳንድ ጊዜ የጥቅሙ መሰረት ጉዳቱ ሊሆን ይችላል። ማለትም ለምሳሌ የመንግስት ንብረትን ለግል ጥቅሙ ያዋለ ቢሆን፣ በዚያው ልክ መንግስት ይጎዳልና። ስለሆነም ተመሳሳይ እንደሚሆኑ ይገመታል። ይሁንና የሚበላለጡ ከሆነ የበለጠውን መውሰድ ተገቢ ነው።

ይሁንና አንዳንድ ጊዜ አንዱን ለመጥቀም ሌላውን ለመጉዳት ተብሎ የተሰራ ስራ፣ ጥቅሙና ጉዳቱ ላይመጣጠን ይችላል። ለምሳሌ በአንድ ጉዳይ ላይ የባለቤቱን መድሀኒት ቤት ለመጥቀም ሲል ተወዳዳሪ የሆነውን ድርጅት እንዲታሸግ በማድረጉ፣በርካታ መድሀኒቶች እንዲበላሹ ምክንያት የሆነበት ሁኔታ አለ።[22] ከዚህ አንጻር ጉዳቱ ሲተመን ባለቤቱ ካገኘችው ጥቅም በላይ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም የደረሰው ጉዳት መጠን ደረጃውን ለመወሰን ከግምት ሊገባ ይገባል።

[20] በአሜሪካ የቅጣት ጋይድላይን ከሁለቱ የበለጠው ለቅጣት አወሳሰኑ እንደመለኪያ ይወሰዳል።127. 2c1.1. b(2)

[21] ይህንን ካታጎሪ ለማስቀመጥ የተለየ መስፈርት አልተጠቀምኩም። በዚህ መልኩ ለማስቀመጥ እንዲቻል የተመረመሩት የቅጣት መዝገቦች የሚበቃ መረጃ የላቸውም። ይሁንና የገንዘቡ መጠን እየጨመረ ሲሄድ ቅጣቱም እንዲጨምር መደረጉ አይቀርም። በዚህ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ግብታዊነት የቅጣት መነሻና መድረሻ በማስቀመጥ ለመቀነስ ይቻላል የሚል እምነት አለ።

[22] ‹ህግና ፍርድ መጽሄት› በህብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ልዩ ፍርድ ቤት በአመት ሁለት ጊዜ የሚዘጋጅ መጽሔት (1977)፣ ቅጽ 2፣ ቁ፣ 2፣ ገጽ 87

ይሁንና የጥቅሙ መሰረት የግድ ጉዳቱ ሳይሆን፣ ጥቅሙንም አግኝቶ ጉዳትም በተጨማሪ ሊያደርስ ይችላል። እንዲህ ባለ ጊዜ ሁለቱንም አንድ ላይ በመደመር በሚገኘው መጠን ደረጃው ይወሰናል ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ የተገኘ ጥቅም መኖሩን ወይም የደረሰ ጉዳት መኖሩን ማስረዳት የማይቻልበት ጊዜ ይኖራል። እንዲህ ባለ ጊዜ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት በዝቅተኛ ደረጃ ከሚገመተው የገንዘብ መጠን ጋር አብሮ የሚታይ ይሆናል።

<u>ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማን መሰረት አድርጎ ደረጃ ማውጣትን በተመለከተ፣</u>

ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ የሚለውን መለኪያ መስፈርቶችን ለማውጣት የወንጀሉን ድንጋጌ በተለያዩ አላማዎች ሊጣስ እንደሚችል መገመት ይቻላል።

- በደረሰበት ኢኮኖሚ ችግር፣
- በአፍቅሮ ንዋይ፣
- በብቀላ (ሌላውን ሰው ለመጉዳት በማሰብ ብቻ፣)
- በአገር ክህደት
- በማን አለብኝነት፣ አጉል ትምክህት፣
- ጥፋትን ለመሸፈን፣
- ወዘተ ሊሆን ይችላል።

በእርግጥ ቸግሮት ስልጣኑን ያለአግባብ የተጠቀመውንና፣ በአፍቅሮ ንዋይ የሰራውን በእኩል ደረጃ ማየት ተገቢ አይሆንም። ከዚህ አንጻር ልዩነት ማበጀት ያስፈልጋል። ይሁንና በአፍቅሮ ንዋይ የተሰራ ነው በሚል ብቻም የገንዘብ መጠኑ አነስተኛ፣ የስልጣን ደረጃውም አነስተኛ የሆነውን በከባዱ በንኡስ ቁጥር 2 ውስጥ እንዲወድቅ ማድረግም የማይገባ ይመስላል።[23] ስለሆነም አፍቅሮ ንዋይ የሚለው በችግር ምክንያት ወንጀሉን ከፈጸሙት ለመለየት ጥቅም ላይ መዋሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይሁንና ወንጀሉን ለማከበድ ከአላማ አንጻር ሊጠቀሱ የሚገባቸው ምክንያቶች ሌሎች ከበድ ያሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይገባል። ከዚህ አንጻር ለምሳሌ ወንጀሉ የተፈጸመው የአገርን ምስጢር ለሌላ ለማዋል ከሆነ ከባድ አላማ ተብሎ ሊከብድ ይችላል። ስለሆነም ከዚህ ጋር ሊወዳደሩ የሚችሉ ተመሳሳይ አላማዎች በሚኖሩ ጊዜ ዳኛው ጉዳዩን በሚያከብደው ውስጥ እንዲወድቅ ያደርጋል ማለት ነው።

እነዚህን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ተቀራራቢና ተመሳሳይ ክብደትና አደገኛነት ያላቸውን በአንድ ላይ በማድረግ፣ አስራ ሁለት ደረጃዎችን ማውጣት ይቻላል።[24]

[23] ሌሎች ከችግር ውጭ ያሉ ምክንያቶች ለምሳሌ፣ በብቀላ፣ ሌላውን ሰው ለመጉዳት ወዘተ በአንድ ላይ ከአፍቅሮ ንዋይ ጋር በእኩል ደረጃ የሚቀመጡ ይሆናሉ።

[24] በዋናው የጥናት ሰነድ የተዘጋጁት ደረጃዎች 18 ሲሆኑ፣ ተመሳሳይ ክብደት ያላቸውን ተመሳሳይ መነሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ እንዲቻል ወደ 12 ወርደዋል። ዝርዝሩንና ምክንያቶቹን ለማየት ዋናውን ጥናት ይመልከቱ።

ደረጃ 1

1. ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣[25]

ደረጃ 2

2. ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 3

1. ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/ በችግር፣
2. መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 4

1. ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣
2. መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 5

1. መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/በችግር፣

ደረጃ 6

1. መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 7

1. ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣
2. ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 8

1. ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣
2. ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 9

1. ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣
2. መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 10

1. ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣
2. መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 11

1. ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 12

1. ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣

[25] ለቅጣት አወሳሰን ደረጃውን ለመወሰን እንዲቻል ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈጸመ እንደሆነ ተደርጎ ይገመታል።

ከእነዚህ ደረጃዎች መካከል፣ በንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 ውስጥ የሚወድቁት የትኞቹ እንደሆኑ መለየት ያስፈልጋል።

በህጉ እንደተቀመጠው ወደ ንኡስ አንቀጽ ሁለት ቅጣቱ የሚያድገው ወንጀሉን ለማከበድ ከተቀመጡት መስፈርቶች አንጻር ከፍተኛ የተባለው ተሟልቶ ሲገኝ ነው። ስለሆነም፣

1. በገንዘብ መጠኑ ከፍተኛ የተባለው ወይም በሀላፊነት ደረጃው ከፍተኛ የተባለው ተሟልቶ ከተገኘ ድርጊቱ በንኡስ ቁጥር 2 ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው።
2. እነዚህ ማክበጃዎች ሁለቱም በአንድ ጊዜ ተሟልተው ከተገኙ፣ በ 407 ድንጋጌ እንደተመለከተው በንኡስ ቁጥር 3 ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው።

ስለሆነም በየንኡስ አንቀጹ የሚወድቁ የወንጀል ደረጃዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል።

407(1)

ደረጃ 1

- ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 2

- ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 3

- ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/ በችግር፣
- መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 4

- ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣
- መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 5

- መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/በችግር፣

ደረጃ 6

- መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣

407 (2)

ደረጃ 1

- ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣
- ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 2

- ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣
- ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣

ደረጃ 3

- ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣
- መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 4

- ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣
- መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣

407(3)

ደረጃ 1

- ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣

ደረጃ 2

- ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው፣ የተፈጸመበት አላማ ከአፍቅሮንዋይ በላይም ሆኖ ከአላማው አስነዋሪነት አንጻር ወንጀሉ ሊከብድ ይገባል የሚል ድምዳሜ ላይ ዳኛው የደረሰ በሆነ ጊዜ፣ በንኡስ አንቀጽ ሁለት ውስጥ የሚወድቁት እንደሚከተለው ይሆናል።

- የጥቅም ወይም ጉዳቱ አነስተኛ/ዝቅተኛ የሀላፊነት ደረጃ ከሆነ (ደረጃ 7)
- የጥቅም ወይም ጉዳቱ አነስተኛ/መካከለኛ የሀላፊነት ደረጃ ከሆነ (ደረጃ 8)
- የጥቅም ወይም ጉዳቱ መካከለኛ/ዝቅተኛ የሀላፊነት ደረጃ ከሆነ (ደረጃ 8)
- የጥቅም ወይም ጉዳቱ መካከለኛ/መካከለኛ ሀላፊነት ከሆነ (ደረጃ 9)

የሚወድቅ ሆኖ፣ ከዚህ በላይ በንኡስ ቁጥር 2 ውስጥ በሚወድቁ የወንጀል ድርጊቶች ከባድ አላማው የተሟላ ከሆነ ከአንድ በላይ የሚያከብዱ ምክንያቶች ስለሚኖሩ በንኡስ ቁጥር 3 ውስጥ የሚወድቅ ይሆናል ማለት ነው።

3.3.2. <u>የስርቆት ወንጀል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች(665 እና 669)</u>

›G<” vK¨< ¾›=ƒÄåÁ ¨”ËM lÓ¹ ¾}KÁ¿ ¾e`qƒ ›Ã’„‹ ulÑ< LÃ }²`´[¨< ¾T>Ñ–< u=J”U uõ`É u?„‹ ²<]Á u}ÅÒÒT> ¾k[u< ÁK<ƒ u›”kê 665 e` ¾}Ökc¨<“ u›”kê 669 e` ¾}Ökc¨< (ŸvÉ e`qƒ) “†¨<::

u›”kê 665 e` ¾}Ökc¨< e`qƒ u›”kê 669 e` Ÿ}Ökc¨< ¾e`qƒ ›Ã’ƒ c=Ñ“²w #}^$ ¨ÃU kLM e`qƒ K=vM ¾T><M c=J” up×ƒU uG<Kƒ Øõ ¾T>KÁ¿ J• “Ñ—K”::

#}^$ ¨ÃU #kLM$ e`qƒ (›”kê 665) ukLM e^ƒ ¨ÃU eŸ ›Ueƒ ›Sƒ ê’< e^ƒ ¾T>ƴek× c=J” u›”kê 669 e` ¾}Ökc¨< ŸvÉ e`qƒ ÅÓV Ÿ1-15 ¯Sƒ ê’< e^ƒ ¾T>Áek× J• ÃÑ—M::

ቁጥር 665#}^ e`qƒ$

#T”U c¨< ¾TÃÑv¨<” wMêÓ“ KTÓ–ƒ ¨ÃU KK?L c¨< KTeÑ–ƒ uTcw ¾K?L c¨< ”w[ƒ ¾J’¨<” }”kdni °n ¨ÃU ŸTÃ”kdkȣ ”w[ƒ ¾}’ÖK” °n ›”e„ ¾¨cÅ ukØ ¾^c< ”w[ƒ ÁÅ[Ñ ¨ÃU u}²ªª] Ÿ^c< ”w[ƒ Ò` ”Ç=”kLkM ÁÅ[Ñ ”Å J’ ”Å ’Ñ\ G<’@ ukLM e^ƒ ¨ÃU 5 ›Sƒ uTÃuMØ ê’< e^ƒ Ãk×M::

ቁጥር 669 ŸvÉ e`qƒ”

#እ”ደ ¨”ËK< ¡wÅƒ“ u}c[k¬ n ›Ã’ƒ u¨”ËK—ው ¾’<a Å[Í“ G<’@ ”Ç=G<U u›c^[l ›Ã’ƒ kØKA ¾}²[²\ƒ ¾p×ƒ T¡uÍ G<’@‹ c=ÁÒØS< p×~ Ÿ›”É ¯Sƒ ¾TÁ”e kLM e^ƒ ¨ÃU Ÿ›e^ ›Ueƒ ¯Sƒ ¾TÃuMØ ê’< e^ƒ ¾T>J’¬፡-

1. ወንጀሉ የሚመለከታቸው

G) ¾}c[k¬ ȣn ¾HÃT•ƒ e`›ƒ uT>ðçUuƒ eõ^ ¨<eØ ¾T>Ñ˜ ¾HÃT•ƒ °n ¨ÃU uu?} S²¡` ¨<eØ ¾}kSÖ °n ¨ÃU KQ´w ¡õƒ uJ’ I”é ¨<eØ ¾}kSÖ dÃ”d©፣ Ÿ=’Øuv© ¨ÃU]"© ªÒ ÁK¬ °n ”ÅJ’፤

K) ¾}K¾ Övm ¾K?K¬ ”cd ¨ÃU cwM ¨ÃU K,K?¢T>¿’>Ÿ?i”' K›?K?Ÿƒ]¡ GÃM K¨<H“ õdi ¨ÃU KT“†¨<U K?L É`Ïƒ ›ÑMÓKAƒ ¾T>¨<M Övm ¾K?K¨< Sd]Á ¨ÃU ȣn ¨ÃU ”Ç=kSØ ¨ÃU ”Ç=L¡ Kȣn TŸT‰፣ K›”É É`Ïƒ ¨ÃU ¾S”Óeƒ Se]Á u?ƒ u}KÃU Kþe u?ƒ ¨ÃU KTSLKh É`Ïƒ ¾}cÖ gkØ ¨ÃU ȣn ”ÅJ’ ’¨<::

2) ወንጀሉን የፈጸመው

G) ¾SŸLŸÁ c^©ƒ ›vM J• ¨”ËK<” ¾ðçS¬ uÕÅ™‡ ¨ÃU u›Kq‡ LÃ c=J” ¨ÃU ¾}c[k¬ °n c^©~” ¾T>ÁÑKÓM ¨ÃU ”Ç=ÁÑKÓM ¾}SÅu c=J”፤

K) ¾S”Óeƒ c^}— ¨ÃU ›”É ¾”ÓÉ“ ÃI” ¾SdcK M¿ e^ ዮT>ÁŸ“¨<” c¬ ¾v”¡ c^} —፣ ጠun፣ ¨<M ›ªªÃ ¾¨Ÿ=M’ƒ eM×” ¾}cÖ¬ ”Å^c? ¨ÃU u”Å²=I ÁK U¡”Áƒ

¾}cÖ¨<” eM×” uTŸ“¨” LÃ ¾T>Ñ˜ ¾”ÓÉ e^ ›eŸ=ÁÏ J• É`Ñ>~” ¾ðçS¬ u}KÃ u}cÖ¬ eM×” U¡”Áƒ u□Ï uÑv¬ ¾S”Óeƒ ¾l´w ¨ÃU ¾ÓM ”w[ƒ LÃ c=J”₣

N) vK J,M₣ ¾u?ƒ ›Ÿ^Ã₣ °n ›SLLi₣ }g"T> ¨ÃU ÃI” ¾SdcK e^ ¾T>Á"H>É J• ¾}c[k¬ ”w[ƒ ¾Å”u—¬ c=J”₣

S) ¾u?ƒ W^}—₣ c^}— ¨ÃU e^ KTÏ J• e^¨<” U¡”Áƒ uTÉ[Ó u›dÇ]¨< ¨ÃU u›c]¨< LÃ Ñ<Çƒ uT>ÁÅ`e G<’@□ c=J”₣

3. አድራጊው

G). uc‹ ¨ÃU u”w[ƒ LÃ ¨”ËM KSðçU ¾}ssS u<É” ›vM c=J”₣

K) e`q~” ¾ðçS¨< u}KÃ ›ÅÑ— SJ’<” uT>ÁdÃ uT“†¨<U K?L G<’@□ ÃMl”U ¾TØmÁ ¨ÃU ¾SŸLŸÁ ¾Ù` Sd]Á ¨ÃU ¾u?ƒ Sc`c]Á Sd]Á uSÁ´ c=J” ¨ÃU u ሌK=ƒ ^c<” ¾S”Óeƒ c^}— uTeScM c=J” u ሌK=ƒ ¨ÃU pØ` uS×e₣ ›Ø` uS´KM ₣u` uSeu`₣ ÓÉÓÇ uSc`c` ¨ÃU uu<É” uSJ” c=J” ¨ÃU ÁM}Öuk ›ÅÑ— G<’@□” ¾l´w wØwØ” ¨ÃU Spcõƒ ÃMl”U □”Å Ó`Ó` nÖKA₣ Ô`õ₣ T°uM ¾SdcK<ƒ” ió” uTÉ[Ó c=J” ’¨<።

ከስርቆት ጋር በተያያዘ የወንጀሉን ክብደት እንዴት መወሰን ይቻላል የሚለው ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ መስፈርቶች ሊታዩ ይችላሉ።

የስርቆት ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ፣ የወንጀሉ አፈጻጸም፣ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት መጠን፣ በተጎጂው ላይ ያደረሰው ተጨማሪ ጉዳት ወይም አደጋ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው።

ይሁንና ወንጀሉ የተፈጸመበት አላማ፣ የወንጀሉ አፈጻጸምን በሚመለከት በጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች ድንጋጌ ቁጥር 84(1)(ሀ)፣(ሐ) እና (መ) ውስጥ እና በ 669(3) ውስጥም ተመልክተው የሚታዩ ስለሆነ፣ በወንጀል አፈጻጸሙ ተከስተው ከሆነ ቅጣቱን ለማክበድ ስለሚውሉ በዚያን ጊዜ የሚታዩ ይሆናሉ። ስለሆነም በወንጀሉ ከተገኘው የገንዘብ መጠን አንጻር የወንጀሉን ደረጃ ማውጣት የተሻለ መስሎ ይታያል። ከዚህ አንጻር በሌሎች አገሮች ከገንዘብ ጋር በተያያዘ እንደስርቆት፣ ማታለል፣ ወይም በግብር ክፍያ ማጭበርበርን የተመለከቱ ጉዳዮች የገንዘብ መጠንን እንደመስፈርት በመጠቀም የወንጀል አፈፃፀም ደረጃ የማዉጣት ልምዱ አለ።

ስርቆት በዋነኛነት የማይገባ ጥቅምን ለማግኘት የሚፈጸም ወንጀል በመሆኑ፣ በወንጀሉ ድርጊት የሚገኘው ጥቅም እየጨመረ በሄደ ቁጥር ሳቢነቱ ስለሚጨምር፣ የወንጀል አፈጻጸሙና ጎላፊነት መውሰዱም በዚያው ልክ ይጨምራል። ከዚህ አንጻር አደገኛነቱ ወይም የወንጀሉ ክብደትን የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ማውጣቱም ተገቢ ይመስላል።
ይሁንና ከወንጀሉ አፈጻጸም ደረጃም የተለየ መገለጫዎች በሚገኙበት ጊዜ ለምሳሌ በወንጀል ሰለባው ላይ ሌላ ተጨማሪ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ቢከሰቱ ቅጣቱን ለማክበድ የሚቻልበት ሁኔታም በዚህ ሰነድ ውስጥ እንዲታይ ተደርጓል።

በዚህ ሰነድ ከስርቆት ወንጀል ጋር በተያያዘ ለየደረጃው የተቀመጡት የተገኘው ጥቅም መጠን መነሻና መድረሻን በተመለከተ በጥናት ላይ ከተመሰረተ መረጃ የተነሳ አይደለም።[26] ዋናው ነገር የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ግምት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የወንጀሉ አደገኛነትና ሊያስከትል የሚችለው ቅጣትንም በዚያው ልክ እያደገ እንዲሄድ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በድንጋጌው መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ ስርቆት ሲሆን በደንብ መተላለፍ እንደሚቀጣ ስለሚያስቀምጥ፣ ለደንብ መተላለፍ የገንዘብ መጠኑ እስከ 100 ብር በሚል የሚታይ ቢሆን በሚል ሀሳብ ቀርቧል።
ስለሆነም ከዚህ መነሻ በመነሻጽ በ 665 መሰረት የወንጀል ደረጃዎች አወሳሰን፣

1. ከብር 100- 1000
2. ከብር 1000-2000
3. ከብር 2000-4000
4. ከብር 4000-10000
5. ከብር 10000-50000
6. ከከብር 50000-100000
7. ከብር 100000 በላይ

ከዚህ በተጨማሪ፣

[26] የስርቆት ወንጀል በ 665 እና ማታለል ወንጀል በ 662 የቅጣት መነሻቸውና መድረሻቸው ተመሳሳይ ቢሆንም፣ በሁለቱ ድንጋጌዎች የቀረቡት ጥናቶች በተለያዩ አጥኚዎች የተሰሩ በመሆኑ በየደረጃው የገንዘብ መጠኑን ለመጠቀም የተለያየ መጠንን ወስደዋል። ይሁንና ወንጀሎቹ በዋነኛነት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የሚሰሩ በመሆኑና የቅጣት መነሻና መድረሻቸው ተመሳሳይ ስለሆነ በዚህ ሰነድ ለሁለቱም ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን ደረጃዎች ተደርገው ቀርበዋል።

1. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በተሰረቀበት ሀብት/ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ መነሻውን ለመወሰን በገንዘብ መጠኑ ከተቀመጠበት ደረጃ በሁለት ወደላይ ያድጋል።

2. የተሰረቀው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ በተመሳሳይ በተመሳሳይ በሁለት ደረጃ ወደላይ ያድጋል።

3. ከዚህ በላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 2 ያሉት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ የእያንዳንዱ ተደምሮ የሚያስገኘው ከፍተኛው ደረጃ ድረስ ያድጋል።

በ 669 ወንጀሉ የስርቆት ወንጀል ቢሆንም ቅጣቱን የሚያከብዱ ድንጋጌዎች ያሉበት ነው። በዚህም መሰረት ቅጣቱ እስከ አስራ አምስት አመት ጽኑ እስራት እንደሚሆን አስቀምጧል።

በዚህም መሰረት ቅጣቱን የሚያከብዱት፣

- በተሰረቀው እቃ አይነት፣
- ድርጊቱን ከፈጸመው አድራጊ ማንነት፣
- የወንጀል አፈጻጸሙን

መሰረት አድርጎ ነው።

እነዚህ ማክበጃዎች ሁሉም ተደራርበው የሚገኙበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ሁሉ፣ አንዱ ማክበጃ ብቻ ተሟልቶ የሚገኝበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ስለሆነም ሁሉም ማክበጃዎች ተሟልተው በሚገኙበት ጊዜ የቅጣቱን መነሻ ከፍ ተደርጎ ለማስቀመጥ በሚያስችል መልኩ የወንጀል ደረጃዎቹ ተዘጋጅተዋል። ከዚህ አንጻር ለቁጥር 665 በተዘጋጀው የገንዘብ መጠን መሰረት ማክበጃዎች ተሟልተው የሚገኙበትን መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ደረጃዎች ወጥተውለታል።

1. ደረጃ 1 ከብር 100 እስከ ብር 1000 ሆኖ በ 669 የተመለከተው አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣
2. ደረጃ 2 እስከ ብር 1000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 2000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣
3. ደረጃ 3 እስከ 1000 ሆኖ ሶስት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 2000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 4000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣

4. ደረጃ 4 እስከ 2000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 4000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 10000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልተው ሲገኙ፣

5. ደረጃ 5 እስከ ብር 4000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 10000 ሆኖ ሁለቱ ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 50000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣

6. ደረጃ 6 እስከ 10000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 50000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 100000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣

7. ደረጃ 7 እስከ 50000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 100000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም ከብር 100000 በላይ ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣

8. ደረጃ 8 እስከ 100000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም ከ 100000 በላይ ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣

9. ደረጃ 9 ከብር 100000 በላይ ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል ማለት ነው።

3.3.3. <u>የማታለል ወንጀል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች (692 እና 693)</u>

በወንጀል ህጉ የተመለከቱት የማታለል ወንጀል የተባሉት ከታች የተዘረዘሩ በመሆናቸዉ በጣም ሰፊ ናቸዉ። በመሆኑም ለጋይድላየኑ ዝግጅት እንዲመች የተወሰኑትን የማታለል ወንጀሎች መምረጥ ያስፈልጋል። አንድ አንድ የማታለል ወንጀል ተብለዉ የተመለከቱት በፍርድ ቤቶች ታሪክ ተከስተዉና ታይተዉ የማይታወቁ በመሆናቸዉ ከተሰበሰበዉ መረጃ ማገናዘብ ይቻላል። በምን መስፈርት አዘዉትረዉ የሚከሰቱትን ለህብረተሰቡ ሠላምና ደህንነት ለኢኮኖሚዉም ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉትን መለየት ይቻላል የሚለዉ ትልቅ ጥያቄ ሆኖ ምላሽ የሚሻ ነዉ። በምጣኔ ሀብት ቋንቋ ደግሞ ለመፍትሔ አፈላለግ የሚቀመጥ የአደጋ መገመቻ መርሆዎች አሉ። እነዚህም ቶሎ ቶሎ የማይከሰቱና ትልቅ አደጋ የማያመጡ፣ቶሎ ቶሎ የማይከሰቱና ከፍተኛ አደጋ የሚያመጡ፣ ቶሎ ቶሎ የሚከሰቱና ዝቅተኛ አደጋ የሚያመጡ እና ቶሎ ቶሎ የሚከሰቱና ከፍተኛ አደጋ የሚያመጡ ናቸዉ። በእነዚህ መርሆዎች መሠረት የማታለል ወንጀል ከክስተትና ከአደጋ አንፃር ቢፈተሽ የመጀመሪያ ሁለቱ ሲቀሩ ቀጥለዉ የተመለከቱት ሁለቱ ቶሎ ቶሎ የሚከሰቱ የወንጀል አይነቶች ሆነዉ ነገር ግን የአደጋዉ መጠን ከፍተኛም ቢሆን ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል ግን የተወሰነ ጉዳት ስለሚያስከትሉት ለእነዚህ ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን ማሉዋሉ ሊዘጋጅ ይገባል ብሎ አዘጋጁ ያምናል።

ይህ በመሆኑ ፍርድ ቤቶችን ከማጨናነቅና ከክስተት አንፃር ከተሰበሰቡት 212 የፍርድ ቤት መዝገቦች 138 የሚሆኑት ማለትም 65% የሚሆኑት በተሻረዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በአንቀፅ 656 አሁን በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀፅ 692 በመተላለፍ የተፈፀሙ ናቸዉ። ሌላዉ ቶሎ ቶሎ በመፈፀም/በመከሰት/ በሁለተኛ ደረጃ ሊቀመጡ የሚችሉት በቀድሞዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 657 በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀፅ 693 በመተላለፍ የሚፈፀሙ ስንቅ የሌለዉ ቼክ

መስጠት ከ212 መዝገብ ዉስጥ 60 የሚሆኑት ሲሆኑ በፔርሴንት ደረጃ 28% ያህል ይሆናሉ ማለት ነዉ። መረጃዉ የሚያሳየዉ ይህ በመሆኑ ለእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቢወጣለት የተሻለ ነዉ።

ቁጥር **692**፣ አታላይነት

1. ማንም ሰው የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገንን ንብረት ጥቅም የሚጐዳ አድራጐት እንዲፈፅም ያደረገው እንደሆነ፣ በቀላል እስራት ወይም እንደነገሩ ከባድነት እስከ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል።
2. በወስላታነት የሌላ ሰውን አገልግሎት እንደማግኘት በመሰለ አሰራር ሆኖ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት አነስተኛ የማታለል ተግባር በፈፀመ ሰው ላይ የደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎች ቅጣት ይፈፀምበታል /አንቀጽ 855 እና 859/

አንቀጽ **693** የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት

1. ማንም ሰው ቼክ በሚወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ/ እንደሆነ፤

   በቀላል እስራት ወይም እንደነገሩ ከባድነት ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል።
2. አድራጐቱ የተፈፀመው በቸልተኛነት እንደሆነ፤ በመቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል።

የማታለል ወንጀል በተመሳሳይ መልኩ ከጥቅም ማግኘት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ደረጃዎቹም በተገኘው ጥቅም መጠን መሰረት በተመሳሳይ ተዘጋጅተዋል።

በቁጥር 692 የቅጣቱ መነሻና መድረሻ ከ665 ስርቆት ወንጀል ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ተመሳሳይ ደረጃዎችና የቅጣት መነሻ ተዘጋጅቷል።

በ692 መሰረት የወንጀል ደረጃዎች አወሳሰን፣

1. ከብር 100- 1000
2. ከብር 1000-2000
3. ከብር 2000-4000
4. ከብር 4000-10000

5. ከብር 10000-50000
6. ከከብር 50000-100000
7. ከብር 100000 በላይ

ከዚህ በተጨማሪ፣

1. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በማታለሉ ተግባር በተወሰደበት ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ መነሻውን ለመወሰን በገንዘብ መጠኑ ከተቀመጠበት ደረጃ በሁለት ወደላይ ያድጋል።
2. የተወሰደው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ በተመሳሳይ በተመሳሳይ በሁለት ደረጃ ወደላይ ያድጋል።
3. የተወሰደው ንብረት ለወንጀል ተጎጂው ልዩ ትርጉም ያለው ከሆነና ወንጀል አድራጊውም ይህንን እያወቀ የወሰደው ከሆነ በአንድ ደረጃ ወደላይ ያድጋል።
4. ከዚህ በላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ያሉት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ የእያንዳንዱ ተደምሮ የሚያስገኘው ከፍተኛው ደረጃ ድረስ ያድጋል።

ለ 693 የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ መነሻው 1 አመት የሚል ስለሆነ፣ የቅጣት መነሻው ይለያይ እንጂ ደረጃውን ለመወሰን ተግባራዊ የሚሆነው ለ 692 ተግባራዊ የሆነው መስፈርት ነው።

በ 693 መሰረት የወንጀል ደረጃዎች አወሳሰን፣

1. ከብር 100- 1000
2. ከብር 1000-2000
3. ከብር 2000-4000
4. ከብር 4000-10000
5. ከብር 10000-50000
6. ከከብር 50000-100000

7. ከብር 100000 በላይ

ከዚህ በተጨማሪ፣

- ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በተወሰደው ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ መነሻውን ለመወሰን በገንዘብ መጠኑ ከተቀመጠበት ደረጃ በሁለት ወደላይ ያድጋል።

3.3.4. <u>የውንብድና ወንጀል ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች(670 እና 671</u>

የውንብድና ወንጀል በ **1997** ዓ.ም ተግባራዊ በሆነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ **670** ሥር ተራ ውንብድና፤ እንዲሁም አንቀጽ **671** ሥር ከባድ ውንብድና በሚል በሁለት አንቀፆች ተከፋፍሎ ይገኛል። ክፍፍሉ መሠረት ያደረገው በዋኛነት የወንጀል ድርጊቱ በሰለባዎቹ ላይ የሚያስከትለውን የጉዳት ዓይነት ወይም ይዘት ወይም ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

አንቀጽ 670 <u>ውንብድና</u>

ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ፣ የሌላ ሰው ንብረት ወይም የሆነውን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኋላ የገጠመውን ተቃውሞ ውጤታማነት ለማስቀረት ሲል፤ በሌላ ሰው ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ከባድ ዛቻ *መፈፀም*፣ ወይም በማናቸውም ሌላ *መንገድ* ይህን ሰው ለመከላከል እንዳይችል ያደረገው ሲሆን፤ ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

አንቀጽ 671 <u>ከባድ ውንብድና</u>

1. አድራጊው በአንቀጽ 670 የተመለከተውን ወንጀል የፈፀመው፦
   ሀ/ በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ላይ የኃይል ተግባር ለመፈፀም በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ሲሆን፤ ወይም
   ለ/ ተበዳዩን እገድልሀለሁ ብሎ እርግጠኛ የሞት አደጋ እንደሚያደርስበት በመቃጣት፣ ይልቁንም በጦር *መሳሪያ* ወይም በተለይ አደገኛ በሆነ ሌላ ዓይነት *መሳሪያ* በማስፈራራት ወይም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት በማድረስ ሲሆን፣ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
2. ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈፀመው ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር *መሣሪያ* ወይም ሌላ አደገኛ *መሳሪያ* በመያዝ፣ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን የተጠቀመ፣ ወይም የተፈፀመው የኃይ ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ በሆነ ጊዜ የሞት ፍርድ ለመወሰን ይችላል። በጦር *መሣሪያ* አማካይነት በልማደኛነት በቡድን የሚፈፀም ውንብድና የሞት ቅጣትን የሚያስከትል ይሆናል።

የውንብድና ወንጀል ከስርቆት የሚለየው አፈፃፀሙ ኃይል የታከለበት ስለሆነ ነው። ስለሆነም የወንጀል ድርጊቱ ሀይል መጠቀምን ያካተተ ስለሆነ፣ የሀይል መጠቀሙን መሰረት አድርጎ ቅጣት በህጉ እንዲከብድ ተደርጓል።

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ወንጀሉ ከስርቆት ጋር የሚያመሳስለው ስለሆነ የተገኘውን ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት መሰረት በማድረግ የቅጣት ደረጃውን መወሰን ምክንያታዊና ሎጂካል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግን ሀይልን የመጠቀም ተግባር ስላለው ከሀይል አጠቃቀሙ አይነትና ከደረሰው ጉዳት አንጻርም ደረጃ ለማውጣት በመስፈርትነት መጠቀም ተገቢ ነው።[27]

የዩኤስ አሜሪካ የቅጣት ጋይድላይን ከውንብድና ጋር በተያያዘ የተዘጋጀው የወንጀል ደረጃን ለመወሰን መስፈርት ሆኖ የተወሰደው የሀይል አጠቃቀሙን መሰረት በማድረግ ሲሆን፣ በቀጣይነት ከተገኘው የገንዘብ ጥቅም አንጻርም ደረጃውን የማውጣት ስራ ተሰርቷል።

በተመሳሳይ መልኩም ለ 670 እና 671 የሀይል አጠቃቀሙን መሰረት በማድረግ ደረጃዎች የወጡ ሲሆን፣ ከዚህ ጎን ለጎን እንደገንዘቡ ከፍተኛነት መጠንም ቅጣቱ ከፍ እንዲል ደረጃው ከፍ እያለ እንዲሄድ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ደረጃው እንደሚከተለው ቀርቧል።

በ670 መሰረት

ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው ተንቀሳቃሽ ንብረት በሚወስድበት ጊዜ፣

1. ደረጃ 1.
    - ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና
    - በወንጀሉ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም እስከ ብር 2000 የሆነ እንደሆነ፣ [28]
2. ደረጃ 2.
    - ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 የሆነ እንደሆነ
3. ደረጃ 3.
    - የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣ ወይም

[27] የውንብድና ወንጀልን በተመለከተ ጥናት ያጠኑት ባለሙያ የወንጀል ደረጃዎቹን ለማውጣት የሀይል አጠቃቀሙን፣ የተጠቀመበትን መሳሪያ፣ የደረሰውን ጉዳት መሰረት በማድረግ እስከ 18 ደረጃዎችን አውጥተዋል። ይሁንና በድርጊቱ የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን የገንዘብ ጉዳት በሚመለከት ደረጃውን ለመወሰን አላካተቱትም። ይሁንና የተገኘው የገንዘብ ጥቅም መጠን ወንጀሉን ለማከበድ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ በማመን በዚህ ሰነድ ደረጃው ሲወጣ የሀይል አጠቃቀሙንም፣ የተገኘውን የገንዘብ መጠን ባካተተ መልኩ ደረጃውን የማውጣት ስራ ተሰርቷል። ከዚህ በተጨማሪ የደረጃዎቹን መጠንም ዝቅ ለማድረግ በሚያስችል መልኩም ለማዘጋጀት ተሞክሯል።

[28] በ 670 የወንጀል አፈጻጸሙ የአካል ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ከባድ ከሆነ በ 671 የሚታይ ሲሆን፣ ቀላል ከሆነ ደግሞ በ 670 ከመከሰሱ በተጨማሪ በ 556 ቀላል የአካል ጉዳት በማድረስ የሚከሰስ በመሆኑ የአካል ጉዳትን በተመለከተ ምን ያህል ደረሰ የሚለውን ደረጃውን ለማውጣት በመስፈርትነት አልዋለም።

- ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም
- ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣

4. ደረጃ 4.
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2000-10000 ከሆነ፣
5. ደረጃ 5
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 10000-30000 ከሆነ፣
6. ደረጃ 6
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተፈጸመው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ፣
    - በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 30000-100000 ከሆነ፣
7. ደረጃ 7
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300 ሺህ እስከ 1 ሚሊዮን ብር ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000-300000 ከሆነ፣
8. ደረጃ 8
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣
9. ደረጃ 9
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1000000 በላይ ከሆነ፣

በ671 (1) መሰረት ወንጀሉን ስለሆነም ቅጣቱን የሚያከብዱ ማክበጃዎች ያሉት ነው። ስለሆነም በአጠቃላይ በድንጋጌው ያሉትን ማክበጃ ሁኔታዎች ስንመለከት በሶስት ደረጃ ከፋፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል። ከዚህ ጎን ለጎንም የገንዘብ መጠኑ እየጨመረ ሲሄድም የቅጣቱ መጠን ከፍ እንዲል ለማድረግ በሚቻል መልኩ ደረጃው ወጥቷል።

1. ደረጃ 1
    - ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 2000 የሚደርስ እንደሆነ፣

2. ደረጃ 2
    - ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ እገልህለሁ ብሎ ያስፈራራ፣ ለዚህም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘቡ መጠን እስከ ብር 2000 የሚደርስ እንደሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2000-10000 የሚደርስ እንደሆነ፣
3. ደረጃ 3
    - የጦር መሳሪያ ይዞ ያስፈራራ ለዚህም እገልህለሁ ብሎ ያስፈራራ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 2000 የሆነ እንደሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣
4. ደረጃ 4
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣
5. ደረጃ 5
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ፣
6. ደረጃ 6
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ፣
7. ደረጃ 7
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1000000 በላይ ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ፣
8. ደረጃ 8
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000 በላይ ከሆነ ወይም፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣(ለእስራት ቅጣት ደረጃ 24፣)
9. ደረጃ 9
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1000000 በላይ ከሆነ፣

በ**671(2)**

- ደረጃ 1

    - ወንጀል የተፈጸመው ከተደራጀ የወንጀል ቡድን ጋር በመሆን ከሆነ፣ ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሣሪያ በመያዝ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን የተጠቀመ እንደሆነ ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሣሪያ በመያዝ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን በመጠቀም የተፈፀመው ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ሆኖ ሁኔታው እጅግ ከባድ በሆነ ጊዜ፣

ደረጃ 2.

- በጦር መሣሪያ አማካይነት በልማደኛነት በቡድን የሚፈፀም ውንብድና

3.3.5. <u>በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ከዝቅተና ወደከፍተኛ የወንጀል ደረጃዎች (555-560)</u>

በሰዎች አካልና ጤንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች አስቦ ወይም በቸልተኝነት፤ በማንኛውም አይነት ዘዴ ቢፈፀሙም፤ ለቅጣት እንደሚዳርጉ የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 553(1) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ይደነግጋል። በዚህ ረገድ ከአንቀፅ 555 እስከ 560 ላሉ ድንጋጌዎች የእጅ እልፊት፣ ቡጢ፣ ቁስል፣ አካል ማጉደል፣ የአካል ጉዳት፣ የአካል የአእምሮና የሞራል ጉዳትና በሰውነት፣ በአእምሮ ውስጥ በጤንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎቸን አካቷል። የወንጀሉ ዓይነት፣ የሚያስከትለው ውጤት ወይም አደገኛነቱና ክብደቱ ላይ ፍ/ቤቱ ጥርጣሬ ውስጥ የገባ እንደሆነ፣ አግባብነት ባለው የህክምና ማስረጃ እንዲረጋገጥ ማድረግ እንደሚችል አንቀፅ 554 ይደነግጋል።

በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚደነግገው የሕጉ ምእራፍ ውስጥ (አንቀፅ 555-560)፤ የተለያየ ክብደትና ዓይነት ያላቸው ወንጀሎች ተዘርዝረው እናገኛለን። በወንጀል ህጋችን በአንቀፅ 555 ስር ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት፣ በአንቀፅ 556 ስር ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት፣ በአንቀፅ 558 ስር ቀላል የአካል ጉዳት ለማድረስ ታስቦ በቸልተኛነት የሚፈፀም ቀላል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት፣ እንዲሁም በአንቀፅ 560 ስር የእጅ እልፊት ወንጀል በማለት ከፋፍለዋቸዋል።

አንቀጽ 555 <u>ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት</u>

ማንም ሰው አስቦ፥-

ሀ/ የተጐጂውን ሕይወተ በሚያሰጋ ወይም በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ በሚያተርፍ ሁኔታ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የሌላ ሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶቹ ወይም ሕዋሳቶቹ አንዱን ያጐደለ፣ እንዳያገለግሉት ያደረገ ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖበሚታይ ሁኔታ መልኩን ያበላሸ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ/ በማሃቸውም ሌላ መንገድ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ እንደሆነ፤

እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳቱ ከባድነት ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል።

አንቀጽ 556 <u>ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት</u>

1. ማንም ሰው ከዚህ በላይ በአንቀጽ 555 ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ አስቦ በሰው አካል ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ በግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።
2. ድርጊቱ በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጣውና ቅጣቱ ከስድስት ወር እስከ ሶስት ዓመት ለመድረስ የሚችል ቀላል እስራት የሚሆነው፡-

   ሀ/ ጥፋተኛው ጉዳት ያደረሰው በመርዝ ወይም በገዳይ መሣሪያ ወይም የአካል ጉዳት ለማድረስ በሚችል በማናቸውም ሌላ መሳሪያ በመጠቀም እንደሆነ፤ ወይም

   ለ/ ጥፋተኛው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታን በመተላለፍ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ. ወይመ

   ሐ/ ተጐጂው ደካማ፣ በሽተኛ ወይም ራሱን ለመከላከል የማይችል እንደሆነ፤ነው።

አንቀጽ 557 <u>የቀጣት ማቅለያ ሁኔታዎች</u>

1. ማንም ሰው በሌላ ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ አስቦ ጉዳት ያደረሰው፡-

   ሀ/ የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን በመተላለፍ /አንቀጽ 75/ ወይም ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሣለፍ /አንቀጽ 78/////////// እንደሆነ፤ ወይም

   ለ/ ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ መቀስቀስ ምክንያት፣ ባልጠበቀው ህሊናን በሚያውክ ድንገተኛ ምክንያት፣ ወይም በከፍተኛ ስሜት ወይም ከብርቱ ዝንባሌ የተነሳ ሆኖ ሁኔታዎቹ በአእምሮ ግምት ድርጊቱን ከመፈፀም የሚያደርሱና በከፊል ይቅርታን የሚያሰጡ እንደሆነ፤ ወይም

   ሐ/ የደረሰው ጉዳት በሕግ የተከለከለ ወይም ጉዳቱ መልካም ጠባይን /ሞራልን/ የሚነካ በሚሆንበት ጊዜ የድርጊቱን ምንነትና ውጤት መገመት በሚችል ተጐጂ ጥያቄ ወይም ፈቃድ መሠረት እንደሆነ፤

   ቅጣቱ ከሁለት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአራት ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) በተመለከተው ሁኔታ ተጐጂው በዕድሜው ወይም በአእምሮው ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ጥያቄው ወይም እሺታው የሚያስከትለውን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ለመረዳት የማይችል እንደሆነ፤ በጥፋተኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት ከአራት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ይሆናል።

አንቀጽ 558 <u>ከጥፋተኛው አሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት</u>

ማንም ሰው ቀላል የአካል ጉዳት ለማድረስ አስቦ፣ በቸልተኛነት ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ ከስድስት ወር እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል።

አንቀጽ 559 <u>በቸልተኝነት የሚፈፀሙ የአካል ጉዳቶች</u>

1. ማንም ሰው በቸልተኛነት በሌላ ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ ቀላል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር አንድ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
2. የደረሰው ጉዳት በአንቀጽ 555 የተመለከተው ዓይነት ከሆነ ወይም ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤነነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ለላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው እንደሆነ፤ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራትና ከአንድ ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ ይሆናል።
3. ወንጀሉ የሚያስቀጣው ጉዳቱ ከባድ ከሆነ በወንጀል ክስ አቅራቢነት፣ ጉዳቱ ቀላል ከሆነ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ነው። የጉዳቱ መጠን የሚወሰነው በአንቀጽ 555 እና 556 በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

አንቀጽ 560 <u>የእጅ እልፊት</u>

1. ማንም ሰው የአካል ጉዳትን ወይም የጤንነት ጉድለትን ሳያደርስ በሌላ ሰው ላየ የእጅ እልፊት ወይም የመጋፋት ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤የግል አቤቱታ ሲቀርብበት ከሶስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ፣ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከሶስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል። ቀላል የሆኑ ሰንበሮች፣ የደም መቋጠር ምልክቶች ወይም በቶሎ የሚያልፍ ሕመም ሥቃይ እንደ አካል ጉዳት ወይም እንደ ጤና ጉድለት አይቆጠሩም።
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ውጭ የሆኑ ጥፋቶች በዚህ ሕግ ስለደንብ መተላለፍ በአንቀጽ 840 በተደነገገው መሠረት ያስቀጣሉ።
3. ተበዳዩ የተፈፀመበትን የእጅ እልፊት ወዲያውኑ በእጅ እልፊት የመለሰ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሌላ ቅጣት በመወሰን ፈንታ እንዳስፈላጊነቱ አንዱን ወይም ሁለቱንም ወገኖች በመገሰጽ ወይም በማስጠንቀቅ ሊያልፋቸው ይችላል።

በሰው አካልና ጤንነት ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ደረጃ ለማውጣት የተለያዩ መስፈርቶች ሊታዩ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል የወንጀሉ አፈጻጸም፣ የተፈጸመበት አላማ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁንና ለምሳሌ ከቁጥር 555 ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው እንደነገሩ ሁኔታና እንደወንጀሉ ከባድነት ቅጣቱ እንደሚወሰን ነው። ከዚህ አንጻር የወንጀል አፈጻጸሙ፣ የተፈጸመበት አላማ ወዘተ በጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች ውስጥ የሚታዩ ስለሆነ ጎልቶ የሚወጣውና የሚቀረው የደረሰው ጉዳት መጠን ነው። ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ሌሎች ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከጉዳቱ መጨመር ጋር በተያያዘ ቅጣቱም እንደሚጨምር ነው። ስለሆነም የደረሰውን ጉዳት ለመለካት በሚያስችል መልኩ ከዝቅተኛ ከባድ የአካል ጉዳት እሰከ ከፍተኛ ከባድ የአካል ጉዳት በመዘርዘር ደረጃውን ለማውጣት ተሞክሯል። ከዚህ በተጨማሪ ጥፋተኛው የሙያ ግዴታ ወይም

ሀላፊነት እያለበት የደረሰ ጉዳት ከሆነ ቅጣቱን ሊያከብድ በሚችል መልኩ ደረጃውን ለማውጣት ተሞክሯል።[29] በዚህም መሰረት ደረጃው እንደሚከተለው ነው።

<u>ለቁጥር **555** የተዘጋጀ የወንጀል ደረጃዎች</u>

ታስቦ ለሚፈፀሙ ከባድ የአካል ጉዳት የተደነገገው ቅጣት በሁለት የተከፈለ ነው። የወንጀሉ አፈፃፀም አደገኛ ሲሆንና የደረሰው ጉዳት ክብደት አሳሳቢ ሲሆን፣ ወንጀለኛው ከአንድ አመት እስከ አስራ አምስት አመት የሆነ ፅኑ እስራት ይጠብቀዋል። የወንጀሉ ክብደትና የጉዳቱ መጠን በጣም አሳሳቢ ያልሆነ ክብደት ያለው ሲሆን& ወንጀሉ ከባድ ተብሎ የሚመደብ ቢሆንም ከአንድ አመት እስከ ሶስት አመት ቀላል እስራት ያስቀጣል። ይህንን መሰረት በማድረግ ደረጃዎቹ እንደሚከተለው ወጥተዋል።

ለቁጥር 555 የተዘጋጀ የወንጀል ደረጃ፣

1. ደረጃ 1፣
    - ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣
2. ደረጃ 2፣
    - አንዱን አካል ያጎደለ ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
3. ደረጃ 3፣
    - አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
4. ደረጃ 4፣
    - መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
5. ደረጃ 5፣
    - በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
6. ደረጃ 6፣
    - የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም
    - ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣

[29] ከ555-560 ላሉት የወንጀል ድንጋጌዎች የቅጣት አወሳሰን ጥናት ያጠኑት አጥኚ የወንጀል ደረጃውን ለመወሰን በወንጀል ድንጋጌው ያሉትን ፍሬነገሮችና በጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ያሉትን ምክንያቶች በማጣመር የወንጀል ደረጃዎችን አዘጋጅተዋል። ይሁንና የወንጀል ህጉ አቀማመጥ በመጀመሪያ ማክበጃ ምክንያቶችን አይተን ከማክበዳችን በፊት መነሻ ቅጣት መወሰን እንዳለብን የሚያመለክት ነው። ስለሆነም የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት በጠቅላላ ማክበጃዎች ውስጥ ያሉትን ምክንያቶች ባላካተተ መልኩ በዚህ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

7. ደረጃ 7፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣

ለቁጥር 556 (ታስቦ የተደረገ ቀላል የአካል ጉዳት) የተዘጋጀ የወንጀል ደረጃ፣

የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 556 ታስቦ የሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳትን ይመለከታል። እንደዚህ ዓይነቱ የአካል ጉዳት በሁለት የተከፈለ ነው። በሕጉ አንቀፅ ንኡስ ቁጥር "1" በገንዘብ ወይም በእስራት የሚያስቀጣ ሲሆን፣ መነሻ ቅጣቱ ከስድስት ወር በታች ነው። የዚህ አንቀፅ ንኡስ ቁጥር 2 ግን ወንጀለኛው ወንጀሉን በመፈፀም የተጠቀመበት ቁሳቁስ፣ አደገኛነት የተጣለበትን ሓላፊነት ወይም የተጎጂው ደካማነት መሰረት በማድረግ ጉዳቱ ቀላል ቢሆንም ቅጣቱ እጅግ ቢያንስ በ 6 ወር ቀላል እስራት ሆኖ እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ያስቀምጣል። የወንጀል ጥፋቱ በዚህ ክፍል ለመመደብ ሕጉ ሶስት መመዘኛዎችን በአማራጭ አስቀምጧል። እነርሱም፣

ሀ. ወንጀለኛው ጉዳቱን ያደረሰው በመርዝ ወይም በገዳይ መሳሪያ ወይም የአካል ጉዳት
ለማድረስ በሚችል በማናቸውም ሌላ መሳሪያ እንደሆነ፣

ለ. የሙያ ወይም ሌላ ግዴታን በመተላለፍ በመጣስ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣

ሐ. ጉዳት የደረሰበት ሰው ደካማ፣ በሽተኛ ወይም ራሱን ለመከላከል የማይችል እንደሆነ
የሚሉ ናቸው።

ስለሆነም በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች መሰረት በማድረግ ደረጃዎቹ እንደሚከተለው ተዘጋጅተዋል።

1. ደረጃ 1፣
    - የደረሰው ጉዳት በ 555 ውስጥ የማይወድቅ ቀላል ጉዳት ከሆነ፣
2. ደረጃ 2፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፣
3. ደረጃ 3፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሁለቱ ተሟልቶ ከተገኘ፣
4. ደረጃ 4፣
    - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሶስቱም ተሟልቶ ከተገኘ፣

ለቁጥር 558 የተዘጋጁ ደረጃዎች

በቁጥር 558 የህሊና ሁኔታው ከ 555 ልዩ ከመሆኑ በስተቀርና በዚህም ምክንያት ቅጣቱ ቀላል እንደሚሆን ከሚያስቀምጥ በስተቀር ደረጃዎቹ ተመሳሳይ ስለሚሆኑ፣ በድጋሚ የቁጥር 555 ደረጃዎች ለ 558 ትም ይሰራሉ።

ለቁጥር 558 የተዘጋጀ የወንጀል ደረጃ፣

i. ደረጃ 1፣
   - ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣
ii. ደረጃ 2፣
   - አንዱን አካል ያጎደለ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
iii. ደረጃ 3፣
   - አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
iv. ደረጃ 4፣
   - መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
v. ደረጃ 5፣
   - በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
vi. ደረጃ 6፣
   - የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
vii. ደረጃ 7፣
   - ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣

ቁጥር 559. (በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ)

በንኡስ ቁጥር 1 ቀላል የአካል ጉዳትን በተመለከተ እራሱን ችሎ በ 556 እንደተመለከተው አንድ ደረጃ ይሆናል።

ደረጃ 1

በንኡስ ቁጥር 2 የተመለከተው የወንጀሉ አይነት በቁጥር 555 ከተመለከተው ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ የወንጀል ደረጃዎቹም ተመሳሳይ ይሆናሉ።

ለቁጥር 559(2) የተዘጋጀ የወንጀል ደረጃ፣

1. ደረጃ 1፣
   - ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣

2. ደረጃ 2፣
   - አንዱን አካል ያጎደለ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
3. ደረጃ 3፣
   - አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
4. ደረጃ 4፣
   - መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
5. ደረጃ 5፣
   - በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
6. ደረጃ 6፣
   - የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም
   - ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣
7. ደረጃ 7፣
   - ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣

560 (እጅ እልፊት)

ከ 3 ወር የማይበልጥ ወይም ከ 300 ብር የማይበልጥ ቅጣት

1. መቀጮ ሲሆን ብር 10 አድርጎ እንደማከበጃ ይወሰናል።
2. የእስር ቅጣት ከሆነ ደግሞ 10 ቀን ብሎ ይጀምራል ማለት ነው።

i. <u>ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ መነሻና መድረሻ ቅጣት፣</u>

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ስራ በእያንዳንዱ ደረጃ ለተቀመጠው የወንጀል ደረጃ መነሻና መድረሻ ቅጣት ማስቀመጥ ነው።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አምስቱ ጥናቶች በሰንጠረዥ ላይ የተመሰረተ ሞዴል ቢያቀርቡም፣ ይሁንና በተለያዩ አጥኚዎች ለየብቻ የተዘጋጁ በመሆኑ፣ ከአቀራረቡም ሆነ ከስሌት አንጻር የተለያየ መነሻና ቅርጽ ያላቸው ናቸው። እነዚህን ለእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌ የተዘጋጁትን ሰንጠረዦች ይዞ መቀጠል ይቻላል። ይሁንና በእያንዳንዱ አቀራረብ መካከል ያለው ልዩነት መሰረታዊ ባለመሆኑ፣ ለእያንዳንዱ የተለያየ ቅርጾችንና ስሌቶችን ማዘጋጀት ስራውን አድካሚ ለአፈጻጸምም አስቸጋሪ

መሆኑ አይቀርም። ስለሆነም ለእያንዳንዱ የተለያየ ሰንጠረዥ ከመጠቀም ለሁሉም አንድ የቅጣት ሰንጠረዥ በማዘጋጀት መጠቀምም ይቻላል።

አንድ ሰንጠረዥ መጠቀም በመቻሉ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል።

1. ለእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌ ራሱን የቻለ ሰንጠረዥ የማዘጋጀት ድካምን ያቀላል። በአሜሪካ አንድ የቅጣት ሰንጠረዥ ተዘጋጅቶ ሁሉም የወንጀል አይነቶች ወደዚህ ሰንጠረዥ እንዲያመለክቱ በማድረግ በተሰራው አይነት ይሆናል ማለት ነው።
2. በሁሉም ወንጀሎች ተመሳሳይ የቅጣት መነሻ ያላቸው ተመሳሳይ የቅጣት ሬንጅ ይኖራቸዋል። ስለሆነም በአንድ የወንጀል ድርጊት ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ የቅጣት ደረጃ ላይ ሊቀመጡ በሚገባቸው የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች መካከልም ወጥነትን ለማረጋገጥ ያስችላል።
3. በተመሳሳይ ደረጃ ላሉት የወንጀል ድርጊቶች ተመሳሳይ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ መጠን መጠቀም የሚያስችል ስለሚሆን ወጥነትን፣ ተመጣጣኝነትን ለማረጋገጥ ይጠቅማል። በእያንዳንዱ የቅጣት መነሻም ሆነ በማክበጃም ሆነ በማቅለያ የተቀመጡት መነሻና መድረሻቸው ቢቀመጥም እያንዳንዱ ሬንጅ ስላለው በዚሁ ውስጥ ዳኛው መንሸራሸር የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።
4. ወደፊት የሚዘጋጁ የቅጣት መመሪያዎችም ራሱን የቻለ ሰንጠረዥ ማዘጋጀት ሳያስፈልጋቸው፣ ለወንጀሉ የተለያዩ ደረጃዎችን ብቻ በማውጣት አንዱን ሰንጠረዥ መጠቀም ስለሚቻል ወደፊት የሚሰሩትን ስራዎች ያቀላቸዋል።

ከእነዚህ ምክንያቶች በመነሳት ለሁሉም የወንጀል ድርጊቶችና ደረጃዎች ሊያገለግል የሚችል የቅጣት መነሻና መድረሻ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ሊያሳይ የሚችል ሰንጠረዥ ተዘጋጅቷል።

ሰንጠረዡ በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ውስጥ ያሉትን የቅጣት መነሻና መድረሻ የተለያዩ ደረጃዎችን በማውጣት ዳኞች በቅጣት አወሳሰን ተመሳሳይና ተቀራራቢ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የሚያስችል ነው። ስለሆነም የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ካስቀመጡት መነሻና መድረሻ ቅጣት ሳይወጣ፣ ይሁንና የቅጣት አወሳሰኑ ወጥነትና ተመሳሳይነት እንዲሁም ተመጣጣኝነት እንዲኖረው የሚያደርግ ስለሚሆን የወንጀል ህጉን ክፍተት የሚያሟላ እንጂ ከወንጀል ህጉ ማእቀፍ ውጭ የሚሆን አይሆንም።

<u>ነጻነትን የሚያሳጡ ወይም የእስራት ቅጣትን በተመለከተ ሰንጠረዥ</u>

በዚህ ሰነድ በአንድ የወንጀል ድርጊት የቅጣት መነሻና መድረሻዎችን የያዘ ከዝቅተኛው የቅጣት መነሻ (የግዴታ ስራ) እስከ ከፍተኛው የቅጣት መድረሻ (የሞት ቅጣት) ድረስ የያዘ የቅጣት ደረጃዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ተዘጋጅቷል።

ሰንጠረዡ ሲዘጋጅ ቅጣት ሲቀል ከሚደርስበት ዝቅተኛ የቅጣት ማቅለያን ሊያሳይ በሚችል መልኩ የተዘጋጀ ነው። ምክንያቱም ቅጣቱ ሲቀል የሚደረስበትንም ደረጃ ሰንጠረዡ ሊያሳይ ስለሚገባ ነው።

በሰንጠረዡ የቅጣት መነሻው ደረጃ በደረጃ እያደገ እንዲሄድ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለዳኛው ቀድሞ የነበረውን ሰፊ ፍቅድ ያጠበዋል ስለሆነም የተለያዩ ዳኞች በተቀራራቢና ተመሳሳይ ወንጀሎች ላይ የሚሰጡት የቅጣት ውሳኔ ተቀራራቢነት ይኖረዋል ማለት ነው።

ሰንጠረዡ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ነው።

1. በመነሻውና በመድረሻው መካከል ቢያንስ የ3 ወር ሬንጅ እንዲኖር ሆኖ ተዘጋጅቷል። (በተለይ ከአንድ አመት በታች ለሚጀምሩ ቅጣቶች መነሻው እራሱ ዝቅተኛ ስለሆነ በተነጻጸሪ ዝቅተኛ ሬንጅ (ፍቅድ) ለዳኛው መተው ምክንያታዊ ነው ከሚል መነሻ ነው።)

2. የቅጣቱ መነሻ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ሬንጁን በሶስት ወር መጠበቅ ከሚገባው በላይ የሚያጠበው ስለሚሆን፣ ከደረጃ 12 ጀምሮ በ6 ወር እንዲሆን ተደርጓል።

3. አሁንም የቅጣቱ መነሻ እየጨመረ ሲሄድ ከዚሁ ጋር ተጣጥሞ ሬንጁ መስተካከል ስለሚኖርበትና ያለአግባብ እንዳይጠብ ከደረጃ 16 ጀምሮ ሬንጁን ለመወሰን ከመነሻው 20 በመቶ በመጨመር ጣሪያው ተወስኗል።

4. የየደረጃው መነሻ ሲቀመጥ የሚቀጥለው መነሻ ከእሱ በፊት የነበረው ማእከላዊ ዋጋ መነሻ እንዲሆን ተደርጓል። ለምሳሌ የደረጃ 12 የቅጣት መነሻና መድረሻ ከ2 አመት እስከ 2 አመት ከ6 ወር ቢሆን፣ የደረጃ 13 የቅጣት መነሻ የዚህ አማካይ የሆነው 2 አመት ከ3 ወር ይሆናል ማለት ነው።

5. በወንጀል ህጉ ቅጣቱ ከመነሻው እንደሚጀምር የተቀመጠ ስለሆነ፣ ለስሌቱ እንዲቀል የዝቅተኛው ደረጃ አማካዩ ብዙውን ጊዜ በወንጀሉ ከተቀመጡት መነሻዎች (1 አመት፣ 3 አመት፣ 5 አመት፣ 7 አመት፣ 10 አመት፣ 15 አመት) ጋር ያልተራራቀ በሆነ ጊዜ እነዚህ የደረጃው መነሻዎች እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ይህ አይነት የቅጣት ሰንጠረዥ በዩኤስ አሜሪካ ካለው የቅጣት ሰንጠረዥ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይሁንና በአሜሪካው ግሪድ ሲስተም ለወንጀል ሪከርድ እራሱን የቻለ ትኩረት ስለሚሰጠው እንደሪከርዱ መጠን የቅጣት መጠኑ ወደጎን የሚያድግ ሆሪዞንታል ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፣ ይሁንና በእኛ አገር የወንጀል ሪከርድ እንደማንኛውም የወንጀል ማክበጃ የሚታይ ስለሆነ፣ ወንጀሉን በተመሳሳይ ሊያከብድ ይችላል በሚል ወደጎን ያለውን የወንጀል ሪከርድ ሰንጠረዥ ማስቀመጥ አስፈላጊ አልሆነም።

በወንጀል ህግ ቁጥር 179 መነሻቸው 10 ቀን የሆነ የቀላል እስራት ቅጣት ቅጣቱ ሲቀል ወደግዴታ ስራ ወይም መቀጮ እንደሚቀየር ይደነግጋል። ይሁንና ወደግዴታ ስራ ሲቀየር የስንት ቀን ስራ እንደሚሆን፣ መቀጫውስ ስንት እንደሚሆን ግልጽ አይደለም። ስለሆነም ለዚህ ተመጣጣኝ የሆነ ስሌት ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። በወንጀል ህጉ ቁጥር 103(1) እስከ 6 ወር የሚደርስ ቀላል እስራት እስከ 6 ወር በሚደርስ የግዴታ ስራ ሊወሰድ እንደሚችል ስለሚያስቀምጥ፣ ለዚህ ማንዋል አላማ የአንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን የግዴታ ስራ ጋር ተመጣጣኝ ተደርጎ ተወስዷል። ስለሆነም ለምሳሌ የእስራት ቅጣቱ በማቅለያ

ምክንያት የሚቀነስ ከሆነ ተቀንሶ በተደረሰበት የእስራት ቀናት ልክ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ሊወሰን ይችላል ማለት ነው። ሰንጠረዡም በዚህ መልኩ ነው ተዘጋጅቶ የቀረበው።

ይሁንና የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ፣ የ6 ወር እስርን ወደመቀጮ ሲቀየር ስንት ይሆናል? ለሚለው ምላሽ ማግኘት ይፈልጋል። በወንጀል ህጉ ቁጥር 90(2) ቅጣቱ በእስራት ብቻ የተቀመጠ ከሆነና ተቀጪው የህግ ሰውነት ያለው ከሆነ እስራቱ ወደቅጣት እንደሚቀየር ያመለክታል። ለዚህም የ5 አመት ቀላል እስራት በብር 10000 እንደሚቀየር ያመለክታል። 5 አመት ቀላል እስራትና ብር 10000 መቀጮ ተመጣጣኝ ተደርገው በህጉ ከተወሰዱ፣ ከዚህ በመነሳት የ6 ወር ቀላል እስራት በገንዘብ ሲገመት ብር 1000 ይሆናል። ስለሆነም የ6 ወር ቀላል እስራት ወደ 1000 ብር የገንዘብ መቀጮ ቢቀየር በህጉ ከተቀመጠው ንጽጽር ጋር ተመሳሳይ ይሆናል። ስለሆነም ከ6 ወር ያልበለጠ ቀላል እስራት በማቅለያ ምክንያት ወደመቀጮ ሲቀየር የሚደረስበትን የመቀጮ መጠን፣ በማቅለያ ከሚደረስበት ቀላል የእስራት ጊዜ ጋር በማነጻጸር በሰንጠረዡ ውስጥ እንዲታይ ተደርገዋል።

ከዚህ በመነሳትም በ39 ደረጃዎች የተከፋፈለ የቅጣት ሰንጠረዥ ተዘጋጅቷል።

<u>ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች ደረጃዎች ሰንጠረዥ</u>		
ደረጃ 1	ከ1 ቀን-20 ቀን የግዴታ ስራ	ከ1 ብር- 100 ብር
ደረጃ 2	ከ10 ቀን-3 ወር ወይም ከ10 ቀን-3 ወር የግዴታ ስራ	ከ 50 ብር - 500 ብር
ደረጃ 3	ከ2 ወር - 5 ወር ወይም ከ2 ወር-3 ወር የግዴታ ስራ	ከ300 ብር- 800 ብር
ደረጃ 4	ከ4 ወር- 7 ወር	(የተጣለው ቅጣት ከስድስት ወር በታች ከሆነ በቀኑ ልክ ወደግዴታ ስራ ወይም እስከ ብር 1000 መቀጮ ሊቀየር ይችላል)
ደረጃ 5	ከ6 ወር-9 ወር	
ደረጃ 6	ከ8 ወር-1 አመት	

ደረጃ 7	ከ1 አመት-1 አመት ከ3 ወር	ከዚህ ጀምሮ ሬንጁን ለመወሰን ጣሪያው ከመነሻው በ25 በመቶ እንዲያድግ ተደርጓል።
ደረጃ 8	ከ1 አመት ከ2 ወር-1 አመት ከ6 ወር	
ደረጃ 9	ከ1 አመት ከ4 ወር -1 አመት ከ8 ወር	
ደረጃ 10	ከ1 አመት ከ6 ወር-1 አመት ከ10 ወር	
ደረጃ 11	ከ1 አመት ከ8 ወር-2 አመት ከ2 ወር	
ደረጃ 12	ከ2 አመት - 2 አመት ከ6 ወር	
ደረጃ 13	ከ2 አመት ከ3 ወር-2 አመት ከ9 ወር	ከዚህ ጀምሮ ሬንጁ በስድስት ወር ውስጥ እንዲቆይ ተደርጓል።
ደረጃ 14	ከ2 አመት ከ6 ወር-3 አመት	
ደረጃ 15	ከ2 አመት ከ9 ወር-3 አመት ከ3 ወር	
ደረጃ 16	ከ3 አመት - 3 አመት ከ7 ወር	ከዚህ ጀምሮ ሬንጁ በ20 በመቶ እያደገ እንዲሄድ ተደርጓል፣
ደረጃ 17	ከ3 አመት ከ3 ወር-3 አመት ከ11 ወር	
ደረጃ 18	ከ3 አመት ከ7 ወር- 4 አመት ከ4 ወር	
ደረጃ 19	ከ4 አመት- ከ4 ወር ከ10 ወር	
ደረጃ 20	ከ4 አመት ከ5 ወር-5 አመት ከ4 ወር	
ደረጃ 21	ከ5 አመት - 6 አመት	
ደረጃ 22	ከ5 አመት ከ6 ወር-6 አመት ከ7 ወር	
ደረጃ 23	ከ6 አመት- 7 አመት ከ2 ወር	

ደረጃ 24	ከ6 አመት ከ6 ወር- 7 አመት ከ8 ወር	
ደረጃ 25	ከ7 አመት- 8 አመት ከ4 ወር	
ደረጃ 26	ከ7 አመት ከ8 ወር- 9 አመት ከ2 ወር	
ደረጃ 27	ከ8 አመት ከ5 ወር- 10 አመት	
ደረጃ 28	ከ9 አመት - 10 አመት ከ10 ወር	
ደረጃ 29	ከ10 አመት- 12 አመት	
ደረጃ 30	ከ11 አመት- 13 አመት ከ2 ወር	
ደረጃ 31	ከ12 አመት- 14 አመት ከ5 ወር	
ደረጃ 32	ከ13 አመት- 15 አመት ከ8 ወር	
ደረጃ 33	ከ14 አመት- 16 አመት ከ10 ወር	
ደረጃ 34	ከ15 አመት - 18 አመት	
ደረጃ 35	ከ16 አመት ከ6 ወር - 19 አመት ከ 6 ወር	
ደረጃ 36	ከ18 አመት - 21 አመት ከ8 ወር	
ደረጃ 37	ከ20 አመት - 25 አመት	
ደረጃ 38	ከእድሜ ልክ እስራት- የሞት ቅጣት	
ደረጃ 39	የሞት ቅጣት	

በገንዘብ የሚወሰን መቀጮን በተመለከተ የተዘጋጀ ሰንጠረዥ

በወንጀል ህጉ የተወሰኑ የወንጀል ድርጊቶች በመቀጮ ብቻ ወይም በመቀጮና በእስራት ወይም በአማራጭ መቀጮን ወይም እስራትን ሊቀጡ እንደሚችሉ ይደነግጋል። ከዚህ አንጻር በተለያየ ደረጃ ለሚገኙት የወንጀል አፈጻጸሞች እንደወንጀሉ ክብደት የመቀጮው መጠንንም ማስቀመጥ ይጠይቃል።

በወንጀል ህጉ ቁጥር 90(2) እንደተመለከተው የገንዘብ መቀጮን ለመወሰን፣

1. የወንጀሉ ክብደት
2. የአደገኛነት መጠን፣
3. የህብቱን ሁኔታ፣
4. የገቢ ምንጩን
5. ስለቤተሰቦቹ አስተዳደር ያለበትን ሸክም
6. እድሜውን
7. ጤንነቱን

ከግምት ባስገባ መልኩ ሊወሰን እንደሚገባ ያስቀምጣል።

በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተመለከቱት የእስራት ቅጣቱንም ለመወሰን በመስፈርትነት ስለተቀመጡ የወንጀሉን ደረጃ መሰረት ባደረገ መልኩ መቀጮው እንደሚያደግ መገመት ይቻላል። ከዚህ አንጻር የመቀጫ ቅጣቱን መጠን ለመወሰን በተመሳሳይ መጠቀም ይቻላል።

ከተራ ቁጥር 3 ጀምሮ ያሉት ከወንጀል አፈጻጸሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሳይሆን፣ የአጥፊውን አጠቃላይ ሁኔታ መሰረት አድርገው ስለሆነ፣ እነዚህን መሰረት አድርጎ ዳኛው መቀጮውን እንዲወስን የተቀመጡ መስፈርቶች ናቸው።

ስለሆነም በተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ልክ እንደእስራት ቅጣቱ ተመሳሳይ ጣሪያ ማስቀመጥ የሚቻል ሲሆን፣ ይሁንና ከተራ ቁጥር 3 ጀምሮ ያሉት ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ፣ ዝቅተኛውን መነሻ ለማስቀመጥ አያስችልም። በወንጀል ህጉ ቁጥር 98(3) ሊነኩ የማይገባቸው ሀብቶች እንዳሉ ተመልክቷል። ስለሆነም ምንም ከፍተኛና አደገኛነት ያለው ወንጀል ቢፈጽምም፣ እንደገቢው ሁኔታ መቀጮ እንዲከፍል የማይገደድበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው። ስለሆነም ዝቅተኛውን መነሻ መወሰን ባይቻልም፣ ከፍተኛውን ጣሪያ ግን መወሰን ይቻላል። ስለሆነም ጣሪያውን ብቻ ስለሆነ ጣሪያውን መሰረት አድርጎ ደረጃዎች እንዲዘጋጁ ተደርጓል።

ከዚህ በተረፈ የእድሜው፣ የጤንነቱንና ስለቤተሰቦቹ ያለበትን የአስተዳደር ሸክም ዳኛው ከግምት በማስገባት ከተቀመጠው ጣሪያ ሳያልፍ መጠኑን ዝቅ በሚችል መልኩ ቢተው ከዚህ በመነሳት ዳኛው መቀጮውን ሊወስን ይችላል ማለት ነው። በዚህ መሰረት የገንዘብ መቀጮ ከዝቅተኛው ጣሪያ 1000 ብር እስከ ብር 100 ሺህ ሊደርስ በሚችል መልኩ ተዘጋጅቷል።[30]

<u>የገንዘብ መቀጮን የሚመለከት ሰንጠረዥ</u>		
ደረጃ	የገንዘብ መቀጮው ጣሪያ	
ደረጃ 1	እስከ 1000	
ደረጃ 2	እስከ 2000	
ደረጃ 3	እስከ 3000	
ደረጃ 4	እስከ 5000	
ደረጃ 5	እስከ 7000	
ደረጃ 6	እስከ 10000	
ደረጃ 7	እስከ 20000	
ደረጃ 8	እስከ 30000	
ደረጃ 9	እስከ 40000	
ደረጃ 10	እስከ 50000	

[30] በወንጀል ህጉ 90(1) መቀጮ የህግ ሰውነት በሚሆን ጊዜ እስከ ብር 500 ሺህ እንደሚደርስ ቢያስቀምጥም፣ የህግ ሰውነት ያላቸውን በተመለከተ እስከ ብር 500 መቼ ሊቀጡ እንደሚገባ በወንጀል ህጉ 90(3) በዝርዝር የተመለከተ ስለሆነ፣ የተፈጥሮ ሰው ግን የሚቀጣው በወንጀል ህጉ ዝርዝር ላይ እንዳለው ከፍተኛው ብር 100 ሺህ ስለሆነ ደረጃው የተዘጋጀው እስከ ብር 100 ሺህ ላለ መቀጮ ነው።

ደረጃ 11	እስከ 75000	
ደረጃ 12	እስከ 100000	
ደረጃ 13	እስከ 125000	
ደረጃ 14	እስከ 150000	
ደረጃ 15	እስከ 200000	
ደረጃ 16	እስከ 250000	
ደረጃ 17	እስከ 300000	
ደረጃ 18	እስከ 350000	
ደረጃ 19	እስከ 400000	
ደረጃ 20	እስከ 500000	

ii. <u>ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ መነሻና መድረሻ ቅጣት፣</u>

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ስራ በእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌዎች ለተቀመጡት የተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች መነሻና መድረሻ ቅጣት ማስቀመጥ ነው።

የወንጀል ህጉ ሁለተኛ ታላቅ ክፍል ልዩ ክፍል ለእያንዳንዱ ወንጀል ተብለው ለተደነገጉ ድርጊቶች መነሻና መድረሻ ጣሪያ ቅጣት አስቀምጧል። ስለሆነም በድንጋጌው ውስጥ ከሚወድቁ የወንጀል ደረጃዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኘው በህጉ የተቀመጠውን መነሻውን ቅጣት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ምክንያቱም ዝቅተኛ ደረጃ የሆነው እሱ ስለሆነና፣ ህጉም ከዚያ መጀመር እንደሚቻል ስላመለከተ ነው።

በሌላ በኩል በወንጀል ህጉ የቅጣት ጣሪያው የተቀመጠ ሲሆን በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከቱት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎች ቢኖሩም በህጉ ከተቀመጠው ጣሪያ ማለፍ እንደማይቻል ያስቀምጣል። ስለሆነም በህጉ የተቀመጠው ጣሪያ ላይ የሚደረሰው ማክበጃዎች ሁሉ ተሟልተው ሲገኙ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ተገቢ ነው። በህጉ ጠቅላላ ማክበጃዎች ተብለው

የተዘረዘሩት በአምስት ንኡሳን ድንጋጌዎች ተካተው የቀረቡ ስለሆነ፣ አምስት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ጣሪያው ላይ ለመድረስ በሚያስችል መልኩ በወንጀሉ ድንጋጌ ጣሪያ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን የሰንጠረዡ እርከን በመውሰድ፣ ከዚህ ከፍተኛ እርከን አምስት እርከን ወደታች ወርዶ በወንጀል ድንጋጌው ከፍተኛ ደረጃ ለተሰጠው የወንጀል ደረጃ መነሻ ማድረግ ምክንያታዊ ይሆናል። በዚህ መልኩ ወንጀል አድራጊው በህጉ የተመለከተው ጣሪያ ቅጣት ላይ ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታን፣ ከህግ አውጪው አላማ ጋር በሚጣጣም መልኩ መፍትሄ የሚያስቀምጥ ስለሚሆን ነው።

ስለሆነም በድንጋጌው ዝቅተኛው የወንጀል ደረጃና ከፍተኛው የወንጀል ደረጃ የሚያርፉበት ከታወቀ፣ በእነዚህ መሀከል ያሉት የተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች በቁጥራቸው ልክ ከመነሻው እስከ መድረሻው ያለውን የቅጣት ዘመን በማካፈል ደረጃቸውን መወሰን ይቻላል። በተቻለ መጠን በየደረጃው መካከል የሚኖረው ልዩነት እኩል እርከን ለማድረግ ያስችላል። ይህንን ለማድረግ የማይቻል በሆነ ጊዜ፣ ወደከፍተኛው በተጠጉት የወንጀል ደረጃዎች መካከል ያለውን የእርከን ልዩነት በመጨመር በማጠጋጋት ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ መነሻና መድረሻ ማስቀመጥ ይቻላል። ስለሆነም ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ ይህንን መስፈርት ወይም መለኪያ መሰረት በማድረግ የቅጣት ደረጃቸው ተወስኗል።

የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተም ለወንጀሉ ድርጊት ከተቀመጠው ጣሪያ ሳይበልጥ በድንጋጌው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ወንጀል አድራጊ እስከመቀጮው ጣሪያ እንዲከፍል ሊወሰንበት እንደሚችል የተቀመጠ ሲሆን፣ የወንጀል ደረጃው ዝቅ እያለ በሄደ ቁጥርም የገንዘብ መቀጮ ጣሪያውም በዚያው መልክ እየቀነሰ እንዲሄድ በማድረግ ደረጃው ተወስኗል።

የወንጀል ህጉ ድንጋጌ	የወንጀሉ ደረጃ	**የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ**	የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን	የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን
በስልጣን አለአግባብ መገልገል				
407(1)				
	ደረጃ 1	ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣	7	2
	ደረጃ 2	ዝቅተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣	10	3
	ደረጃ 3	• ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/ በችግር፣ ወይም • መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣	13	4
	ደረጃ 4	• ዝቅተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣ ወይም	16	5

		• መካከለኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣		
	ደረጃ 5	መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት/በችግር፣	19	6
	ደረጃ 6	መካከለኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣	23	6
407(2)				
	ደረጃ 1	• ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ ወይም • ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣	25	7
	ደረጃ 2	• ከፍተኛ ስልጣን፣ ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ፣ ወይም • ዝቅተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በአፍቅሮ ንዋይ	26	8
	ደረጃ 3	• ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣ • መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣	27	9
	ደረጃ 4	• ከፍተኛ ስልጣን፣ መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣ • መካከለኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣	28	10
407(3)		•		
	ደረጃ 1	• ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ በችግር፣	29	11
	ደረጃ 2	• ከፍተኛ ስልጣን፣ ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣	32	12
ስርቆት				
665				
	ደረጃ 1	ከብር 100- 1000	2	
	ደረጃ 2	ከብር 1000-2000	4	
	ደረጃ 3	ከብር 2000-4000	6	
	ደረጃ 4	ከብር 4000-10000	8	
	ደረጃ 5	ከብር 10000-50000	10	
	ደረጃ 6	ከብር 50000-100000	12	
	ደረጃ 7	ከብር 100000 በላይ	14	
669				

	ደረጃ 1	እስከ ብር 1000 ሆኖ በ669 የተመለከተው አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣	7	
	ደረጃ 2	እስከ ብር 1000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 2000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣	9	
	ደረጃ 3	እስከ 1000 ሆኖ ሶስት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 2000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 4000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣	11	
	ደረጃ 4	እስከ 2000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 4000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 10000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልተው ሲገኙ፣	13	
	ደረጃ 5	እስከ ብር 4000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ ብር 10000 ሆኖ ሁለቱ ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 50000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣	15	
	ደረጃ 6	እስከ 10000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 50000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 100000 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣	18	
	ደረጃ 7	እስከ 50000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም እስከ 100000 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም ከብር 100000 በላይ ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፣	21	
	ደረጃ 8	እስከ 100000 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም ከ100000 በላይ ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣	24	
	ደረጃ 9	ከብር 100000 በላይ ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣	27	

የማታለል ወንጀል				
692				
	ደረጃ 1	ከብር 100 እስከ ብር 1000	2	1
	ደረጃ 2	ከብር 1000-2000	4	1
	ደረጃ 3	ከብር 2000-4000	6	2
	ደረጃ 4	ከብር 4000-10000	8	3
	ደረጃ 5	ከብር 10000-50000	10	3
	ደረጃ 6	ከብር 50000-100000	12	4
	ደረጃ 7	ከብር 100000 በላይ	14	4
693(1)				
	ደረጃ 1	ከብር 100 እስከ ብር 1000	2	1
	ደረጃ 2	ከብር 1000-2000	5	1
	ደረጃ 3	ከብር 2000-4000	8	2
	ደረጃ 4	ከብር 4000-10000	11	3
	ደረጃ 5	ከብር 10000-50000	14	4
	ደረጃ 6	ከብር 50000-100000	18	5
	ደረጃ 7	ከብር 100000 በላይ	22	6
693(2)				
	ደረጃ 1	በቸልተኝነት የተፈጸመ ማታለል	2	2
የውንብድና ወንጀል				
670				
	ደረጃ 1	ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም እስከ ብር 2000 የሆነ እንደሆነ፣	7	
	ደረጃ 2	• ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት	9	

		ተግባር ወይም የህይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 የሆነ እንደሆነ		
	ደረጃ 3	• የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የህይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣	11	
	ደረጃ 4	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2000-10000 ከሆነ፣	13	
	ደረጃ 5	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 10000-30000 ከሆነ፣	15	
	ደረጃ 6	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተፈጸመው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ፣ • በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 30000-100000 ከሆነ፣	18	
	ደረጃ 7	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ	21	

		ከብር 300 ሺህ እስከ 1 ሚሊዮን ብር ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000-300000 ከሆነ፣		
	ደረጃ 8	• ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣	24	
	ደረጃ 9	• ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1000000 በላይ ከሆነ፣	27	
671(1)				
	ደረጃ 1	ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 2000 የሚደርስ እንደሆነ፣	21	
	ደረጃ 2	• ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ እገልህለሁ ብሎ ያስፈራራ፣ ለዚህም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘቡ መጠን እስከ ብር 2000 የሚደርስ እንደሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 2000-10000 የሚደርስ እንደሆነ፣	22	
	ደረጃ 3	• የጦር መሳሪያ ይዞ ያስፈራራ ለዚህም እገልህለሁ ብሎ ያስፈራራ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 2000 የሆነ እንደሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣	23	
	ደረጃ 4	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 10000-30000 ከሆነ ወይም፣	24	

		• ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 2000-10000 ከሆነ፣		
	ደረጃ 5	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 30000-100000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 10000-30000 ከሆነ፣	25	
	ደረጃ 6	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000-300000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 30000-100000 ከሆነ፣	26	
	ደረጃ 7	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1000000 በላይ ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 300000-1000000 ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100000-300000 ከሆነ፣	27	
	ደረጃ 8	• ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100000 በላይ ከሆነ ወይም፣ • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 300000-1000000 ከሆነ፣	29	
	ደረጃ 9	• ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1000000 በላይ ከሆነ፣	31	
671(2)				
	ደረጃ 1	ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሣሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሣሪያ በመያዝ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን የተጠቀመ ወይም የተፈፀመው	38	

		ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፣		
	ደረጃ 2	• በጦር መሣሪያ አማካይነት በልማደኛነት በቡድን የሚፈፀም ውንብድና	39	
		በሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት ማድረስ		
555				
	ደረጃ 1	ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣	7	
	ደረጃ 2	• አንዱን አካል ያጎደለ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	10	
	ደረጃ 3	• አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	13	
	ደረጃ 4	• መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	16	
	ደረጃ 5	• በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	19	
	ደረጃ 6	• የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	23	
	ደረጃ 7	• ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ	27	

		ያለበት ከሆነ፣		
557[31]	በቁጥር 557 ያለው ማቅለያ ተሟልቶ በሚገኝበት ጊዜ ለ555 እና ለ556 የቅጣት እርከኖች በሚከተለው መልኩ ይሆናል።			
555				
	ደረጃ 1	ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣	5	
	ደረጃ 2	• አንዱን አካል ያጎደለ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	6	
	ደረጃ 3	• አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	7	
	ደረጃ 4	• መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	8	
	ደረጃ 5	• በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	9	
	ደረጃ 6	• የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	10	
	ደረጃ 7	• ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	11	

[31] በ 557 ያሉት ማቅለያዎች ባሉ ጊዜ ቅጣቱ እንደሚቀል ያስቀምጣል። ሲቀልም ቅጣቱ ከሁለት አመት ያልበለጠ እንዲሁም ከብር 4000 ያልበለጠ መቀጫ እንደሚሆን ያስቀምጣል። ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት የቅጣት ደረጃዎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የቅጣት መነሻቸው እንዲስተካከል ተደርጓል።

556				
	ደረጃ 1	• የደረሰው ጉዳት በ 555 ውስጥ የማይወድቅ ቀላል ጉዳት ከሆነ፣	2	2
	ደረጃ 2	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፣	5	
	ደረጃ 3	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሁለቱ ተሟልቶ ከተገኘ፣	7	
	ደረጃ 4	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሶስቱም ተሟልቶ ከተገኘ፣	9	
557	በ557 ያለው ማቅለያ ተሟልቶ በተገኘ ጊዜ በ556 የሚያስቀጣው ቅጣት እርከን ከዚህ በታች በቀረበው መሰረት ይሆናል።			
556		•		
	ደረጃ 1	• የደረሰው ጉዳት በ 555 ውስጥ የማይወድቅ ቀላል ጉዳት ከሆነ፣	2	
	ደረጃ 2	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፣	3	
	ደረጃ 3	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሁለቱ ተሟልቶ ከተገኘ፣	4	
	ደረጃ 4	• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በድንጋጌው ከተቀመጡት ማክበጃዎች ሶስቱም ተሟልቶ ከተገኘ፣	5	
558				
	ደረጃ 1	• ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣	5	
	ደረጃ 2	• አንዱን አካል ያጎደለ ወይም	6	

		• ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣		
	ደረጃ 3	• አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	6	
	ደረጃ 4	• መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ	7	
	ደረጃ 5	• በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	7	
	ደረጃ 6	• የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	8	
	ደረጃ 7	• ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	9	
559 (1)				
	ደረጃ 1	• ቀላል የአካል ጉዳት	2	1
559(2)				
	ደረጃ1	• ሊድን የሚችል የአካል ጉዳት ያደረሰ፣	5	2
	ደረጃ 2	• አንዱን አካል ያጎደለ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ	6	3

		ያለበት ከሆነ፣		
	ደረጃ 3	• አስፈላጊ ብልቱን ያጎደለ፣ በሽታ እንዲይዘው ያደረገ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	6	3
	ደረጃ 4	• መልኩን ያበላሸ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ	7	4
	ደረጃ 5	• በሰውነቱ ወይም በአእምሮው ለዘወትር ጠንቅ ያተረፈ (ሰርቶ መብላት እንዳይችል ያደረገው) ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 4 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	7	4
	ደረጃ 6	• የተጎጂውን ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም • ድርጊቱ በደረጃ 5 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	8	5
	ደረጃ 7	• ድርጊቱ በደረጃ 6 የተመለከተው ሆኖ ሙያዊ ግዴታ ያለበት ከሆነ፣	9	6
560				
	ደረጃ 1	እጅ እልፊት	2	1

iii. <u>የቅጣት ማክበጃ አሰላልን በሚመለከት፣</u>

በህጉ ላይ እንደተመለከተው፣ ዳኛው በመቀጠል ተግባራዊ እንዲያደርግ የታዘዘው የቅጣት ማክበጃዎች መኖራቸውን መርምሮ በዚህ መሰረት ቅጣቱን እንዲያከብድ ነው። በወንጀል ህጉ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች እያንዳንዳቸው በአምስት በአምስት ንኡሳን ድንጋጌዎች ተከፋፍለው (ተጠቃለው) እናገኛቸዋለን።

ይሁንና በህጉ እንደተመለከተው ቅጣቱ ቢከብድም ለወንጀሉ ከተቀመጠው ጣሪያ[32] እንደማያልፍ አመልክቷል።

ይህም የሚያመለክተው ሁሉም ማክበጃ ሁኔታዎች ተሟልተው ቢገኙ ቅጣቱ ሲከብድ ገደቡ የተቀመጠው ጣሪያ እንደሆነ ነው። ይህ በሌላ አነጋገር ማክበጃ የተባሉት ሁሉም ሁኔታዎች ካልተሟሉ ቅጣቱ ቢከብድም የወንጀል ጣሪያው ላይ ሊደርስ እንደማይችል ነው።

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችል ጥያቄ አለ። እነዚህ በአምስት ንኡሳን ቁጥሮች ውስጥ የተቀመጡት ቅጣት ማክበጃዎች እንዳለ እንደአንድ ማክበጃ ሊወሰዱ ይገባል? ወይስ እያንዳንዱ ምክንያት ለየብቻው እንደአንድ ማክበጃ ምክንያት ሊወሰድ ይገባል? የሚል ነው።

ከዚህ አንጻር የተለያየ ትርጉም ሊቀመጥ ይችላል። አንደኛው ትርጉም ሊሆን የሚችለው ህግ አውጪው እንደአንድ ማክበጃ ምክንያት አድርጎ አይቷቸው ሊሆን ይችላል እንዳንል ከአንድ በላይ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ድንጋጌ ውስጥ ያስቀመጣቸው ማክበጃዎች ተመሳሳይነት ስላላቸው ሊሆን ይችላል በሚልም ሊታይ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዶቹ ምክንያቶች ጎን ለጎን የሚኖሩ ሳይሆኑ በአማራጭ ሊኖሩ የሚችሉ ናቸው። ይሁንና ለምሳሌ በአንድ ድንጋጌ ውስጥ ያሉ ማክበጃዎች ከአንድ በላይ ተሟልተው ቢገኙና፣ አንዱ ብቻ ተሟልቶ ከተገኘው ጋር እኩል ቅጣቱ እንዲከብድ ተፈልጎ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ፣ ከአንድ በላይ ማክበጃ ምክንያቶች ያሉትና አንድ ብቻ ያሉት እኩል ይታያሉ ማለት ምክንያታዊ አይሆንም። ስለሆነም ሁለት አማራጭ መንገዶቹን ልንከተል እንችላለን። አንደኛው መንገድ በድንጋጌው ውስጥ ያሉትን ምክንያቶች አውጥቶ በመዘርዘር ለእያንዳንዱ ማክበጃ የሚጨመረውን መጠን በማስቀመጥ ቅጣቱን መወሰን ነው። ይህ ዝርዝሩን ረጅም ያደርገዋል። የማክበጃ ጊዜውንም በርካታ ያደርገዋል። በሌላ በኩል አሁን በድንጋጌው ያለውን ቁጥር እንዳለ በመውሰድ፣ ለእያንዳንዱ አጠቃላይ ሬንጅ በማስቀመጥ፣ ዳኛው እንደምክንያቶቹ ብዛት መጠን በሬንጁ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው እንዲወስን እድል መስጠት ነው። ይህ አማራጭ ቁጥሩን አነስ ያደርገዋል። ለዳኛው ዲስክሬሽን ሰፋ ያለ እድል ይሰጣል። ለቅጣት ማንዋሉ ዝግጅትም ቀላል ይሆናል። ከዚህ በመነሳት በዚህ ሰነድ ሁለተኛውን አማራጭ ማለትም በአንድ ድንጋጌ ውስጥ ያሉ ማክበጃ ምክንያቶች (ለምሳሌ 84(1)(ሀ)) እንደአንድ ማክበጃ ምክንያት የሚወሰዱ ናቸው የሚል ነው። ይሁንና ለአንድ ማክበጃ ምክንያት ቅጣቱ ሲያድግ የቅጣቱ ሬንጅ ስላለው በሬንጁ ውስጥ በአንድ ድንጋጌ ውስጥ ያሉት ምክንያቶች እንደብዛታቸው መጠን የሬንጁ ጣሪያ አካባቢ ዳኛው ቅጣቱን ሊያስቀምጥ ይችላል። በዚህ መልኩ ሚዛናዊነትን ማስጠበቅ ይቻላል የሚል መነሻ አለው።

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜ አንድ ምክንያት ብቻውን የሬንጁን ከፍተኛ ሊያሰጥ ይችላል። ጨካኝነት ሲገለጽ በጣም የተለያየ መገለጫ ይኖረዋል። ይህ ማለት በአጭሩ ለምሳሌ በንኡስ አንቀጽ አንድ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ተሟልተው የተገኙት አንዱ ብቻ ቢሆን፣ እንደምክንያቱ ባህርይ በሬንጁ ዝቅተኛ መነሻ ሊያስቀምጥለት፣ ወይም ብቻውን በጣም ከባድ በመሆኑ ከፍተኛው ጣሪያን ሊወስን ይችላል። በሌላ በኩል ከአንድ በላይ የሆኑ ምክንያቶች በመኖራቸውም እንዲሁ ወደጣሪያው ሊደርስ ይችላል፣

[32] የወንጀል ህግ ቁጥር 183

ወይም ከጣሪያው ቀንሶ ሊወስን ይችላል። ይሁንና በዚህም ሆነ በዚያ ዳኛው ከወንጀል ድርጊቱ ጋር በማነጻጸር የሚወስነው ይሆናል ማለት ነው።

የማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቅጣቱ በምን ያህል ይከብዳል? የሚለውን በተመለከተ በዚህ ሰነድ በዩኤስ አሜሪካ የቅጣት ጋይድላይን ያለው ስልት ተወስዷል። አንድ ማክበጃ ምክንያት ከአለ ወደላይ አንድ እርከን ይጨምራል። ከአንድ በላይ ማክበጃ ካለ፣ በማክበጃው ቁጥር ልክ ወደላይ እየተደመረ ይጨምራል። ይሁንና በማክበጃው ምክንያቶች ለማንኛውም ወንጀል ከአምስት እርከን በላይ መጨመር አይቻልም። የሚጨመረው እርከን ለወንጀሉ በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው ከፍተኛ ጣሪያ የሚያልፍ ከሆነ፣ ወደጣሪያው በማውረድ ቅጣቱ ይስተካከላል ማለት ነው።[33]

iv. <u>የቅጣት ማቅለያዎችን አሰላል በተመለከተ፣</u>

በወንጀል ህጉ የቅጣት ማቅለያዎች መሰረት አድርጎ ቅጣቱ ሲቀል እስከምን ድረስ ሊወርድ እንደሚችል በቁጥር 179 ተመልክቷል። ስለሆነም የህግ አውጪው አላማና ፍላጎት ተግባራዊ መሆን ስለሚኖርበት፣ ይህንን አላማ ሊያሳካ በሚችል መልኩ የቅጣት ማቅለል ስራው ሊሰራ ይገባል ማለት ነው።[34]

በህጉ የተቀመጡት የቅጣት ማቅለያዎች አምስት ናቸው። ስለሆነም እነዚህ አምስት ማቅለያዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ በድንጋጌው ዝቅተኛ መነሻ ላይ ለሚገኝ የወንጀል ድርጊት በህጉ የተቀመጠው ዝቅተኛ ማቅለያ ላይ መውረድ ይኖርበታል። ከዚሁ ጋር በተጣጣመ መልኩም ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ደረጃቸው ከፍ እያለ የሚሄደው የወንጀል ደረጃዎች ቅጣቱ ሊቀልላቸው ይገባል።

ለምሳሌ በቀላል እስራት አንድ አመት የሚጀምር አምስት ማቅለያዎች ስለሚኖሩት አምስቱ ማቅለያዎችን መሰረት አድርጎ አምስት እርከን ሲቀንስ በትክክልም በህጉ 179 በተመለከተው መሰረት አስር ቀን የሚያስቀጣው እርከን ላይ ስለሚወድቅ ችግር የለውም።

ይሁንና ከአንድ አመት ጽኑ እስራት የሚጀምር የእስር ቅጣትን በሚመለከት ከ6 ወር በታች ስለማይሄድ በማቅለያው ተጠቃሚነቱ ይቀንሳል ማለት ነው። ስለሆነም አምስት ምክንያቶች ተሟልተው በሚገኙበት ጊዜ ከሚለው መነሻ በመነሳት አምስት እርከኖች ሊቀነስለት ይችላል። ይሁንና ከ6 ወር በታች ሊወርድ አይችልም። ስለሆነም በድንጋጌው መነሻ ቅጣቱ 1 አመት ጽኑ እስራት የሆነ አምስት ማቅለያ ምክንያቶች ቢኖሩት፣ አምስት እርከን ወደታች ሊቀንስ ይችላል። ይሁንና በምንም መልኩ ቢሆን ከ6 ወር በታች አይወርድም ማለት ነው።

[33] በወንጀል ህጉ ቁጥር 92 በአፍቅሮ ንዋይ ምክንያት በሚፈጸም ወንጀል ቅጣቱን አክብዶ እስከ ብር 100 ሺህ ድረስ እንደሚቀጣ የተቀመጠውን ይህ ማንዋል እንደሚከለክለው ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

[34] የማክበጃ ምክንያቶች በነጠላ ወይም በጥቅል በድንጋጌው አወሳሰድ ስልት በተመሳሳይ ለጠቅላላ ማቅለያ ምክንያቶችም ይሰራል።

በሌላ በኩል መነሻቸው ከአንድ አመት በላይ በጽኑ እስራት የሚያስቀጡትን በተመለከተ ከእነዚህ ጋር የተጣጣመ ስሌት መከተል ተገቢ ነው። ለዚህም ምክንያቱ በ179(ሐ) እንደተመለከተው፣

1. መነሻቸው 3 አመት ጽኑ እስራት የሆነ ቅጣቱ ሲቀል 1 አመት ጽኑ አስራት ይሆናል።
2. መነሻቸው 5 አመት ጽኑ እስራት የሆነ ቅጣቱ ሲቀል 1 አመት ጽኑ እስራት ይሆናል፣
3. መነሻቸው 7 አመት ጽኑ እስራት የሆነ ቅጣቱ ሲቀል 1 አመት ጽኑ እስራት ይሆናል፣
4. መነሻቸው 10 አመት ጽኑ እስራት የሆነ ቅጣቱ ሲቀል 1 አመት ጽኑ እስራት ይሆናል፣
5. መነሻቸው 15 አመት ጽኑ እስራት የሆነ ቅጣቱ ሲቀል 1 አመት ጽኑ እስራት ይሆናል፣

በዚህ መልኩ ለምሳሌ መነሻው 3 አመት ላይ ያረፈ ወንጀለኛና፣ መነሻው 10 አመት ላይ ያረፈ ወንጀለኛ አምስቱም ጠቅላላ ማቅለያ ምክንያቶች ተሟልተውላቸው ሲገኝ አንድ አመት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ሚዛናዊነትን የሚያሳጣ ይሆናል። ስለሆነም በሁሉም መካከል ሚዛናዊነትን ለመፍጠር እንዲቻል የሚከተለው አሰራር ተቀይሷል።

1. ከህጉ እንደምንረዳው፣ ከዝቅተኛው የጽኑ እስራት ከፍ ብሎ የሚገኘው የጽኑ እስራት መነሻ 3 አመት ጽኑ እስራት ነው። የሶስት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት ያለበት ቅጣቱ ሲቀንስ 1 አመት ስለሚሆን፣ የሚኖረው ቅነሳ ጊዜ በጠቅላላ 2 አመት ሲሆን፣ ይህም የጠቅላላው የ3 አመቱ 2/3ተኛ ነው። አንድ አመት የቅጣት መነሻ የሚገኝበት እርከን ደረጃ 7 ሲሆን፣ 3 አመት የቅጣት መነሻ የሚገኝበት እርከን ደረጃ 16 ነው። ስለሆነም በሁለቱ እርከኖች መካከል ያለው ልዩነት 9 እርከን ነው። 9 እርከን ከ10 የሚያንሰው በአንድ ስለሆነ፣ ለአምስት እርከኖች ለእያንዳንዳቸው የሁለት እርከን ቅነሳ የሚያመጡ ቢሆን ተቀራራቢ ውጤት ይሰጠናል። ስለሆነም ከሶስት አመት ጀምረው ለሚያስቀጡ የተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች ለአንድ ማቅለያ ምክንያት ሁለት እርከን የቅጣት ቅነሳ ይደረጋል ማለት ነው። ይሁንና ቅጣቱ ሲቀል ከጠቅላላው ዝቅተኛ 1 አመት በታች አይወርድም ማለት ነው።

   ምሳሌ፣

   - ወንጀለኛው ጥፋት የፈጸመበት የወንጀል ድርጊት በህጉ የተቀመጠው የቅጣቱ መነሻ 3 አመት ከሆነ፣ እና ወንጀለኛው ከፈጸመው የወንጀል ባህርይ አንጻር በእርከን 16 (ከ3 አመት-3 አመት ከ7 ወር) ውስጥ የሚወድቅ ቢሆን እና አምስት ማቅለያዎች ሁሉ ተሟልተው ቢገኝ ለእያንዳንዱ ሁለት እርከን ሲቀነስ ዝቅተኛው እርከን 6 (ከ8 ወር-1 አመት) ውስጥ ይወድቃል። ይሁንና ደረጃ ስድስት መነሻው ከአንድ አመት በታች ስለሆነ፣ ወደእርከን 7 (ከ1 አመት-1 አመት ከ3 ወር) ተስተካክሎ በዚህ ውስጥ ቅጣቱ ይጣላል ማለት ነው።
   - ወንጀለኛው ጥፋት የፈጸመበት የወንጀል ድርጊት በህጉ የተቀመጠው የቅጣቱ መነሻ 3 አመት ከሆነ፣ እና ወንጀለኛው ከፈጸመው የወንጀል ባህርይ አንጻር በእርከን 20 (ከ4 አመት ከ5 ወር- 5 አመት ከ4 ወር)) ውስጥ የሚወድቅ ቢሆን እና አምስት ማቅለያዎች ሁሉ ተሟልተው ቢገኝ ለእያንዳንዱ ሁለት እርከን (በጠቅላላው 10 እርከን) ሲቀነስ ዝቅተኛው እርከን 10(ከ1 አመት ከ6 ወር-1 አመትከ10 ወር) ውስጥ ይወድቃል። ስለሆነም ቅጣቱ በደረጃ 10 ውስጥ ባለው ውስጥ ይወሰናል ማለት ነው።

- ወንጀለኛው ጥፋት የፈጸመበት የወንጀል ድርጊት በህጉ የተቀመጠው የቅጣቱ መነሻ 3 አመት ከሆነ፣ እና ወንጀለኛው ከፈጸመው የወንጀል ባህርይ አንጻር በእርከን 20 (ከ4 አመት ከ5 ወር- 5 አመት ከ4 ወር)) ውስጥ የሚወድቅ ቢሆን እና ሁለት ማቅለያዎች ሁሉ ተሟልተው ቢገኝ ለእያንዳንዱ ሁለት እርከን (በጠቅላላው 4 እርከን) ሲቀነስ ዝቅተኛው እርከን 16(ከ3 አመት -3 አመት ከ7 ወር) ውስጥ ይወድቃል። ስለሆነም ቅጣቱ በደረጃ 16 ውስጥ ባለው ውስጥ ይወሰናል ማለት ነው።

2. የቅጣት መነሻው 5 አመት ለሆነ (የቅጣት መነሻው 3 አመት ከሆነው ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን) ጠቅላላ የሚቀነሰው መጠን የ5 አመት 2/3ተኛ ይሆናል። ይህ 40 ወራት ይሆናል። ከመነሻው 5 አመት (60 ወራት) ላይ 40 ወራት ሲቀነስ 20 ወራት ሲሆን፣ ይህ የሚገኘው ደረጃ 11 (ከ1 አመት ከ8 ወር- 2 አመት ከ2 ወር) ላይ ነው። በደረጃ 11 እና በደረጃ 21 መካከል ያለው ልዩነት የአስር እርከን ስለሆነ፣ የቅጣት መነሻቸው 5 አመት ለሆኑ ወንጀሎች በማቅለያ ምክንያት የሚቀነስላቸው የሁለት እርከን ቅናሽ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ መልኩ በተመሳሳይ የቅጣት ማቅለያው እየተሰራ ይሰላል ማለት ነው።

3. የቅጣት መነሻው 7 አመት(84 ወራት)(እርከን 25) ለሆነው የዚህ 2/3ተኛው 56 ወራት ስለሚሆን፣ ይህ ከ84 ወራት ላይ ሲቀነስ የሚደረስበት 28 ወራት ወይም እርከን 13 ውስጥ የሚወድቅ ነው። በደረጃ 13 እና 25 መካከል ያለው ልዩነት 12 እርከን ሲሆን ይህ በአማካይ ለእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት የሁለት እርከን የቅጣት ቅነሳ የሚኖር ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ አራተኛና አምስተኛ ማቅለያዎች የሶስት እርከን ቅናሽ ይኖራቸዋል ማለት ነው።[35]

4. የቅጣት መነሻው 10 አመት(120 ወራት)(እርከን 29) ለሆነው የዚህ 2/3ተኛው 80 ወራት ስለሚሆን፣ ይህ ከ120 ወራት ላይ ሲቀነስ የሚደረስበት 40 ወራት በእርከን 17 (ከ3 አመት ከ3 ወር-3 አመት ከ11 ወር) ውስጥ ነው። በደረጃ 17 እና 29 መካከል ያለው ልዩነት 12 ሲሆን ልክ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 3 በተመለከተው መሰረት ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ማቅለያዎች ሁለት እርከን ቅናሽ የሚኖራቸው ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ አራተኛና አምስተኛ ማቅለያዎች የሶስት እርከን ቅናሽ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

5. የቅጣት መነሻው 15 አመት(180 ወራት)(እርከን 34) ለሆነው የዚህ 2/3ተኛው 120 ወራት ስለሚሆን፣ ይህ ከ180 ላይ ሲቀነስ የሚደረስበት 60 ወራት በእርከን 21 (ከ5 አመት-6 አመት) ውስጥ የሚወድቅ ነው። በደረጃ 21 እና 34 መካከል ያለው ልዩነት 13 እርከን ሲሆን ይህ በአማካይ ለእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት የሁለት እርከን የቅጣት ቅነሳ ያመጣና በቀሪነት ከሶስተኛው እስከ አምስተኛው ላሉት የቅጣት ማቅለያዎች የ3 እርከን ቅናሽ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

6. በህጉ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሌላ ለጽኑ እስራት መነሻዎች ከአሉ፣ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሰረት 2/3ተኛ በመቀነስ ቅጣቱ ሲቀል የሚደርስበትን ማወቅ ይቻላል። በዚህ መሰረት ለእያንዳንዱ ማቅለያ ስንት እርከን መቀነስ እንደሚቻልም ማወቅ ይቻላል ማለት ነው።

7. እንደሚታወቀው ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣት የሚያቀሉት ማክበጃ ምክንያቶች ከተደመሩ በኋላ ስለሚሆን፣ ዳኛው ለወንጀሉ መነሻ በሆነው እርከን ላይ ማክበጃዎችን መሰረት አድርጎ ቅጣቱን ካሳደገ በኋላ፣ የቅጣት ማቅለያን መሰረት በማድረግ

[35] ትርፍ የሆነው እርከን ለመጨረሻዎቹ ማቅለያዎች ከሚሆን፣ ለመጀመሪያዎቹ ማቅለያዎችም ማድረግ ይቻላል። አጠቃላይ ውጤቱን አይቀይረውም።

ቅጣቱን ሲያቀል የሚጠቀመው ስሌት ለወንጀሉ ድርጊት መነሻ በሆነው የቅጣት መነሻ መሰረት የተቀመጠውን የማቅለያ ስሌት ነው።

ምሳሌ፣

- ወንጀል አድራጊው ጥፋት የፈጸመበት ወንጀል በድንጋጌው የተቀመጠው የቅጣት መነሻ 3 አመት ጽኑ እስራት ቢሆን እና ይሁንና በደረጃውም ሆነ በሌሎች ማክበጃ ምክንያቶች የደረሰበት የቅጣት እርከን ከአምስት አመት በላይ ቢሆን (ለምሳሌ እርከን 22 (ከ5 አመት ከ6 ወር-6 አመት ከ7 ወር)፣ የማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ማቅለያዎች የሚያስገኙት የማቅለያ መጠን ለ3 አመት መነሻ ተደርገው የተመለከቱት እንጂ፣ በጽኑ እስራት ከ5 አመት ጀምሮ ለሚያስቀጡት የተቀመጠው አይሆንም።

v. <u>ተደራራቢ ወንጀል በሆነ ጊዜ፣</u>

በህጉ ላይ እንደተመለከተው ለእያንዳንዱ ወንጀል የሚያርፍበትን የወንጀል ደረጃ ላይ ቅጣት በማስቀመጥ የሚወስነውን የቅጣት መነሻ መሰረት በማድረግ ቅጣቶቹን ከደመረ በኋላ፣ የቅጣቱ ድምር የሚገኝበትን ዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ ላይ ይወድቃል። በመቀጠልም ጠቅላላ ማክበጃዎችን ማቅለያዎችን በቅደም ተከተል እየደመረና እየቀነሰ የመጨረሻው የቅጣት ደረጃ ላይ ይደረሳል ማለት ነው።

vi. <u>ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ፣</u>

- ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ እና ደጋጋሚ የሆነው ለአንድ ጊዜ ብቻ ከሆነ፣ ለአዲሱ ወንጀል ከተቀመጠው መነሻ ደረጃ በሁለት እርከን ከፍ በማለት የቅጣቱ መነሻ ይወሰናል። በቀጣይነትም ተደራራቢነት፣ ጠቅላላ ማክበጃዎች፣ ጠቅላላ ማቅለያዎች እንደቅደምተከተላቸው ተግባራዊ ይደረጋሉ።
- ጥፋተኛው በደጋጋሚ ወንጀል ከአንድ በላይ ወንጀሎች ፊጽሞ ከሆነ የአዲሱ ወንጀል መነሻ ከሆነው እጥፍ በመጨመር በሚገኘው ደረጃ ላይ የሚገኘውን ቅጣት መነሻ ያደርጋል። በቀጣይነት ተደራራቢነት፣ ጠቅላላ ማክበጃዎችን ወዘተ ቅደም ተከተሉን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ይወስናል። ይሁንና በህጉ ላይ ከተመለከተው ጠቅላላ የቅጣት ጣሪያ ማለፍ የለበትም።

vii. <u>ቅጣትን በመሰለው ማቅለልን በተመለከተ፣</u>

የወንጀል ህጉ አንቀጽ 180 ፍርድ ቤቱ በመሰለዉ ቅጣትን ማቅለል አለበት ወይም ይችላል ተብሎ በህግ ተደንግጎ በሚገኝበት ጊዜ የቅጣት ዓይነት ሳይወሰን ወይም መነሻ ቅጣት ሳይወሰን መነሻ ከሆነዉ ቅጣት ዝቅ አድርጎ ወይም ቀለል ያለ ሌላ ዓይነት

ቅጣት ተክቶ ለመወሰን ሥልጣን አለዉ ይላል። ቅጣት በመሰለዉ እንዲቀል በሚደረግበት ጊዜ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ከፍል ለየቅጣቱ ዓይነት ከተደነገገዉ መነሻ ዝቅ ሊል አይችልም ይላል። ስለዚህ በሚያሳምን ምክንያት በቂ ማብራሪያ በመስጠት፥-

- የገንዘብ መቀጮን ከ 10 ብር ሳይወርዱ መቅጣት፤
- ቀላል እስራትንም ከ 10 ቀን ሳይወርዱ መቅጣት፤
- ጽኑ እስራትንም ከአንድ ዓመት ሳይወርዱ ማቅለል ይቻላል ማለት ነዉ።

ከዚህ አንጻር በህጉ በግልጽ ቅጣትን በመሰለው ማቅለል ይችላል በሚል ተደንግጎ በሚገኝ ጊዜ በዚህ ሰነድ በተዘጋጀው መመሪያ ሳይገደድ ዳኛው ከህጉ ጠቅላላ ማቅለያ ሳይወርድ ቅጣቱን መወሰን ይችላል ማለት ነው።

viii. ተጨማሪ ማስታወሻዎች

1. ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ ከሆነ፣ ወንጀሉን በማነሳሳት ወይም በአባሪነት የሰራ በሆነ ጊዜ፣

በወንጀል ህጉ በሙከራ ለተደረገ ወንጀል፣ በማነሳሳትና በአባሪነት ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ ለታሰበው ወንጀል በህጉ በተደነገው ቅጣት በሁለት እርከን ዝቅ በማድረግ የቅጣቱ መነሻ ይሆናል።[36]

2. ዳኛው በህጉ ከተቀመጡት ውጪ ያሉ ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶችን በሚጠቀም ጊዜ

ዳኛው በህጉ ከተመለከቱት ውጪ ቅጣቱን ማቅለያ ወይም ማክበጃ ምክንያቶች የሚጠቀም በሆነ ጊዜ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶች ወይም ጠቅላላ ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ እንደሚደረገው የእርከን ጭማሪ ወይም ቅነሳ በማድረግ ማለትም ለማቅለያነት ወይም ለማክበጃነት የተቀመጠውን ጊዜ ተመሳሳይ በመጠቀም ቅጣቱን ማክበድ ወይም ማቅለል ይችላል፤፤ ይሁንና በህጉ ከተመለከተው ጣሪያ ወይም ዝቅተኛ ጣሪያ ማለፍ አይችልም።

3. በዚህ ማንዋል የተመለከቱት መገለጫዎች ቅጣት ሊወሰንበት የቀረበውን የወንጀል አይነት የማይወክሉ ሆነው በተገኙበት ጊዜ

እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥመው ዳኛው የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በዚህ ደረጃ በወጣላቸው ሊወክል የማይችል ከሆነ ተመሳሳይ ከሚሆኑት ጋር በማመሳሰል የቅጣት ደረጃውን ሊወስን ይገባል።

4. ዳኛው በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው ቅጣት ውጪ ቅጣት መጣል የሚችልበት ሁኔታ

ዳኛው በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን ፍትህ የሚዛባ ነው ብሎ ያመነ ከሆነ፣ የዚህን የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በዚህ ጋይድላይን ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል። ይሁንና ይህ በልዩ ሁኔታ በጣም አስፈላጊ እና ፍትህ በእርግጥም ይዛባል ተብሎ ሲታመን ብቻ ሊፈጸም የሚገባ ነው።

[36] US sentencing guideline manual 2C1.2. page 131

5. <u>የንብረት ግምትን መወሰንን በተመለከተ</u>

አብዛኛውን ከገንዘብ ጋር በተያያዘ የገንዘብ መጠኑን መሰረት በማድረግ የተቀመጡ ደረጃዎችን በሚመለከት በወንጀሉ ግምቱን ለማስወሰን በአቃቤ ህግና በተከሳሽ መካከል ክርክር ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ግምቱን ለማወቅ በፍትሀብሄር የካሳ መጠንን ለማወቅ የሚያስፈልገውን ያህል የማስረጃ ክርክር እንዲኖር አይጠበቅም። ወንጀሉ ከጥሬ ገንዘብ ጋር የተያያዘ ከሆነ አያስቸግርም። ይሁንና ወንጀሉ ከንብረት ወይም የውጭ ምንዛሪ ጋር የተያያዘ ከሆነ የሚከተሉት መመሪያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

1. ወንጀሉ የተፈጸመው በኢትዮጵያ ብር ካልሆነ፣ የገንዘቡ ምንዛሪ መጠን ቅጣቱ ሊወሰን ባለበት ጊዜ ባለው ምንዛሪ መሰረት ይሆናል።
2. ድርጊቱ ንብረት እቃን የሚመለከት ከሆነና በግምቱ ላይ ተከሳሹ ክርክር ካቀረበ እናም በዳኛው ግምት በአቃቤ ህግ የቀረበው ግምት የማይገባና ተገቢ ያልሆነ ነው ብሎ በገመተ ጊዜ በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ መሰረት ግምቱን ይወስዳል። (ለምሳሌ በበሬ ስርቆት የተከሰሰ ሰው ከሆነ፣ በሬው የሰባም ሆነ የከሳ በወቅቱ ያለው አማካይ የበሬ ዋጋ ተወስዶ ቅጣቱ ይሰላል።

b. <u>የሁለቱ አማራጭ ሞዴሎች ጠንካራ ጎንና ውሱንነት ትንተና የውሳኔ ሀሳብ</u>

<u>ሞዴል **1** (ቀመርን ወይም ፎርሙላን መሰረት ያደረገ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ፣</u>

በዚህ ሞዴል አማካይነት ቅጣታቸው እንዲወሰን የቀረቡት ከባድ ወንጀሎች የሚባሉ አስገድዶ መድፈር፣ ተራ ግድያ፣ ሽብርተኝነት ናቸው። ይሁንና ይህ ሞዴል ወይም አማራጭ ለሁሉም የወንጀል ድንጋጌዎች በተመሳሳይ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ነው።

የዚህ ሞዴል ዋና መገለጫዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. በዚህ ሞዴል የቀረበው መፍትሄ ለአንድ የወንጀል ድንጋጌ አንድ መነሻ እንዲኖረው ማድረግ ነው። መነሻውን ለመወሰን የተለያዩ አማራጮች ቀርበዋል።[37] አንደኛው አማራጭ በአንድ የወንጀል ድንጋጌ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ የወንጀል ውሳኔዎችን ለእያንዳንዱ የተወሰነውን ወስዶ በመደመርና አማካይ በማውጣት በዚህ የወንጀል ድንጋጌ ለሚወድቁት መነሻ የሚሆነውን ቅጣት ማስቀመጥ አንዱ አማራጭ ነው። ሁለተኛው አማራጭና ተቀባይነት ያገኘው በ 179 ቅጣቱ ሲቀል መነሻው በሆነውና በወንጀሉ በተቀመጠው ጣሪያ በመደመር የሚገኘውን ውጤት

[37] ስለአማራጮቹ የበለጠ ለመረዳት በተራ አገዳደል ወንጀል እና በአስገድዶ መድፈር የተዘጋጁትን ጽሁፎች ማንበብ ይረዳል።

ለሁለት በማካፈል ዝቅተኛው መነሻ፣ እንዲሁም በወንጀል ድንጋጌው በተቀመጠው የቅጣቱ መነሻን ከቅጣት ጣሪያው ጋር በመደመር ለሁለት በማካፈል የሚገኘውን ለቅጣቱ መነሻ እንደጣሪያ ማስቀመጥ ነው።

2. የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩበት ጊዜ ደግሞ እንደቁጥራቸው ብዛት በመነሻው የቅጣት መጠን በመቶኛ እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ በማድረግ መፈጸም ነው።

ይህ ሞዴል፣

1. በአንድ የወንጀል ድርጊት ለምሳሌ 665 ለሁሉም የወንጀል አፈጻጸሞች (የወንጀል ድርጊቱ 1000 ብርም ሆነ 100 ሺህ ብር መስረቅ ቢሆንም) ተመሳሳይ የሆነ መነሻ ያስቀምጣል። ስለሆነም እስከአሁን በአሰራር በአቃቤ ህጎች፣ በዳኞችና በሌሎችም ባለሙያዎች የነበረውን መነሻው ምን ይሁን የሚለውን ችግር ያስወግዳል።
2. በቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል የነበረውን ሰፊ ፍቅድ በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ለዳኛው የሚተወው ፍቅድ ጠባብ ያደርጋል። ስለሆነም ተቀራራቢ የቅጣት መነሻዎችን ለማስቀመጥ ይረዳል።
3. የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩበት ጊዜ ወጥነት ባለው መልኩ ለመጨመርም ለመቀነስም ያስችላል።

<u>ሞዴል **2** (ለወንጀል አፈጻጸሙ ደረጃዎችን በማውጣት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ)</u>

በዚህ ሞዴል መሰረት፣

1. በእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ ላሉት የወንጀል ድርጊቶች እንደአደገኛነታቸው ደረጃ በማውጣት ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ድረስ እንዲዘረዘሩ በማድረግ የቀረቡ ሲሆን፣ ለዝቅተኛው የቅጣት መነሻ በህጉ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ በማድረግ፣ እንደአደገኛነቱ ደረጃ የቅጣት መነሻው እየጨመረ እንዲሄድ በማድረግ የቅጣት መነሻ ያስቀምጣል።
2. ዳኛው ቅጣቱን ሲወስን ከወንጀሉ ልዩ ባህርይ (individualization) አንጻር ሊታዩና ለቅጣት አወሳሰን ሊረዱ የሚችሉ ፍሬነገሮች ስለሚኖሩ፣ ጠባብ የሆነ ለዳኛው ፍቅድ ስልጣን ትተዋል። ስለሆነም በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊቶች መካከል የሚሰጠው ቅጣት ተመሳሳይና ተቀራራቢ እንዲሆን ያደርጋል።
3. የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ በሚኖርበት ጊዜም በህጉ ከተቀመጠው ጣሪያ ወይም በህጉ ከተቀመጠው ዝቅተኛ ወለል ሳያንስ ለመወሰን በሚያስችል መልኩ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ እኩል ዋጋ በመስጠት፣ በቅጣት ማክበጃው ቁጥር ልክ ቅጣቱ በምን ያህል እንደሚከብድ የሚያሳይ ስለሆነ፣ ወጥነትንና ተመጣጣኝነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው።

ይህ ሞዴል፣

1. በአንድ የወንጀል ድርጊት ውስጥ የሚወድቁ ቢሆንም እንደአደገኛነታቸው ደረጃ ስለሚያወጣና የቅጣት መነሻቸው የተለያየ እንዲሆን ስለሆነም ከወንጀል ድርጊቱ ጋር ተመጣጣኝነትን ለመፍጠር ያስችላል።

2. በቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል የነበረውን ሰፊ ፍቅድ በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ለዳኛው የሚተወው ፍቅድ ጠባብ ያደርጋል። ስለሆነም ተቀራራቢ የቅጣት መነሻዎችን ለማስቀመጥ ይረዳል።

3. የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች በሚኖሩበት ጊዜ ወጥነት ባለው መልኩ ለመጨመርም ለመቀነስም ያስችላል።

ሁለቱም ሞዴሎች በቅጣት አወሳሰን ያለውን ችግር ከመፍታት አንጻር ጠቀሜታቸው ግልጽ ነው። ይሁንና እያንዳንዱ ሞዴል የራሱ ተመራጭነት እና የራሱ ውሱንነት አለው።

1. ሞዴል አንድ ከሞዴል ሁለት ጋር ሲነጻጸር ቀላልና ለመፈጸም አያስቸግርም። ለሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ተጨማሪ ጥረት ሳይጠይቅ በዚሁ ሞዴል መሰረት መስራት ይቻላል። ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ የሚሆን አማካይ ማዘጋጀት ነው። ከዚህ አንጻር ተመራጭነት አለው።
2. ሞዴል አንድ በሌላ በኩል የአደገኛነታቸው ደረጃ ወይም የወንጀል ክብደታቸው የተለያየ ቢሆንም ለሁሉም አንድ መነሻ በማድረጉ ወጥነትን ያረጋግጣል እንጂ ተመጣጣኝነትን ከማረጋገጥ አንጻር ችግር አለው።

በተቃራኒው፣

1. ሞዴል ሁለት ወንጀሎቹን በአደገኛነታቸው ደረጃ ቅደም ተከተል የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ ተመጣጣኝነትን ከማረጋገጥ አንጻር የተሻለ ተመራጭነት ያለው ሲሆን፣
2. ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የወንጀል ደረጃዎችን ማውጣትንና የቅጣት መነሻዎችን መስራትን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ የዝግጅቱን ስራ ከባድ ያደርገዋል።
3. ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜ በወንጀል ደረጃዎቹ ውስጥ ሊወከል የማይችል የወንጀል ተግባር ሊያጋጥምና በየትኛው ደረጃ ላይ እንደሚቀመጥ ሊያስቸግር ይችላል። ወይም የትኛው የወንጀል ደረጃ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ሊያስቸግርና ሊያከራክር ይችላል። በዚህ መልኩ ችግሩ ሊነሳ የሚችለው ከገንዘብ ግምት ጋር በተያያዘ ሊሆን ይችላል።

ሁለቱም ሞዴሎች ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የራሳቸው ጠቃሚና ውሱንነት ያላቸው ሲሆን፣ ሁለት አማራጭ ውሳኔዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። እነርሱም፣

1. ከሁለቱ ሞዴሎች አንዱን መምረጥ፣ ወይም
2. ሁለቱንም ሞዴሎች ከወንጀል ድርጊቶቹ አንጻር አግባብነት ያላቸውን መርጦ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

ስለሆነም፣

1. ሞዴል ሁለትን ለከባድ ወንጀሎች ለምሳሌ እንደ ሽብርተኝነት እና አስገድዶ መድፈር መርጦ ሙከራ በማድረግ፣
2. ሞዴል አንድን በተዘጋጀላቸው የወንጀል አይነቶች ሙከራ በማድረግ፣

ከሚገኘው ተሞክሮና ልምድ በመነሳት ወደፊት ከፖይለት በኋላ አንዱን ሞዴል ወይም ሁለቱንም ሞዴል ጎን ለጎን ለማስኬድ የሚወሰንበት አቅጣጫ መምረጥ ቢቻል የሚል የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አስተያየት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማዘጋጀት ስራ ተጀመረ እንጂ አላለቀም። ዋናው ስራ የሚሆነው ከዚህ በኋላ ያለው ነው። ከዚህ አንጻር፣

1. ይህ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በአግባቡ ተግባራዊ እየተደረገና የተፈለገውን ውጤት እያመጣ መሆኑን መከታተል ያስፈልጋል።
2. ተግባራዊ በማድረግ ምን ችግሮች እንዳጋጠሙ፣ ከዚህ አንጻር ሊሸሻል የሚገባው የመመሪያው ክፍል መኖሩን አጥንቶ የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ ያስፈልጋል።
3. መመሪያው ዳኞች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከተቀመጠው ሬንጅ ውጭ ሊወስኑ እንደሚችሉ ያስቀምጣል። እነዚህ የዳኞች ውሳኔዎች በእርግጥም ተገቢ ውሳኔዎች ናቸው? ከዚህ አንጻርስ መመሪያውን ማስተካከል ያስፈልጋል? ወይስ ዳኞች ከመመሪያው ውጭ የሄዱበት ምክንያት በቂ አይደለምና ተመሳሳይ ነገር ወደፊት እንዳይፈጸም መመሪያ ማውጣት ያስፈልጋል? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በአግባቡና በስርአት እያጠኑ መመሪያውን የማሻሻል ስራ መስራት ያስፈልጋል።
4. የቅጣት አወሳሰን የተፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ የወንጀል ህጉን ማሻሻል የሚጠይቁ ጉዳዮች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚህን በጥናት መለየት ያስፈልጋል።
5. አሁን ጥናት የተደረገው በተወሰኑ የወንጀል ድንጋጌዎች ስለሆነ፣ በቀጣይነት በሌሎችም ድንጋጌዎችም ላይ መስራት ይጠይቃል።

ስለሆነም እነዚህ ሁሉ ስራዎችን የሚከታተልና የሚመራ አንድ ተቋም ማቋቋምን ይጠይቃል። በአሜሪካም በእንግሊዝም ለዚህ ተብሎ ቋሚ የቅጣት አወሳሰን ኮሚሽኖች ተቋቁመው ይሰራሉ። ጠቀሜታ እንዳላቸውም አረጋግጠዋል። ስለሆነም መመሪያውን ለማውጣት ስልጣን በተሰጠው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውስጥ ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ተጠሪ የሆነ አንድ ቋሚ አካል ማቋቋም ያስፈልጋል። ስያሜውና ዝርዝር አደረጃጀቱና አወቃቀሩ ወደፊት ሊወሰን ይችላል።

በመጨረሻ በዚህ ሰነድ የቀረቡት የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ የሚጀምሩበትን ጊዜ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። በመመሪያዎቹ መሰረት ለመስራት ገና ከክስ ዝግጅት ጀምሮ ተሟልተው ሊቀርቡ የሚገባቸው መረጃዎች እንደሚኖሩ መገመት ይቻላል። ስለሆነም መመሪያው ከመዘጋጀቱ በፊት የተዘጋጁ እና በክርክር ላይ ያሉ ጉዳዮች መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊው መረጃ ላይኖራቸው ይችላል። ስለሆነም መመሪያው ስራ ላይ እንደሚውል ከተወሰነ በኋላ የተወሰነ ጊዜ ባለጉዳዮች እንዲያውቁትና እንዲለማመዱት ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም መመሪያው ከወጣ በኋላ የተወሰነ የመዘጋጃ ጊዜ ቢኖር ጠቀሜታ ይኖረዋል በማለት ጸሀፊው አስተያየት ያቀርባል።

ማጠቃለያ

በወንጀል ህጉ ቁጥር 1 የወንጀል ህጉ አላማና ግብ መሆን ያለበት ምን እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል። ይህም የሚከተለው ነው።

‹የወንጀል ህግ አላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርአት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅ ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን፣ ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎቹና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከማድረግ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጸሙ ተጨማሪ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው› ይላል።

ይህንን አላማ እንዲያሳካም ቅጣት ወጥነት፣ ተመጣጣኝነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያመጣ ሊሆን ይገባል።

በዚህ ጽሁፍ የቅጣት ጋይድላይን ለማዘጋጀት በተመረጡት የወንጀል ድንጋጌዎችና በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ስለቅጣት አወሳሰን የተቀመጡት ድንጋጌዎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ቅጣቶች ወጥነት፣ ተመዛዛኝነት ያለው፣ፍትሀዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ አለመሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል።

በአጠቃላይ በተለያዩ የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መዝገቦች ላይ በተደረገው ምርመራ፣

- በየትኛውም መዝገብ ቅጣቱን ለመወሰን መነሻው ስንት መሆን እንዳለበት ተመልክቶ እንደማይታይ፣
- ዳኞች በማክበጃነት የቀረቡትንና በማቅለያነት የቀረቡትን ምክንያቶች የሚቀበለውና የሚቀበሉትንና የማይቀበሉትን ከለዩ በኋላ፣ ከምክንያቶቹ ጋር ግንኙነቱን ለማስረዳት በማይቻል መልኩ በጥቅሉ የቅጣቱ መጠን የሚያስቀምጡ መሆኑንም መረዳት ተችሏል።

ስለሆነም፣

- መነሻ የቅጣት መጠኑ ስንት እንደሆነ፣
- በማክበጃነት የተቀመጡት ምክንያቶች ቅጣቱን በማክበድ ያላቸው አስተዋጽኦ እንዲሁም ማቅለያ ምክንያቶች እንዴት አገልግለው ቅጣቱ እንደቀለለ

ለማወቅ እንደማይቻል፣ ስለሆነም በአጭሩ ቅጣቱን ለመወሰን በቀረቡት ምክንያቶችና በተወሰነው ቅጣት መካከል ያለው ምክንያታዊ ግንኙነትን ለማስረዳት የማያስችል መሆኑን በጽሁፉ በዝርዝር ተመልክቷል።

በቅጣት አወሳሰን በተነጻጻሪ የኮመንሎው ስርአት የሚከተሉት እነአሜሪካና እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ስርአት ጋር ተመሳሳይ ከሆነው የፈረንሳይና ጀርመን ቅጣት አወሳሰን በተሻለ ወጥነትን፣ ተመጣጣኝነትን፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማምጣት የሚያስችል እንደሆነ ተመልክተናል።

ከዚህ በመነሳትም በቅጣት አወሳሰን ጋይድላይን ዝግጅት ጥሩ ተሞክሮ ካላቸው አሜሪካና እንግሊዝ ተሞክሮ በመውሰድ፣ በአጠቃላይ የወንጀል ህጉን አላማ እንዲሁም በቁጥር 88 ንኡስ ቁጥር 2 ከተመለከተው ግብ አንጻር ዘላቂ በሆነ መልኩ ወጥነት ያለው የቅጣት አወሳሰን ስርአት እንዲኖረን የሚያስችል መፍትሄ ይህ ጽሁፍ ይዞ ቀርቧል። ከዚህ አንጻርም ሁለት አይነት የቅጣት አወሳሰን ሞዴሎች በዚህ ጽሁፍ ቀርበዋል።

በዋነኛነት የቀረቡት አማራጮች አንደኛው በቀመር (ፎርሙላ) ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ሁለተኛው አማራጭ የወንጀል ደረጃዎችን እንደክብደታቸው በማዘጋጀት ላይ የተመሰረተ ነው። በእነዚህ አማራጮችም ቀድሞ የነበረውን ሰፊ ልቅ ለማስወገድ የቅጣት መነሻዎች ተቀምጠዋል።

ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ወንጀልን መሰረት አድርጎ የሚጣል ቅጣት ከወንጀል አድራጊው ማንነት ጋርም የተያያዘ መሆን ስላለበት፣ ለዚህ የሚሆን ጠባብ ፍቅድ ስልጣን ለዳኞች ሊኖር እንደሚገባ በማሰብ በፎርሙላውም ሆነ በሰንጠረዡ ሰፊ ያልሆነ ለዳኞች ፍቅድ የሚተው እንደሆነ ያመለክታል።

የማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችም ለሁሉም በተመሳሳይ መልኩ ውጤት ሊኖራቸው በሚችል መልኩ የሚሰሉበትን ስርአት አስቀምጧል።

በዚህ መልኩ በመስራት በአገራችን በቅጣት አወሳሰን ወጥነትን፣ ተመጣጣኝነትን፣ ግልጽነትንና ተገማችነትን ለማምጣት በሚያስችል መልኩ ውጤት ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ይታመናል።

<u>ዋቢ ሰነዶች</u>

1. Sentencing Guideline Around the World.

2. United States Sentencing Commission Guideline Manual

3. **Sentencing in Germany: Basic Questions and New Developments** *By Professor Dr. Franz Streng∗* (pdf_vol_08_no_02_153_172_articles_streng>PDF

4. Sentencing Guidelines: Reflection on the Future (2001).

5. Sentencing and Punishment in the Netherlands (2003).

6. The Dutch Criminal Justice System. Organization and Operation.

7. magistrate court sentencing guideline

8. Guideline Judgments Case Compendium S G C Sentencing

9. Federal Sentencing Under the Advisory Guidelines: A Primer for the Occasional Federal Practitioner

10. United states Federal Sentencing guidelines http/www Ussc. Gov. http /Juris. Law. Pitt. Edu/World /Finland htm.

11. A research on “Sentencing Guidelines around the world” by Diane Machine and http (Canda. Justice. Gc/en/rs/rep/rr 02.12 nepdf

12. Sentencing in Germany at http: ll wings buffalo educ/law/bc/c/bclratticles (71. inster /Pdf/.

13. **Research on Sentencing: The Search for Reform, Volume l and II** http://www.nap.edu/catalog/101.html

14. **State Sentencing Guidelines** *Profiles and Continuum* www.pewcenteronthestates.org

15. የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ 1996

16. የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ህግ 1957

17. የተሸሻለው ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ 433/97